30
les nilotiques

የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ

# መግለጫ መፅሐፍ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም




soleb



ዳህለክ
መረብ
አዱሊስ
መጠራ
ደብረ-ዳሞ
ሳቢያ
የሃ
ጉንዳ-ጉንዴ
አክሱም
ሐውልቲ
ገርዓልታ
አዲ ገላሞ
ትግራይ
ሚካኤል አምባ
ዉቅሮ
ክዊሃ/ቢለት
መቀሌ
ማርያም ናዝሬት
ጎንደር
አዘዞ
ሚስፋስ ባሕሪ
ጣና
ይምርሐነ ክርስቶስ
ገነተ ማርያም
ላሊበላ
እመኪና መድሃኒዓለም
ደጋ እስጢፋኖስ
ሬማ መድሃኒዓለም
ላስታ
ሐይቅ እስጢፋኖስ
ዘይላ
ወሎ
አትሮንሳ ማርያም
መሻለ ማርያም
ጠጠር ጉር
መንዝ
ፊቂ ደቢስ
አምባ ገብርኤል
ራሳ
አስባሪ/ገንደበሎ
ፈረዋንዳ በሪ
ኖራ
ወለቃ
ደብረብርሃን
ይፋት
ሱሬ ቀበናዋ
ሃርላ
ደርቢጋ
እንሳላሌ
ራሬ
ሚጁ
ሸዋ
ሐረር
ጩርጩር
አዲስ አበባ
የረር ተራራ
አዳዲ ማርያም
አሶሎ
ፈጠጋር
ዳዋሮ
ጢያ
ሶዶ
ስልጤ
ዝዋይ
አርሲ
ሃድያ
ሻርካ
ባሊ
አባያ
ጋሞ
ቱቱ ፈላ
ጨልባ ቱቱቲ
0
100
200 km
የመካነ-ቅርስ ወይም ታሪካዊ ቦታዎች
ከተማ
ባሊ ታሪካዊ አካባቢ
ስልጤ አሁናዊ አካባቢ
Source : Map tiles by Stamen Design, under CC BY 3.0.
N
S

# የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ፤ አቀማመጥ ማሳያ ንድፍ

ተራ ቁጥር 1 - 18፣
ከገጽ 22-76 የሚገኙ
የተለያዩ ፎቶዎች የተወሰዱባቸውን
ቦታ ሲያመለክቱ ○፣ ደግሞ
ከመፅሐፋ ሽፋን ገጽ ፎቶ
ጋር ያገናኛል።



ሶሌብ አሳታሚ፣ በመጀመሪያ በጥንታዊ የግብፅ ታሪካዊ ስፍራዎች ላይ ተመርኩዞ ስራ የጀመረ፣ ኋላም የህትመት አድማሱን በማስፋት፣ የተለያዩ ዘመናት ታሪኮችን፣ እንዲሁም ከግብፅ (የግብፅ ጥናት) በተጨማሪ ሱዳንንና ኢትዮጵያን ያካተተ የናይሎቲክ ጥናቶች ህትመት ተቋም ለመሆን የበቃ ድርጅት ነው። የህትመቶች መለያ ቁጥር ቀደም ሲል ከታተሙ ውጤቶች የቀጥለ ሆኗል።
(Issn 1639-3465)

**English version**
print 26.00 euros
Isbn 978-2-918157-65-6
**free digital version**
Isbn 978-2-918157-66-3

**Amharic version**
print 26.00 euros
Isbn 978-2-918157-67-0
free digital version
Isbn 978-2-918157-68-7

**French version**
free digital version
Isbn 978-2-918157-69-4

**éditions Soleb 2025**

https://www.soleb.com/livres/addis-ababa/index.html

**የአክሱማውያን ገንቦ**
ከ2ኛው–4ኛው ክ.ዘ
ሸክላ፤ ቁመት 20 ሳሜ፣
ወርድ 17 ሳሜ፣
Medogue፣ ኮድ Je 1394
ገጽ 38

የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ

# መግለጫ መፅሐፍ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም

s o l e b

ማውጫ


**ቀዳሚ ቃል** በአንዷለም ግርማዬ 5

**ከሜዳ ወደ ግምጃ**
የዓውደ-ርዕይ ፈር ቀዳጅ
ክሌሞ ሜናር፣ሉሲል ደኒዞ እና አን-ሊዝ ጉዠ 7

**የኢትዮጵያ ጥንታዊነት**
የኢትዮጵያ ጥንታዊነት፤
ሉሲል ደኒዞ 15

የመጀመሪያው ሺህ አመት
ከኢትዮ-ሳባውያን ኃያልነት፣ እስከ አክሱም ዘመን ምስረታ
ሉሲል ደኒዞ 18

በሜዳ ፍየል ቅርጽ የተሰራ የማንነት መገለጫ
ሉሲል ደኒዞ 22

በለጽሑፉ መሰዊያ
ዮሐንስ ገ/ሥላሴ እና ሉሲል ደኒዞ 25

የሐውልቲ የተቀረጹ ምስሎች
ዮሐንስ ገ/ሥላሴ እና ሉሲል ደኒዞ 26

ተክሌ ሐጎስ እና ሉሲል ደኒዞ
ሕሉፍ በርሔ 30

አክሱም፤ በቀይ ባህር አካባቢ የነበረ የአፍሪካ አስተዳደር
ሉሲል ደኒዞ 32

የአክሱም ሳንቲሞች
አየለ ታሪቀኝ 36

የአክሱማውያን ባለ ሦስት እግር ማሰሮ
ሕሉፍ በርሔ እና ሉሲል ደኒዞ 38

የአደን ተምሳሌት መቅረዝ
ሉሲል ደኒዞ 40

**የመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያ**
በእምነትና ንግድ መንታ መንገዶች ላይe
አሜሊ ሼክሩን እና ማሪ-ሎር ዴራ 43

አብያተ-ክርስቲያናት
ማሪ-ሎር ዴራ እና ደረሰ አየናቸው 45

የአዋጅ መስቀል
ክሌር ቦስክ-ቴሴ 49

የቤተ-ክርስቲያን ካስማ
ክሌር ቦስክ-ቱሴ 52

የዕጣን ማጨሻዎች
አን-ሊዝ ጉዦ እና ማሪ-ሎር ደራ 54

የኢትዮጵያ ሱልጣኔቶች
አሜሊ ሼክሩን እና ቲሞቲ ኢንሶል 56

አረቢኛ ጽሑፍ አዘል የመቃብር ላይ ድንጋይ
ዡሊያ ሎአዞ 58

ፊደላት-አዘል የጌጣጌጥ ቅርጽ-ማውጫ
ሲሞ ዶርሶ 60

ሀኩናዎች
ሲሞ ዶርሶ፣ አሜሊ ሼክሩን እና ሮማ መንሷ 62

የቻይና ሸክላ ስባሪዎች
ሃና ፓርሰን-ሞርጋን 64

የግዙፍ ድንጋዮችና ሐውልቶች ባህል
አን-ሊዝ ጉዦ እና አለባቸው በላይ 66

የትክል ድንጋይ ስባሪ
አን-ሊዝ ጉዦ እና አለባቸው በላይ 70

ባለ-ዳሌ ገንቦ፤ የሻይ ባህል መገለጫ
አን-ሊዝ ጉዦ እና በርትራን ፖአሶኔ 72

ጨሌዎች (ዶቃዎች) ከመንዝና ጨርጨር
አለባቸው በላይ 74

**የአርኪኦሎጂ ሳይንስ** 77

የድንጋይ ሥነ-ጥበብ
አንቱአን ጋሪክ 79

የሸክላ ሥነ-ጥበብ
አን-ሊዝ ጉዦ 80

የብረታ-ብረት ሥነ-ጥበብ
ካሮሊን ሮቢዮ-ብሩነር 81

**ማጠቃለያ** በዦን-ኒኮላ ባክ 83

**ማጣቀሻዎች / መፍትሔ ቃላት** 86

**ምስጋና / ጸሐፊዎች** 94

# ቀዳሚ ቃል

**ይህ የመግለጫ መጽሐፍ** (Guidebook)፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም፣ የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ መመሪያ ነው። የመግለጫ መጽሐፉ በመጀመሪያ ደረጃ የዓውደ-ርዕዩን ዓላማ እና የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ምርምር ወሰንን በማብራራት ይጀምራል፤ ይህ የጥናት ዘርፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1ኛው ሺህ ዓመት አንስቶ ከክርስቶስ ልደት በኋላ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ያደርሰናል፤ ይህ ጊዜ ደግሞ የጥንታዊ ሥርዎ-መንግሥታትን አነሳስና ውድቀት፣ ሐይማኖታዊ ሥርጭት እና ማህበረሰባዊ ለውጦች፣ የመሳሰሉትን ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚያስዳስሰን ነው። የአርኪኦሎጂ ምሁራን ከፖለቲካዊው ኃይልና ባህል በዘለለ የማህበረሰቡን የዕለት ተዕለት ኑሮ፣ እምነት እና ከመልክዓ-ምድሩ ጋር ተጣጥሞ የመኖሩን ሚስጥር ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ። በመካነ ቅርስ ቦታዎች፣ ሐውልቶች፣ እንዲሁም በቅሪተ-አካላትና ቁሶች ላይ የሚያደርጓቸው ምርምሮች ለዚህ ድጋፍ ናቸው።

ኢትዮጵያ በታሪካዊ ቅርሶቿ የምትታወቅ፣ ብዙ ቦታዎቿም በዓለም አቀፍ ቅርሥነት የተመዘገቡ፣ በዘርፉ ሀብት የበለጸገች ሀገር ነች። ይህ እውነታ ደግሞ በረጅምና ዘመናዊ የምርምር ሥራ ተደግፎ የተገለጠ ሲሆን፣ በታሪካዊ ሳይንስ ዘርፍ ከሰሃራ በስተደቡብ ካሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ አንዷ የጥናት ማዕከል እንድትሆን አስችሏታል። ምርምሩ፣ የግብርና ቴክኒኮችን፣ የንግድ አውታሮችን እድገት፣ የተለያዩ የፖለቲካ መዋቅሮችን ብቃት፣ እንዲሁም የተለያዩ ማህበረሰቦችን ተቻችሎ የመኖር ሚስጥር ለመረዳት ሚናው የጎላ ነው። ከዚህ በመነሳት ያለፉት 3000 ዓመታት ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ መሠረት የጣሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይቻላል።

በኢትዮጵያ፣ የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ጥናት የጀመረው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ በጀርመን የቅርስ ተመራማሪዎች፣ በጥንታዊቷ አክሱም ነው። ይህ ጥናታዊ ጉዞ ብዙ ጥንታዊ መታሰቢያ ቅሪት-ህንጻዎችን፣ እና የአክሱም የሥልጣኔ አሻራዎችን፣ ወደ ብርሐን በማምጣት የአካባቢውንና የአገሪቱን ያለፈ ታሪክ፣ የማወቅ ጉጉት በእጅጉ እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል። ከዚህ በመቀጠል በደቡብ ኢትዮጵያ የተካሄዱ ተከታታይና ተጨማሪ ጥናቶች የኢትዮጵያን ጥንታዊ የሥልጣኔ አሻራዎችን በመለየት ለታሪካዊ ግንዛቤ ዕድገት ተጨማሪ ግብዓት ሆነዋል። በኢትዮጵያ ቅርስ ጥናት ምስረታ ሂደት ቁልፍ ሚና ከተጫወቱ አካላት ውስጥ፣ ፍራንስዋ አዛይስ (François Azaïs) የተባሉት ሊቅ ሁሌም ተጠቃሽ ናቸው።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ዙሪያ ከተከናወኑ ተግባራት አንዱ ተቋም ግንባታ ሲሆን፤ ለዚህም በብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ የተጀመረው የአርኪኦሎጂ ክፍል፣ ቀጥሎም የኢትዮጵያ አርኪኦሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ተጠቃሽና ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት አመላካች ናቸው። እነዚህ ተቋማት፣ በጊዜ ሂደት አሁን የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን (Ethiopian Heritage Authority) በመባል ለሚታወቀው ተቋም መመስረት ምክንያት ሁነዋል። ስብስቦችን በማደራጀት፣ በዳሰሳ ጥናቶች (field surveys)፣ በቅሪተ-አካላት ቁፋሮ (excavations) ተግባራት ውስጥ ሁሌም ተጠቃሽ ናቸው። በሌላ በኩል የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል (French Center for Ethiopian Studies)፣ ከቀደምት ጊዜያት አንስቶ እስካሁን የዘርፉ ተባባሪ፣ የምርምር ሥራዎችም በከፍተኛ ሁኔታ እንዲስፋፋና ለሌላው እንዲተዋወቁ የሚያደርግ አጋር ድርጅት ነው።

የብሔራዊ ሙዚየሙ ስብስቦች፣ ይህንን ረጅም የምርምር ታሪክ የሚያሳዩ ምስክሮች ናቸው። እነዚህ ቅርሶች በጥናታዊ ቁፋሮ ወቅት የተገኙ ቁሳቁሶችንና ቅሪተ-አካላትን ያካትታሉ፣ እናም በጊዜ ሂደት ለተሻሻሉና እየጨመሩ ለሄዱ የዘርፉ ምርምር ፍላጎቶች ማሳያ ናቸው። መጀመሪያ ላይ ጥናቶች በአክሱም እና በኢትዮጵያ ክርስቲያን መካነ-ቅርስ አካባቢዎች ላይ ያተኮሩ ቢሆንም፣ ቀስ በቀስ ሌሎች አካባቢዎችንና ታሪካዊ ዘመናትን ያካተተ የምርምር ፕሮግራም ተዘርግቷል። ቅርሶቹ ከአክሱም፣ ሐውልቲ፣ የሃ፣ አዱሊስ፣ እና መጠራ የተገኙትን ያካትታሉ። እያንዳንዳቸው ስብስቦች የታሪክ አንድ ክፍል በመሆናቸው በማህበረሰቦች ወይም በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ የመረጃ ምንጮች ሆነው ያገለግላሉ።

የዓውደ-ርዕዩ ዓላማ፣ እነዚህን ግኝቶች ከታሪካዊ እና ባህላዊ ዕሴታቸው እንዲሁም ከግኝት ዓውዳቸው ጋር ለህዝብ ማቅረብ ነው። የተመልካቾችን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ መግለጫ ሰሌዳዎችን (notices)፣ካርታዎችን፣ እና የልኬት ሞዴሎችን (scale models) ተጠቅሟል፣ እነዚህም ቅርሶቹን ስለፈጠሩት ወይም ለአገልግሎት ስለሚጠቀሟቸው ማህበረሰቦች አኗኗርና ልማድ ለመረዳት ያግዛሉ። በተጨማሪም፣ የቅርሶቹ ትርዒት በጊዜ ቅደም ተከተል የተዘጋጀ፣ አስተማሪ ከሆኑ ቁሳቁሶች ጋር የተቀናጀ፣ እና የቅርስ ጥናት ዘዴዎችን ለማሳየት በሚችልና ደህንነታቸውን ባስጠበቀ መልኩ የቀረበ ነው። ከዛ በዘለለ፣ ቅርሶችን ለወደፊት ምርምር እና ግንዛቤ የመጠበቅ አስፈላጊነት ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ትኩረት ተሰጥቷል።

ይህ ዓውደ-ርዕይ ታዋቂ ቅርሶችን እና የዕለት ተዕለት ሕይወት ቁሳቁሶችን ያካትታል፣ እነዚህም በጥበባዊ ዋጋቸው እና የቀድሞውን ዘመን ማህበረሰብና ባህል ለማሳየት በሚያስችል ብቃታቸው ተመርጠዋል። አቀራረቡም፣ የኢትዮጵያን ባህል እና ቅርስ ብዝኀነት በሙሉ ገጽታው የማሳየት አካሄድን ተመርኩዟል፤ ይህም የመካከለኛ ዘመንን፣ ከአክሱም መንግሥት በፊት ወይም ከእሱ ጋር አብረው ይኖሩ የነበሩ፣ ግዙፍ ድንጋዮችን ወደ አገልግሎት በመቀየር ባህል የሚታወቁት ማህበረሰቦችን (megalithic cultures) ያካትታል። ጎብኚዎች፣ በእነዚህ ቅርሶች ትዕይንት፣ ያለፉት ዘመናት ተጨባጭ ቅሪቶች ጋር እንዲተዋወቁ፣ እና ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይጋብዛል።

በመሠረቱ፣ ይህ ዓውደ-ርዕይ፣ እና በተጓዳኝ የተዘጋጀው መግለጫ መጽሐፍ፣ በዐይነተልዩ የሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ መስታወት አንድ አካል ተደርጎ የሚቆጠር ነው። በተጨማሪም የታሪክ ዘመን አርኪኦሎጂ፣ ጥልቅና በብዝኃነት የበለጸገውን የአገሪቱን ባህል እና ቁስ ለመረዳት ብሎም ለማስረዳት ያለውን ሚና በግልጽ ያመለከተ ዓውደ-ርዕይ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ። ■

**አንዷለም ግርማዬ**

*መሪ ሥራ አስፈፃሚ*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም

ጥር 2017 ዓ.ም

# ከሜዳ ወደ ግምጃ፤

የዓውደ-ርዕይ ፈር ቀዳጅ

## አርኪኦሎጂ በኢትዮጵያ

አርኪኦሎጂ (ሥነ-ቅርስ) ፣ ያለፉና ጥንታዊ ማህበረሰቦችን፣ ቁሳዊ ባህል፣ መኖሪያ አካባቢ፣ የመታሰቢያ ሐውልቶችና የመሳሰሉ ቅሪቶችን መሰረት በማድረግ የሚያጠና የማህበረሰብ ሳይንስ ዘርፍ ነው። ሰዎች ከውልደት እስከ ሞት ያለፉበት የህይወት መንገድና ይዘታን፣ ይህም ከዕለት ተዕለት ኑሮ እስከ አመራር ወይም እምነት ሁኔታ ያለውን አካሄድ ለመረዳት ያስችላል። የዘርፉ ቀደምት ዓላማና ግብ፣ በጊዜ ሂደት ውስጥ የነበሩና ያለፉ፣ እንደ ወሰን፣ ባህልና ወግ፣ እንዲሁም አስተዳደራዊ መዋቅሮች ያሉ ገፅታዎችን በማጥናትና፣ በታሪክ ውስጥ ላሉ ክፍተቶች ማሟያ ማቅረብ ሲሆን አሁን ግን የማህበረሰብ ብዝሃነትንና በአንድና ውስን በሆነ አካባቢ ውስጥ የመኖር ጉዳይን የማጥናት ዓላማን በተጨማሪ አካቷል።

እንደ ኢትዮጵያ አውድ «ታሪካዊ አርኪኦሎጂ» የምንለው አንድ የትምህርት መስክ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱም ከክርስቶስ ልደት በፊት 1ኛው ሺህ ዓመት ጀምሮ እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለውን ታሪክ የሚሸፍን ነው። ይህም ጥንታዊቷንና በመካከለኛው ዘመን የነበረችውን ኢትዮጵያን የሚያጠና የአርኪኦሎጂ አንድ አካል ነው። ይህ ዘመን ግብርና የጀመረበትና ያደገበት፣ የንግድ እንቅስቃሴዎችና አውታሮች የሰፉበት፣ ረቂቅና ጠንካራ አስተዳደራዊ መዋቅሮች የጎለበቱበትና መታሰቢያዎቻቸው የገነኑበት፣ ፊደላትን ያጎለበቱና ፊደላት የሌላቸው ማህበረሰቦች በጋራ የኖሩበት 3 ሺህ ዓመታትን ይቃኛል። ስለሆነም የዛሬዋን ኢትዮጵያ መሰረት ለመረዳትና በትክክል ለማህበረሰቡ ለማስገንዘብ ታሪካዊ አርኪኦሎጂ አስፈላጊ ነው።

ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ በሆነው አየር ንብረቷ፣ የመልክዓ-ምድር አቀማመጧ፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ በርካታ ቅሪተ-አካል ቅርሶችን ጨምሮ ገና ባልተነኩ ሃብቶች የበለፀገች ሀገር ናት። በታሪካዊ ሳይንስ ረገድ ኢትዮጵያ ለጥናትና ምርምር የተነሣሳችና ከስሀራ በታች ካሉ ሃገራት ግንባር ቀደም ነች። ይህ ደግሞ በሀገር ውስጥና በተለያዩ ዓለማት ተመራማሪዎች ያላሰለሰ ጥረት፣ ከቅድመ-ታሪክ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ያሉ ጊዜያትን የሚሸፍኑ ዘርፈ ብዙ ጥናት ፕሮግራሞች መቀየሳቸው ያመጣው ስኬት እንደሆነ መጥቀስ ይቻላል።

## ከሳይንሳዊ አሰሳ እስከ ቅርስ ተቋም

ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአውሮፓውያን ተጓዦች ሲገለፁ የነበሩት ጥንታዊ መታሰቢያ ህንፃዎች እና ሐውልቶች እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ድረስ በደንብ አልተጠኑም። የቅሪተ-አካል ጥናት እንቅስቃሴ አሃዱ ብሎ ከጀመራቸው መታሰቢያዎች መካከል የአክሱም ግዙፍና ረጅም ሐውልቶች ይጠቀሳሉ። በወቅቱ በሚገባ ጥናትና ቁፋሮ የተደረገ ሲሆን የጀርመን አርኪኦሎጂካል አሰሳ ቡድን ይህን ተግባር ከውኗል። ቡድኑ የታሪካዊ አርኪኦሎጂ መነሻ ነጥብ ሊባል በሚችል መልኩ፣ የተለያዩ መታሰቢያ ቅሪቶችና ህንፃዎች ያስተዋወቀ ሲሆን እነዚህም ከክርስቶስ ልደት በኋላ የመጀመሪያው ሺህ ዓመት ላይ የነበሩ መሆናቸው፤ በተደረጉ በርካታና ተከታታይ ጥናቶች ለማረጋገጥ ተችሏል። ቀጣይ ጥናቶች በ1920ዎቹ እና 30ዎቹ በደቡብ ኢትዮጵያ በፍራንስዋ አዛይስ እና ፍሮቤኑስ ተቋም (Frobenius institute) በተከታታይ የተከናወኑ ሲሆን በጥናቶቹ በርካታ ጥንታዊ ትክል ድንጋዮችን ለአርኪኦሎጂው ዓለም በማስተዋወቅ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል።

የኢትዮጵያ አርኪኦሎጂ አባት ብለን ልንገልፀው የምንችለው አዛይስ፤ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ድጋፍ፣ ለአርኪኦሎጂ የተለየ ተቋም እንዲመሰረት በማድረግ በዘርፉ ከፈረንሳይ ጋር ልዩ የትብብር ማዕቀፍ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ አበርክቷል። ይህም እ.ኤ.አ 1952 ዓ.ም እውን ሲሆን ንጉሱ በሰጡት ተቋም፣ ከፈረንሳይ መንግሥት ከተላኩ ተመራማሪዎች ጋር በመተባበር ሥራ ተጀምሯል። ንጉስ ነገስቱ፣ ለዚህ ተቋም ወሳኝ የሆኑ ሃብቶችን በመለገስ፣ እንዲሁም ቅርስ ጥበቃን በተመለከተ ሕግ በማውጣት ጥምር ተሳትፎ አድርገዋል። በብሔራዊ ቤተ-መጻህፍት ውስጥ የነበረው ክፍል (እ.ኤ.አ 1952-1961 ዓ.ም) ኋላም የኢትዮጵያ አርኪኦሎጂ ተቋም (እ.ኤ.አ 1961-1966 ዓ.ም) በመባል፣ የተለያዩ የመስክ አሰሳዎች፣ ቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮዎች፣ እንዲሁም እስካሁን ጠቃሚ የዕውቀት ምንጭ የሆኑ የብራናና ሌሎች መፃህፍትን ቆጠራ በማድረግ ረገድ በርካታ ተግባራትን ማከናወን ችሏል። እ.ኤ.አ በ1966 ዓ.ም ተሻሽሎና የሥነ-ሕይወት ቅሪተ-አካል ጥናትን በማካተት፣ በመላው አገሪቱ ያልተገደበና ዘርፈ ብዙ

ተግባራት እንዲኖሩት ያስቻለ፣ የኢትዮጵያ ቅርስ አስተዳደር መስሪያ ቤት የተቋቋመ ሲሆን በሰሜን ኢትዮጵያና የቅሪተ- የሚደረጉት የቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮዎች በ1970ዎቹ ቀጥለዋል።

በደርግ ዘመነ መንግሥት (እ.ኤ.አ 1974-1991 ዓ.ም) የኢት ዮጵያ ቅርስ አስተዳደር መስሪያ ቤት ወደ ብሔራዊ ቅርስ ጥበቃና ጥናት ማዕከል ተቀይሮ በባህልና ስፖርት ጉዳዮች ሚኒስቴር ሥር ራሱን የቻለ ተቋም ሆነ። ሆኖም እስከ 1989 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የተለየ አዋጅ አልወጣም። የደርግ መንግሥት፣ በ1980ዎቹ መጨረሻ በአብዝኅኛዎቹ የውጭ ተመራማሪዎች ላይ እግድ የጣለ ቢሆንም ጥቂቶች ከኢትዮጵያውያን አቻዎቻቸው ጋር በመሆን በብዙ አካባ ቢዎች የቅርስ ክትትልና ምዝገባ በማድረግ ቆይተዋል።

ከደርግ ውድቀት በኋላ ወደ ስልጣን የመጣው ኢህአዴግ (እ.ኤ.አ 1991-2018 ዓ.ም) ዘመን ላይ፣ በ1990ዎቹ አዲስ የጥናት ምህዳር ሊመጣ ችሏል። እ.ኤ.አ 1994 ዓ.ም ተቋሙ በአዋጅ «የኢት ዮጵያ ቅርስ ጥበቃና ጥናት ማዕከል» ተብሎ (እ.ኤ.አ 1999-2000 ዓ.ም) ቆይቷል። በመቀጠልም «የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃና ጥናት ባለስልጣን» (እ.ኤ.አ 2000-2021 ዓ.ም) የሚል ስያሜ ይዞ ቆይቷል። በዚህም ጥናትና ምርምርን በማበረታታት፣ በመላው አገሪቱ የተሐድሶ ስልጠናዎችን በመስጠትና አዳዲስ ሰራተኞችን በመቅጠር ተቋሙን የማሳደግና የጥናት ምህዳሮችን የማስፋት ሥራ ተሰርቷል። እ.ኤ.አ 2010 ዓ.ም ተቋሙ ወደ ብሔራዊ ሙዚየም ግቢ በመዛወር የራሱን ቢሮ የገነባና ያደራጀ ሲሆን በመጨረሻም አሁን ወደ ሚጠራበት «የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን» ስያሜ በመሸጋገር በቱሪዝም ሚኒስቴር ሥር ሊሆን ችሏል።

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች፣ እ.ኤ.አ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ የተቋቋመው «ኢትዮ-ፈረንሳይ ጥናት ተቋም»፣ ኋላም እ.ኤ.አ 2007 ዓ.ም «የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል (CFEE)» የተባለው አጋር ድርጅት ጋር ይያያዛሉ። ይህ ማዕከል ከኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ጋር የሚሰራ እንዲሁም፣ በፈረንሳይ ብሔራዊ የሳይንስ ጥናት ማዕከል (CNRS) እና ውጭ ጉዳይ ሚንስቴር (MEAE) ሥር ያለ፤ ብዙ የኢትዮ-ፈረንሳይ የጋራ ፕሮግራሞችን የሚያስተባብር ተቋም ነው።

## የቅርስ ስብስቦች እንደ ታሪክ ምርምር መዛግብት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ስብስቦች በሰዎች የተለገሱ ወይም የተገዙ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቁሶችን ያካተቱ ቢሆንም፣ በዋነኝነት ግን በቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮ ወቅት የተገኙና የተሰበሰቡት ናቸው። የመጀመሪያው የስብስቦች መረጃ መዝገብ ወደ 1952 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የሚወስደን ሲሆን፣ ይህም የፈረንሳይ ተመራማሪዎች በተቋሙ የገቢ ዕቃዎች መዝገብ በመክፈትና መፅሔት በማዘጋጀት፣ ወደ ስብስቦች የሚካተቱ ቁሶችን መረጃ መያዝ የጀመሩበት ወቅት ነው። ይህ መፅሔት እስከ 1970ዎቹ የቀጠለና እስካሁን ድረስ ስብስ ቦችን ለመከታተልና ለማሰናዳት ደጋፊ በመሆን የሚያገለግል መረጃ ነው። ብዙ የጥናት ፍላጎቶችና የማወቅ ጉጉቶች፣ ብሎም የተለያዩ ቅሪተ-አካል ስፍራዎች መገኘት ለሙዚየሙ ስብስቦች መበራከትና ተቋማዊ ዕድገት አስተዋፅኦ አድርገዋል።

የኢትዮጵያ አርኪኦሎጂ ኢንስቲቲዩት (ተቋም) እ.ኤ.አ 1952 ዓ.ም ሲቋቋም፣ አጠቃላይ የአገሪቱን ቅርስ በማጥናትና በመጠበቅ ረገድ ቢሆንም፣ በወቅቱ ንጉሰ-ነገሥቱ አክሱምና የክርስቲያኑ መነሻ አካባቢዎች ላይ ትኩረት እንዲደረግ ይፈልጉ ነበር። በዚህም ጥንታዊ ስፍራዎች በነበሩት፣ የትግራይና የኤርትራ አካባቢዎች ላይ በዋነኝነት ጥናቶች ነበሩ። ይሁንና ጎን ለጎን መታሰቢያ ቅርሶችንና ቅሪተ-አካል ስፍራዎችን የመለየትና የመመዝገቡ ሥራ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ተጠናክረው ቀጥለው ነበር። ለዚህም የተፃፉ መዛግብት፣ የአየር ወይም የየብስ አሰሳ፣ እንዲሁም ከማህበረሰቡና የሀገር ሽማግሌዎች ጋር ይደረጉ የነበሩ ውይይቶች ብርቱ ድጋፍ ሆነው ያገለግሉ ነበር። የማህበረሰቡ ድጋፍ ማሳያ ምሳሌዎች ከነበሩ ሁኔታዎች ውስጥ፣ በስጦታ የተበረከቱ ጥንታዊ የደቡብ አረቢያ ቁሶች፤ ገበሬዎች በእር ሻዎቻቸው ላይ ድንገት የሚያገኙአቸውና ጠብቀው ያቆዩዋቸው ቁሶችና ሳንቲሞች፣ እንደ ሐውልቲ ዐይነት የቅሪተ-አካል ጥናት ቦታን መጠቆም የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው። እ.ኤ.አ ከ1953-1974 ዓ.ም በርካታ ቦታዎች፣ በአክሱም፣ ሐውልቲ፣ የሃ፣ አዱሊስ እና መጠራ ላይ የኢትዮጵያን ጥንታዊነት ከመረዳት አንጻር ብዙ የታሪክ እውቀቶችን የሚያሰፋ ጥናታዊ ተግባራት ተሰርተዋል። እስካ

ሁንም በተገኙ ቁሶችና ቅሪቶች ደረጃም እነዚህ ቦታዎች ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው። የቅሪተ-አካል ጥናት ላይ የሚደረጉ ቁፋሮዎች በአንድ ጊዜ መሆን የማይችሉና በተለያዩ ወቅቶች የሚደረጉ ዘመቻዎች ከመሆናቸው አንጻር ቁሳዊ ስብስቦችም በዚህ መልኩ የተጠራቀሙ ናቸው። ሌላው የተቋሙ የትኩረት አቅጣጫ ከመስክ በኋላ ያሉ ቁልፍ ተግባራትን ለምሳሌም፣ ስብስቦችን ማጥናት፣ መዘርዘር ወይም አግባብ ባለው ሰነድ ማስቀመጥና በኢትዮጵያ ዓመታዊ መፅሔት (Annales d'Éthiopie) ላይ ታትመው ለተማሪዎችና ምሁራን እንዲደርሱ ማድረግ ነበር።

ደርግ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ በሰሜን የአገሪቱ ክፍል የነበረው የመስክ ሥራ ቀነሰ። ይህም የጥናት አቅጣጫዎችን ወደ ሥነ-ሕይወት ቅሪትና ቅድመ-ታሪክ ዘመናት ብሎም ወደ ሌሎች ያገሪቱ አካባቢዎች፣ እንዲያዘነብሉ ያደረገ ክሥተት ሆኗል። ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 50 ኪ.ሜ ዕርቀት ላይ የሚገኘው የመልካ ቁንጥሬ ቅሪተ-አካል ቦታ መገኘት አንዱ ምሳሌ ነው። ወቅቱ ለታሪካዊ አርኪኦሎጂ ሌላ የእይታና የትኩረት አቅጣጫ ነፀብራቅ ይዞ መጥቷል።

የኢትዮጵያ አርኪኦሎጂ ተቋም ትኩረት ወደ ምሥራቅና ደቡብ ከመዞሩ አንጻር በርካታ ግዙፍ ትክል ድንጋዮችና መሰል መታሰቢያ ስፍራዎች ሌላ የጥናት ማዕከል ለመሆን በቁ። በሶሬ ቀበናዋ፣ ጋቲራ፣ ዲማና ጢያ የተደረጉ የቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮዎች ለዚህ ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው። ሌላው መካከለኛው ኢትዮጵያ በተለይም የንጉሳ ውያን አብያተ-ክርስቲያናት የተመራማሪዎችን ቀልብ የሳቡ የጥናት አቅጣጫዎች ሆኑ። ምንም እንኳን የአርኪኦሎጂ ጥናት በወቅቱ ባይደ ረግም፣ በጎንደርና ላሊበላ የሚገኙ አብያተ-ክርስቲያናት በወቅቱ በሥነ-ጥበብ ህንፃ ባለሞያዎች ጥናት ይደረግባቸው ነበር።

በደርግ ዘመነ መንግሥት የተገኙ ቁሳዊ ቅሪተ-አካላት ስብስቦች ጥቂት ናቸው። ይሄ ደግሞ ከቁፋሮ ይልቅ አሰሳና ምዝገባ ሰፊውን ጊዜ ይወስድ ስለነበርና እንዲሁም የመታሰቢያ ቦታዎች ባህሪና አገልግሎት እንደምክንያት ሊጠቀስ ይችላል። ከዛም አልፎ በወቅቱ የትኩረት አቅጣጫ በነበሩ ቦታዎች ምናልባትም የማህበረሰቡ ቁሳዊ ባህል አነስተኛ መሆን ከግምት ሊገባ ይችላል።

እ.ኤ.አ በ1990ዎቹና 2000ዎቹ የተከናወኑ የቅሪተ-አካል ጥናት ሥራዎች ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ማህበረሰብ ብዝሃነትና ያለፉ 3 ሺህ ዓመታት ታሪክ ግንዛቤ በማስጨበጥ ደረጃ አዲስ ምዕራፍ የከፈቱ ናቸው። ትኩረታቸውን በመካከለኛው ዘመን ታሪክ ላይ ያደረጉ፣ በርካታ ጥናታዊ ፕሮግራሞች የወቅቱን ማህበረሰብ አኗኗርና አሰፋፈር ከመመርመር አኳያ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ላይ የመሳተፍ ፍላጎት ያሳዩበት ወቅትም ነው። ይሄ ደግሞ በምሥራቁና መካከለኛው የአገሪቱ ክፍል የነበረውን ጥናታዊ ክፍተት ሊደግፍ ችሏል። መሰልና ቀጣይነት ያላቸው ፕሮግራሞች የአገሪቱን የኋላ ታሪክ ከመገንባትና ከማደስ አንጻር ፋይዳቸው ሰፊ ነው።

በአክሱም፣ ውቅሮ፣ ደሴ፣ ሃርላ እና መልካ-ቁንጥሬ ካሉ የቅሪተ-አካል ጥናት ስብስብ ቁሶች በስተቀር እ.ኤ.አ ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ በተከናወኑ ጥናታዊ ቁፋሮዎችና አሰሳዎች የተገኙ ሁሉም ቅሪተ-አካላት በኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ተመርጠው የተደራጁና የቀረቡ ናቸው። ከዕድሜ አንጻር ትንሹ ቢሆንም ቅሉ፣ በሥነ-ህይወት ቅሪተ-አካላት ሆነ ቁሳቁሶች አንጻር፣ ተቋሙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለና የበለፀገ፣ በብዙ ምሁራንም ቀን በቀን የሚጎበኝና የአዳዲስ መረጃዎች ምንጭ በመሆን የቀጠለ እንደሆነ መናገር ይቻላል።

## ታሪካዊ ዘመናትን በዐውደ-ርዕይ ማሳየት

የዓውደ-ርዕይ ፅንሰ-ሀሳብ ተቋሙ በተመሰረተ ማግስት የመጣ ሲሆን ይህም ጥናታዊ ግኝቶችን ለህዝብ ማጋራት ከሚል ራዕይ የመነጨ ነበር። ስብስቦችን በዐይነትና በተገኙበት ቦታ መሰረት የመለየትና ለጎብኚዎች ግልፅ በሆነ መልኩ የማስቀመጥ ሥራ እ.ኤ.አ በ1955 ዓ.ም በአርኪኦሎጂ ህንፃ ውስጥ የተጀመረ ሲሆን፤ ወቅቱ የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ 25ኛ ዓመት ኢዮቤልዩ በዓል የሚከበርበት ስለነበረ በእሳቸውና ለእሳቸው የተዘጋጀ ዓውደ-ርዕይ ብለን ልንጠራው እንችላለን። ከሁለት ዓመታት በኋላ ቅሪተ-አካላትንና ቁሶችን በሳይንሳዊ መንገድ መተንተንና ለእይታ የማቅረብ አዲስ ሃሳብ ተነስቶ ግንባታው በተጠናቀቀው ብሔራዊ ቤተ-መፃ ህፍት፣ በቅርሶች ሙዚየም ውስጥ ዐውደ-ርዕይ ተዘጋጀ። በወቅቱ



ማበጠሪያ-ቅርፅ ትክል ድንጋይ፤ ኦሶሎ፣ ስልጤ አካባቢ፣ እ.ኤ.አ 1967 ዓ.ም



በእንስሳ ቅርፅ የተሰራ ሸክላ፤ ሐውልቲ፣ እ.ኤ.አ 1959 ዓ.ም

ከቁሶች ገለፃ በተጨማሪ የተገኙባቸውን ቦታዎች በቃልና በካርታ ለማሳወቅ ጥረት ተደርጓል፤ በቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮና ዳሰሳ ወቅት ጥቅም ላይ ስለዋሉ የአሰራር ዘዴዎችና ፕሮቶኮል ለጎብኚዎች የማስረዳት ሥራም ተከናውኗል።

እ.ኤ.አ በ1966/67 ዓ.ም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም አምስት ኪሎ ላይ በታዋቂው አርበኛ ፊታውራሪ ሽመልስ ሐብቴ (የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሪ፣ የይምጡ በዝና ወንድም) ይዞታ ላይ የራሱን ቅጥር ግቢ ያገኘበት ወቅት ነው። የዚህ ቅጥር የኋላ ታሪክ የተወሰኑ ጉዳዮችን ይዟል። በመጀመሪያ በፋሽስት ኢጣልያ ተይዞ የነበረና አሁን የጣልያን ህንፃ ተብሎ የሚጠራው ቤት የተገነባበት ወቅትን (እ.ኤ.አ 1937-1941 ዓ.ም)፣ ከዛም ለልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴ መኖሪያ በመሆን አገልግሎት የሰጠበት (እ.ኤ.አ 1941-1944 ዓ.ም) በመጨረሻም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሆኖ ያገለገለበት (እ.ኤ.አ 1949-1966 ዓ.ም) ለሙዚየሙ ከመሰጠቱ በፊት የነበሩ ተጠቃሽ ታሪኮች ናቸው።

እ.ኤ.አ 1967-1999 ዓ.ም ስለነበሩ ዓውደ-ርዕዮች ይሄ ነው የሚባል በቂ መረጃ የለም፤ ነገር ግን የተመረጡ የሥነ-ህይወት ቅሪተ-አካላት፣ የቅድመ-ታሪክ፣ የህዝቦችን ባህል ወካይና የታሪክ ዘመን ቅርሶች በሁለት ክፍሎች ለእይታ ቀርበው ነበር። በጠቅላላው ግን ሰፊና ምቹ ማዕከል የማስፈለጉ ጉዳይ በ1970ዎቹ የተጀመረና፣ ቅርሶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ (Unesco) የማስመዝገብ ሂደት ጋር የተገናኘ ወሳኝ ምዕራፍ እንደሆነ መገለፅ ይቻላል።

አሁን ያለው ብሔራዊ ሙዚየም ህንፃ በ1980ዎቹ ግንባታው የተጀመረና በ1990ዎቹ ለአገልግሎት የበቃ ነው። ህንፃው የራሱ ቅርጽ ያለውና ዘመናዊ ሲሆን፣ በውስጡ ያሉ ትዕይንቶችም ብዙ ጊዜ ማስተካከያና ለውጥ ተደርጎባቸዋል። የሙዚየሙ ዓውደ-ርዕይ እሳቤዎች በአራት የትርኢት ክፍሎች የተከፈሉ ሲሆን፤ የሥነ-ህይወት ቅሪት እና የቅድመ-ታሪክ፣ የታሪካዊ አርኪኦሎጂ፣ ሥነ-ጥበብና፣ የማህበረሰቦች መንፈሳዊና ባህላዊ ቁሶች በመባል ይታወቃሉ። እያንዳንዳቸው የዓውደ-ርዕይ ክፍሎች ከ100-200 ስኩዌር ካሬ ሜትር ይዞታ ያላቸው ናቸው። በብዙ ጎብኚዎች የሚታዩ፤ በተለይም የትምህርት ተቋማት ተማሪዎቻቸውን በማምጣት ስለአገሪቱ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች እውቀት እንዲገበዩ የሚያደርጉበት ከመሆኑ አንጻር ታሪካዊ ጠቀሜታው እጅግ ከፍተኛ ነው።

የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ እ.ኤ.አ 1999 ዓ.ም የተደራጀ ሲሆን እ.ኤ.አ 2012-2022 ዓ.ም እድሳትና የመልሶ ማደራጀት ተግባራት ተከናውነውለታል። ቀደም ሲል በነበረው ዓውደ-ርዕይ፣ ዋና ዋና ቁሶች ለእይታ ቀርበው የነበሩ ቢሆንም፤ ስብስቦች የተገኙበትና የተቀመጡበት አውድ ከግልፅ ማስረጃ ጋር የተቃኘ ካለመሆኑ የተነሣ በዓውደ-ርዕዩ እሴትና ትርጉም ላይ ቅሬታ ያሥነሳ ነበር። ሌላው አንገብጋቢ ጉዳይ የመካከለኛው ዘመን ቅሪተ-አካል ጥናቶች በጣም ውስን ስለነበሩ፣ እና በዓውደ-ርዕዩም በቂ ቦታ ስላልተሰጣቸው፣ እድሳቱ አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም ይህ አዲሱ ዓውደ-ርዕይ ዘርፈ ብዙ እድሳትን ይዞ መጥቷል ማለት ይቻላል። ጊዜ ያለፈባቸውና ያረጁ ገለፃዎችና እይታዎች ተቀይረዋል፣ ከ2000ዎቹ ዓመታት በኋላ ብቅ ያሉ የመካከለኛው ዘመን ታሪካዊ ክሥተቶች፣ የምሥራቅና ደቡባዊ የአገሪቱ ክፍሎችን ታሪካዊ ክንውኖች አካተው ስለ ኢትዮጵያ ባህልና ቅርስ ያለው ገፅታ በተወሰነ መልኩ እንዲያድግ በር ከፍተዋል። ክፍሉ ለጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ጥሩ ማሳያ እንደመሆኑ፣ የክርስቲያኑን፣ የሙስሊሙን እንዲሁም የግዙፍ ድንጋይ ጥበብ ማህበረሰብ ባህልና አኗኗርን ከመጀመሪያው ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የሚያሳዩ ቅርሶችን ይዞ ጎብኚዎችን በሚገባ በማስተናገድ ላይ ይገኛል።

ዓውደ-ርዕዩ ለህዝብ ተቀባይ መሆን በሚችል መልኩ ትምህርታዊ አቀራረብ ለመጠቀም ሞክሯል፣ በተለይም የቅሪተ-አካል ጥናት ስፍራዎች ከሚነግሩን የማህበረሰቡ ቀደምት አኗኗርና ከሚያሳዩን ቁሳዊ ባህል አንጻር የጊዜ ቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተችሏል።

በዚህ የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ ስብስብ ገላጭ መፅሐፍ ውስጥ፣ የማህበረሰብ አርማና የትኩረት አቅጣጫ የሆኑ እቃዎች፣ እንዲሁም በእለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች በሰፊው ተካተዋል። በተጨማሪ ለትዕይንት የተመረጡት እቃዎች

በዓውደ-ርዕይ ዓላማና ግብ መሰረት ገላጭና ተመልካች በቀላሉ ሊረዳቸው የሚችሉ መሆናቸውን፣ ከግምት ያስገባ ሲሆን የእቃው ጥራትና ውበትም እንደ መስፈርት ተወስዷል። የአውደ-ርዕዩ ማጠቃለያ በአርኮኦሎጂ ጥናት ውስጥ የሚስተዋሉ ጥበባትን በማስተዋወቅ፣ ስለ መገልገያዎቹ አነስተኛ መግለጫ በመስጠት፣ ብሎም በቅሪተ-አካል ጥናት ውስጥ ያላቸውን ከፍ ያለ ቦታ በማሳየት፣ ለጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም እውቅናን ለመስጠት፣ መጠበቅና መንከባከብ እንዳለብንም በማመልከት ተቋጭቷል። ■ [ክ.ሜ፣ ሉ.ዴ፣ አ.ሊ.ጉ]



በብሔራዊ ቤተ-መጽሐፍት የተደረገ ዓውደ-ርዕይ፤ እ.ኤ.አ 1957 ዓ.ም

# የኢትዮጵያ ጥንታዊነት፤

## ከማኅበረሰቦች ብዝኀነት

## ወደ አንድ ወጥ ፖለቲካዊ መዋቅር

**«ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ»** የሚለው ቃል የሚወክለው ከታሪክ ዘመን መባቻ፣ እስከ መካከለኛው ዘመን ማብቂያ ድረስ ያለውን ጊዜ ነው። ይህም ጥንታዊ ጽሕፈት ከታየበት ከክርስቶስ ልደት በፊት 1ኛው ሺህ ዓመት፣ እስከ 7ኛው እና 8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአክሱም መንግሥት እስከወደቀበት ያለውን ድህረ ክርስቶስ ጊዜ የሚሸፍን ነው።

አሁን ባለው የዕውቀት ደረጃ፣ የጽሑፍ እና የአርኪኦሎጂ መረጃዎች የዛሬዋን ኤርትራን እና ደጋማ የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል የሚሸፍን ተዛማጅ ባህላዊ ዘመንን ለመረዳት አስችለዋል። ይህ ሰፊ ክልል የተለያዩ መልክዓ-ምድራዊ ገጽታን የተላበሰ ሆኖ በከፍታ ያሉ ደልዳላ ስፍራዎች የሚበዙበትና በቀይ ባህር ዳርቻዎች የሚዋሰን ነው። አካባቢያዊ ተፈጥሮና አየር ንብረት ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶችን ለመለየት፣ ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ብሎም ለገበያ ከማቅረብ አንጻር ለጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ሥልጣኔ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል።

የድንጋይ ወይም ባልጩት ቁሶችና መሳሪያዎች ጥናት እንደሚያሳየው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ6ኛው ሺህ ዓመት፣ በአፍሪካ ቀንድ እና በደቡባዊው አረብ መካከል ጥብቅ የንግድ ግንኙነት መኖሩን በተጨባጭ የሚያሳዩ ህያው የታሪክ ምስክር ናቸው። ይህም ከክርስቶስ ልደት በፊት በመጀመሪያው ሺህ ዓመት ተጠናክሮ ጥንታዊው ዘመን መገባደጃ ላይ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። የፊደላት መቀረፅ፣ እንደ ብረታ-ብረት ያሉ የፈጠራ ውጤቶች መዳበር፣ የመገበያያ ሳንቲሞች መመረት፣ የሐይማኖታዊ ሥርዓቶች ውህደትና መሰል ሁኔታዎች የዚህ እውነታ ዋነኛ ማሳያዎች ናቸው።


ጥንታዊቷ ኢትዮጵያን በመካነ-ቅርስ ጥናት ባለሞያዎች ከፍተኛ የሆነ ትኩረት እንድታገኝ ካስቻሉ መታሰቢያ ተቋማት አንጻር የየሃ ቤተ መቅደስና የአክሱም ሐውልቶች በግንባር ቀደምትነት ዋነኛ ተጠቃሽ ናቸው። እ.ኤ.አ. 1905 የአክሱም መካነ-ቅርስ ስፍራ የጀርመን አሳሾችን ቀልብ በመሳብ ሳይንሳዊ ጥናት ብሎም የሁለቱን ሀገራት ፖለቲካዊ ግንኙነት ከማጠናከር አንጻር የሚጠቀስ የመጀመሪያ የአርኪኦሎጂ ተልዕኮ ተከናውኗል፤ በዚህም መታሰቢያ ቅርሶች፣ መገልገያ ቁሶችና የተቀረጹ ጽሑፎች ላይ ጥናት የተደረገ ሲሆን እስካሁንም ድረስ የበርካታ ሀገራት የመስኩ ተመራማሪዎችን ቀልብ በመሳብ ረገድ አስተዋጾው የጎላ ሥራ ነው።

የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ጥናት በአአክሱም ሥርዎ-መንግሥት መታሰቢያ ቅርሶችና ቅሪቶች ዙሪያ የተመረኮዘ ነበር። እነዚህም ቅሪቶች የዘመን ልኬት ጉዳይን ለመወሰን በተመራማሪዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህ ደግሞ የአክሱም ሥርዎ-መንግሥት ከመፈጠሩ በፊት የነበሩ ቅሪቶችና አሻራዎች ቅድመ-አክሱም ዘመን፣ ሥርዎ-መንግስቱ ገናና በነበረበት ወቅት የአክሱም ዘመንና የአክሱም ዘመን ኃያልነት ማብቂያና በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ተመሰረተው የዛግዌ ሥርዎ-መንግሥት ድረስ ያለው ጊዜ ድህረ-አክሱም ዘመን የሚል ስያሜ እንዲያገኙ አድርጓል። እነዚህ የዘመን ልኬት አመላካች ስያሜዎች ምንም እንኳን የታሪክ ሙሉነትና ተአማኒነት ሁኔታ ላይ ክፍተት ቢኖርባቸውም እስካሁን ተመራማሪዎችን ያግባባሉ።

የታሪክና መካነ-ቅርስ ጥናቶች፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጥንታዊነት ወደኋላ ሁለት ሺህ አመታት የሚዘረጋ ታሪክ ያለው እንደሆነ ሲያመለክት፤ ይህም ብዝኃነትና የግል መገለጫ ባህል ባላቸው አርሶና አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ በተዋረድ የመጡትን፣ ኋላም የቀጠሉትን ንጉሳዊ አገዛዝ ሥርዓቶችን፣ ከግምት ያስገባ ነው። እነዚህ የስልጣኔ አሻራዎች በጥሩ መሰረተ ላይ በተገነባ፣ ከቅድመ-አክሱም ዘመን ጀምሮ እስከ አሃዳዊውና ጠንካራው የአክሱም ሥርዎ-መንግሥት ድረስ የዘለቀ፣ እጅጉን በተሳሰረ ማህበረሰብና ግዛታዊ መዋቅሮች፣ ይወከላሉ። ■ [ሉ.ዴ]



የሃ የሚገኘው ታላቁ የአልማቃህ ቤተ-መቅደስ፤ በ1950ዎቹ ዓመታት



ከታላቁ የየሃ ቤተ-መቅደስ ስር በሚገኘው የድንጋይ መቃብር፤
የተደረገ ስነ-ቅርስ ቁፋሮ፤ እ.ኤ.አ 1960 ዓ.ም



"ዙፋኖች" የአማልክት መቀመጫ፤ አክሱም
ጽዮን አካባቢ፣ በ1950ዎቹ ዓመታት



የአክሱም ሐውልት መገኛ ሜዳ፤ በ1950ዎቹ ዓመታት

## የመጀመሪያው ሺህ አመት፤
## ከኢትዮ-ሳባውያን ኃያልነት፣ እስከ አክሱም ዘመን ምስረታ

ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለው 2 ሺህ ዓመት በላይኛው (ናይል) አባይ ሸለቶ፣ በተለይም ከሱዳን ጋር በነበረው የባህል ልውውጥ በእጅጉ የሚታወቅ ሲሆን በ14ኛው ሺህ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ግን፣ ደቡብ አረቢያ የበላይነቱን ወስዳለች። የጽሑፍ ጥቅም ላይ መዋልን እንደ ማስረጃ ብናስቀምጥ፣ ከደቡብ አረቢያ ነገስታት በኩል የነበረው የባህል ልውውጥ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ለውጥ ማምጣቱ ይወሳል። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደተቀረፁ የሚታወቁት ጽሑፎች የራሳቸው የሆነ ልዩ መገለጫ አላቸው። ይሁንና ከደቡብ አረቢያ ፊደላት የተወረሱም ይገኙባቸዋል፤ ያ ደግሞ ለነበረው ጠንካራ የንግድ ግንኙነት ማስረጃ ነው።

በአፍሪካ ቀንድና አረብ ሰርጥ መካከል ሲከናወኑ ከነበሩት፣ የድንጋይ መሳሪያዎች፣ ከወርቅና ከዝሆን ጥርስ የተሰሩ፣ ውድ ጌጣጌጦች ልውውጥ በዘለለ፣ በወዲያኛው በኩል የነበረው፣ የእጣን ንግድን በበላይነት የመቆጣጠር ፍላጎት፣ ይበልጥ የመቀራረብ ምክንያት ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። ከዚህም የተነሣ እነዚህ አካባቢዎች በጥንታዊያን የግብፅ መዛግብት የተጠቀሰውንና የንግድ ልውውጥ ይካሄድበት እንደነበረ የተገለፀውን «የፑንት ምድር» እንደሚወክሉ ይታመናል። ከኢትዮጵያ እስከ ቀይ ባህር ዳርቻ ከተገኙ ቅሪተ-አካላት መረጃ ስንነሳ፣ በእርግጥ የደቡብ አረቢያዋ ንግስት ሳባ መንግሥት፣ የኢትዮጵያን ከፍተኛ ቦታዎች ጨምሮ፣ በቀጠናው በነበረው የእጣን ንግድ እንቅስቃሴ ላይ ግንባር ቀደም ተዋናይ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ከዛ ባለፈ፣ በቅሪተ-አካላት የተመለከተው የእደ-ጥበብ፣ የህንፃ ንድፍ፣ የሐይማኖትና የንግስና ሥርዓት ከደቡባዊው አረብ ባህል፣ በተለይም ከሳባ መንግሥት ጋር የተዛመደ ነው። ከዚህ አንጻር ጊዜው የኢትዮ-ሳባውያን ዘመን በመባል ይታወቃል። በአካባቢው አዲስ ይሰፍሩ የነበሩና በቦታው ያሉ ቀደምት ማህበረሰቦች የየራሳቸውን ባህል ጎን ለጎን ከማዳበር በተጨማሪ በመጋራት መርህ ግንኙነት ነበራቸው።

ቀደምት በቦታው የነበሩ ህዝቦች ታሪክ በአብዝሃኛው በኢትዮ-ሳባውያን መታሰቢያዎች ታሪክ የተዋጠና በበቂ ሁኔታም ያልተመዘገበ እንደመሆኑ፤ ከተለያየ ማህበረሰብ ምድብ፣ ምን ያህሉ በባህል ልውውጥ ክሥተት ውስጥ እንደተሳተፉ ለመገመት አስቸጋሪ ነው። ሆኖም የቅርብ ጊዜያት ጥናቶች እንደሚያስረዱት፣ በአካባቢው አዲስ ይሰፍሩ የነበሩ ህዝቦች የሚይዙት ቦታ ወይም ወሰን የተገደበ፣ ይሁንና ከጥቂት ግጭቶች ባለፈ ከቀደምት ነዋሪዎች ጎን ለጎን መበራከታቸውንና ማደጋቸውን እንደቀጠሉ ያስረዳሉ።

ዋነኞቹ የኢትዮ-ሳባውያን ዘመን ቅሪቶች በየሃ፣ ሐውልቲና ውቅሮ የተገኙ ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት 800 ዓመት አካባቢ ጀምሮ የተነሣን የአንድ ወይም የብዙ ነገስታት ስብስብ የሆነ ፖለቲካዊ ኃይል በአካባቢው እንደነበር ያመላክታሉ። መረጃዎች የሃን የኢትዮ-ሳባውያን የኃይል ማዕከል ወይም መቀመጫ ሲያደርጉ፣ ቤተ-መቅደስ፣ ቤተ-መንግሥትና ከድንጋይ የተቀረፁ የአስክሬን ማስቀመጫዎች፣ በስፍራው መገኘታቸው የሳባውያን ልሂቃንና ባለፀጋዎች በዚያ እንደነበሩ ማስረጃ መሆናቸውን በማቅረብ ነው። ይህን የኢትዮ-ሳባውያን የፖለቲካ አካል ለመረዳት በሐውልቲ ጎቦቼላ ተቀርጾ የተገኘው ጽሑፍ እጅጉን ጠቃሚ ነው። ይህ ጽሑፍ የዳኢማት ሙቃሪብ እና ኤስቢ (ስብ) የሚሉ ቃላትን የያዘ ሲሆን፣ ትርጉሙ በአንድ ንጉሥ የሚተዳደር ግዛትና የመንግስቱም መጠሪያ ስም ዳአማት እንደሚባል ያሳያል።

በቁጥር ብዙ የሆኑና የተቀረፁ ጽሑፎች ሐይማኖታዊ መታሰቢያ ከነበሩ ቅሪት ህንፃዎች አካባቢ የተገኙ ቢሆንም፤ ከጊዜ በኋላ ለአብያተ-ክርስቲያናት ግንባታ ጥቅም ላይ የዋሉም አሉ። እነዚህ ሐይማኖታዊ መታሰቢያ ህንፃዎች በዚህ ወቅት በደንብ ጥናት ከተደረገባቸው ቦታዎች ግንባር ቀደምና የኢትዮ-ሳባውያን ቤተ-መቅደስ በአካባቢው እንደነበር የሚጠቁሙ ናቸው። ከታላቁ የየሃ ቤተ-መቅደስ በተጓዳኝ በሐውልቲና ውቅሮ ተጨማሪ ሁለት መሰል መታሰቢያዎች በቁፋሮ ተለይተዋል። ተገጣጣሚ ድንጋዮችን በመጠቀም የተሰሩ የወለል ንጣፎችና ግድግዳዎች ቅርጽ እንደ ሲርዋህ ካሉ የደቡብ አረቢያ ቤተ-መቅደሶች ጋር በቀጥታ ተያያዥና ተመሳሳይ ናቸው። ከዚህ አንጻር፣ ምንም እንኳን ሌሎች እምነቶችና የአምልኮ ሥርዓቶች በአካባቢው



በግራት ባዕል ገብሪ የተደረገ ስነ-ቅርስ ቁፋሮ፤ የሃ፣ በ1970ዎቹ ዓመታት

ማህበረሰብ ውስጥ እንደነበሩ ቢጠበቅም፤ በኢትዮጵያ የተገኙት ሐይማኖታዊ ቅሪት ህንፃዎች ለጨረቃ ወይም ፀሐይ አምላክ ለሆነው አልማቃህ መታሰቢያ የተሰጡ እንደመሆናቸው በኢትዮ-ሳባውያን ዘመን ክብር ሲሰጣቸው የነበሩት አማልክት ከደቡብ አረቢያ ጋር ተመሳሳይ እንደነበሩ እርግጥ ነው።


ስለ ጥንታዊው የአምልኮ ሥርአትና በወቅቱ ሲኖሩ ስለነበሩ ህዝቦች በማስ ረጃነት ከሚያገለግሉ ነገሮች ውስጥ፣ ከቤተ-መቅደሶች ቅሪት አካባቢ የተገኙት፣ አማኞች ለአማልክት ክብር በስጦታ ያቀርቧቸው የነበሩ ግብዓቶች ተጠቃሽ ናቸው፤ አንዳንድ የድንጋይ መሰዊያና ዕጣን ማጨሻዎች ባለፀጋውንና የደቡብ አረቢያን ዕደ ጥበብ ተጠቃሚ መደብ ሲያመለክት፣ በሰው፣ በእንስሳ ወይ በሥነ-ህንፃ ንድፍ የተቀረፁ መስዋዕቶች ደግሞ ቀሪውን ህዝብና ባህል ለመረዳት ጠቅመዋል። አንዳንድ የመስዋዕት ቁሳቁሶች ከግብፅ፣ ከሱዳን ወይም ከህንድ ጋር ስለነበረው ቁርኝት ጠቋሚ ሲሆኑ፣ በአጠቃላይ ግን የቅድመ-አክሱም ማህበረሰብ የተለያየ ባህላዊ መገለጫ ወይም ልማድ እንደነበረው ማረጋገጫ ናቸው።

በሐውልቲና የሃ፣ ከመቅደሶች በተለየ ሁኔታ ለአስተዳደራዊ ወይም ንጉሳዊ መቀመጫ እንደነበሩ የተገመቱ ሁለት መታሰቢያ ህንፃ ቅሪቶች ተገኝተዋል። ከነዚህ አንዱ የሃ ካለው ቤተ መቅደስ በቅርብ እርቀት ከሚገኘው ግራት በአል ገብሪ የተስተዋለው፣ ሰፊ ቦታ ያካለለና የዕንጨት ማዕዘን ጥቅም ላይ የዋለበትን የግንባታ ጥበብ፣ የተላበሰ ቅሪት ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ500 ዓመት አካባቢ የፈራረሰ የኢትዮ-ሳባውያን ቅርስ ነው።

እነዚህ አካባቢዎች በኃይልና ሆን ተብሎ በተደረገ የጥፋት ዘመቻ ምክንያት የወደሙ የጥበብ አሻራዎች አሉ፤ ለምሳሌ የግራት በአል ገብሪ ውድመት በእሳት ነበር። ከዛ ቀጥሎ የቅድመ-አክሱም ማህበ ረሰብ፣ ከደቡብ አረቢያ አቻ ባህልና ወግ ጋር ጎን ለጎን እንዲሁም በጋራ የዳበረበትና ለመጪው የአክሱም መንግሥት መሰረት የጣለበት፣ ነገር ግን እስካሁን በውል ያልተመዘገበ ወቅት አልፏል። ■ [ሉ.ዴ]



እንደገና ጥቅም ላይ የዋለ በዋልያ ቅርፅ የተሰራ ህንጻ ጌጥ፤ የሃ፣ አቡነ አጽፈ ቤ/ክ፣ በ1950ዎቹ ዓመታት




የሃ፣ በተደረገ ስነ-ቅርስ ቁፋሮ የድንጋይ መቃብር ውስጥ የተገኙ ቁሳቁሶች፤ እ.ኤ.አ 1960 ዓ.ም

## በሜዳ ፍየል ቅርጽ የተሰራ የማንነት መገለጫ ከ8ኛ-6ኛ መቶ ክ.ዘ (ቅ.ክ.ል)

ከታላቁ የየሃ ቤተ-መቅደስ አጠገብ፣ ዓለት ተጠግቶ በተሰራ የመቃብር ቦታ፣ እ.ኤ.አ 1960 ዓ.ም በተካሄደ የአርኪኦሎጂ ቁፋሮ ጥናት አማካኝነት የተገኘና የኢትዮ-ሳባውያን ዘመን መገለጫ፤ ቅርስ

አራት ማዕዘን፣ የደቡብ አረቢያን ፊደላት የያዘ፣ ብሎም በዛው አካባቢ ታዋቂ በነበረው የሜዳ ፍየል አምሳል አራት እግሮች ያሉት፣ ሦስት ማዕዘን ፊት ገፅታ፣ ሁለት ቀንዶችና ጭራ-መሰል አካል፣ እንዲሁም በመሀሉ ፍርግርግ መሳይ ክፍተቶች ያሉት የመዳብ ቅይጥ ሥራ ነው። ስለ አሰራሩ ሲታሰብ፣የማንጠልጠያ ቀለበት ከመበየዱ በፊት፣ ቀልጦ የተዘጋጀውን መዳብ በቅርፀ-አካል ላይ በማፍሰስ መሰል ቅርጽ እንዲይዝ የተደረገ ነው። የኋለኛውም ተመሳሳይ ሲሆን ቀንዶቹ የተሰበሩ የሜዳ ፍየል ተምሳሌት አለው፤ አራቱ የፊደላት ሚስጥራዊ ፍቺ «ህንት» (hn`t) የሚል የሰው ስም ያመለክታል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ቅርስ ስብስብ፣ ከየሃ፣ መጠራ፣ ሐውልቲና ሳቢአ አካባቢዎች የተገኙ (ወደ አርባ የሚጠጉ የኢትዮ-ሳባውያንን ዘመን አመላካች ማኅተሞች) አካቶ ይዟል። መጠናቸው ከአንድ ሳንቲም እስከ ሁለት ሦስት እጥፍ፣ ቅርጻቸው ከቀላል እስከ ውስብስብ መስመሮችና የእንስሳ ቅርፅና ረቂቅ ንድፎች ይገኙባቸዋል። የአሳ፣ የአዕዋፋት፣ የበግ፣ የበሬ፣ የአንበሳና የሜዳ ፍየል የመሣሰሉትን እንስሳት ቅርጽ የያዙ ቁሶች፣ በቀጥታ ከአምልኮ ጋር የተገናኘ መገለጫ እንዳላቸው ይታመናል። እነዚህ የእንስሳት ቅርጾች ከደቡብ አረቢያ አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀሩ፣ በኢትዮጵያ ለሚገኙት ልዩ መገለጫ ናቸው።

እያንዳንዳቸው ልዩና የግል ቅርጽ መላበሳቸው፣ ብሎም የአንድን ግለሰብ ሙሉ ስም ወይም ምህፃረ-ቃል አመላካች ፊደላት መላበሳቸው፣ የማንነት ማረጋገጫ ቁስ (ማኅተም) ሊያስብላቸው ችሏል። በሌላ በኩል፣ አስተዳደራዊ ቁሳቁስ ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። አቀራረፃቸው፣ ለምሳሌ በጣት ቀለበት አምሳል መሰራታቸው፣ ለአያያዝ ቀላልና ሚስጥራዊ ከመሆናቸው ባለፈ፣ በቀላሉ እንደ ሸክላ ያሉ ወይም መሰል እቃዎች፣ ለአገልግሎት ከመድረሳቸው በፊት ይህ ቅርጸ-ማኅተም በላያቸው እንደሚረገጥ ይታመናል። ምናልባትም የንብረቱን ባለቤት ለማሳየት እንደማረጋገጫ ጥቅም ላይ ሳይውሉ አይቀርም። መሰል ህትመት፣ በተለያዩ የሸክላ ስባሪዎች ህንፃ ላይ ተገኝተዋል። ለምሳሌ የበሬ ቅርጽ የያዘ የሸክላ ስባሪ በየሃ፤ ግራት በአል ገብሪ ቤት መንግሥት መግቢያ ላይ ተገኝቷል። እነዚህ ውድ ሊባሉ የሚችሉ ቁሳቁሶች በአብዝሃኛው ከሌሎች መገልገያዎች ጋር በመሆን በመቃብር ጉድጓዶች መገኘታቸው ምናልባትም የንብረቶቹን ባለቤት ኃያልነት፣ ወይም በወቅቱ የነበረውን ታላቅነት አመላካች ሳይሆኑ አይቀሩም።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለተኛው ሺህ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ፣ መሰል ማኅተሞች ሸክላና ድንጋይን በመጠቀም በአካባቢው ይመረቱ ነበር። በአብዝሃኛው ሞላላ ቅርጽ የተላበሱ፣ የተለያዩ መስመሮችን ወይም ውስብስብ ንድፎችን የያዙ፣ እንዲሁም ተንጠልጣይ እንደነበሩ የሚጠቁሙ ቀዳዳዎችን የያዙ ናቸው። ለንግድ ልውውጥ ይውሉ የነበሩ ግብአቶችን፣ የባለቤትነት ማረጋገጫ አገልግሎት ከመስጠታቸው አንጻር፣ የንግድ ልውውጥ ምን ያህል በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደነበረውና እንዳደገ ያሳያሉ።

የኢትዮ-ሳባውያንን ዘመን ማኅተሞች ለየት የሚያደርጋቸው፤ እንደ ብረታ-ብረት ያሉ የተሻሉ ጥሬ ዕቃዎችን መጠቀማቸው፣ የእንስሳትን ምስል የተላበሱ ንድፎችንና የደቡብ አረቢያ ፊደላትን ማካተታቸው ነው። ይህ ደግሞ በቅድመ-አክሱም ዘመን ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች፣ ከደቡባዊው የአረብ ዓለም ጋር የነበራቸው የባህል ልውውጥ፤ ለኢትዮ-ሳባውያን ዘመን የባህል ማዕቀፍ መሸጋገሪያ ድልድይ እንደሆነ ማስረጃ ነው። ■ [ሉ.ዪ]

**በሜዳ ፍየል ቅርጽ የተሰራ የማንነት መገለጫ፤ I**

ከ8ኛ-6ኛ መቶ ክ.ዘ (ቅ.ክ.ል)

መዳብ ቅይጥ፤ ቁ. 6.5 ሳሜ፤ ስ. 8.7 ሳሜ፤ ወ. 1.3 ሳሜ

የሃ፤ ቀብር 6፣ ክፍል B፣ ኮድ Je 2220



## ባለጽሑፉ መሰዊያ
## ከ5ኛ-4ኛው ክ.ዘ (ቅክል)

ይህ ልዩ የሆነ መሰዊያ እ.ኤ.አ 1955 ዓ.ም በአርኪኦሎጂ ቁፋሮ ከተገኙ መሰል ስብስቦች ውስጥ አንዱ ነው። በትኩረትና በልዩ ጥንቃቄ ከመሬት መለየት ከመቻሉና ከግኝቱ አውድ በተጨማሪ፣ በደቡብ አረቢያና በሰሜናዊው የአፍሪካ ቀንድ የነበረውን የባህል ልውውጥ ለማጥናት አጋዥ የሆኑ ጽሑፎችን የያዘ የታሪክ ቁስ ነው።

ጥሩና ስስ በሆነ የኖራ ድንጋይ የተቀረጸው ይህ መሰዊያ አራት ማዕዘን ጎኖች አሉት። ከሥር ወደ ላይ ሦስት ዲግሪ አቀማመጥ ያለው መሆኑ የፒራሚድ ቅርጽ እንዲኖረው ያስቻለና፣ የደቡብ አረቢያ ቤተ መቅደስ ንድፍ ነጸብራቅ ነው። መሰዊያው ከሥር ጉጥ፣ አናት ላይ ፅዋ–መሰል ክፍት ቅርፅ፣ በላዩ ላይ የአልባስጥሮስ ሳህን መሰል ክብ ሽፋን የተቀመጠበት ነው።

በሁለቱ ጎኖች የጥንታዊ አፃፃፍ ስልትን የተከተለ፣ ይህም ከግራ ወደ ቀኝና ከቀኝ ወደ ግራ የሚሄድ፣ በሦስት መስመሮች የተከፋፈለ ጽሑፍን ይዟል። ፊደላቱ የመታሰቢያ ትርጓሜ ያላቸው፣ የመሰዊያውም ዕድሜ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ5ኛው–4ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ እንደሆነ ተገምቷል።

የተቀረጸው ጽሑፍ እንደሚከተለው ነው።

1. ←*(A) (symbol)*| *ṢBḤHMW (B)* | *w*| *LḤY* | *bn* | *FQM* |
2. →*(B) M* | *ḎMRYB* | *hqny*|
3. ←*(B) ’LMQH* | *lṭl* |

የሚል መልዕክት አለው። ትርጓሜውም፤ ስብህምው እና ልህይ፣ ከፍቅም ቤተሰብ፣ ከማሪብ ነገድ፣ ይህን መሰዊያ ለአማልክቱ አልመቅህ አቀረቡ በዚህም ዕድሜያቸው ረዘመ።

ይህ ጽሑፍ ስዕለት አቅራቢዎችን ስምና ዘር ግንዳቸውን፣ ስዕለት ተቀባዩን አማልክትና፣ የስዕለቱን ምክንያታዊ መረጃ፣ በማሳየት ረገድ የተሟላ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። እንዲህ ዐይነት ቅሪተ–አካል ግኝት ከብዙ በጣም በጥቂት የሚስተዋል ክሥተት ነው።

አልማቃህ በደቡብ አረቢያ የሚገኙ የሳባውያን አማልክት የበላይ አምላክ ነው፤ ጽሑፉም በቀጥታ ከሱ ጋር ይዛመዳል። የአርኪኦሎጂ ጥናት የተከናወነባቸው የኢትዮጵያ ቀደምት ቤተ–መቅደሶችና የተቀረፁ ጽሑፎችም፣ አልማቃህ በዳኣማት ሥርዎ–መንግሥት የሚወደስ ዋና አምላክ እንደ ነበረ በርካታ የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ። በተጨማሪ መቀመጫው ማሪብ (የአሁኗ የመን) ውስጥ የነበረው የሳባ ሥርዎ–መንግሥት ጠባቂ አምላክ ነበር። የዚህ ቦታ ስም በዚህ መሰዊያ ላይ መጠቀሱ ልዩ የጥናት ትኩረት እንዲሆን አስችሏል። ከደቡብ አረቢያ ባህረ–ገብ አካባቢ ወደ አፍሪካ ቀንድ ለነበረው ስደት ሳባ እንደምክንያት ከመቆጠሯ አንጻር በተጨማሪም የቤተሰብ ወይም xየዘር ግንድ ስም እንደሆነ የሚገመተው ፍቅም (Fqm) የሚለው ቃል በብዙ መሰል ጽሑፎች ግርብ (Grb) ከሚባል ስም ጋር ተጠቅሶ የመገኘቱ ሁኔታ በትውልዶች መካከል ወጥ የሆነ የመስዋዕት ሥርዓት እንደነበር ይጠቁማል።

ይህ መሰዊያ ከአክሱም 10 ኪ.ሜ እርቀት በሐውልቲ ቤተ–መቅደሶች ዙሪያ፣ ልዩ ስሙ ጎቦቼላ በሚባል አካባቢ፣ በተደረገ የአርኪኦሎጂ ቁፋሮ የተገኘ ነው። የመሰዊያውን ዕድሜ ለመለየት በተደረጉ የመጀመሪያ ናሙና ጥናቶች ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ5ኛ–4ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት የተገመተ ቢሆንም፣ ከቦታው ገፅታና ሲወርድ ሲዋረድ የተፈራረቀበት ዘመናትን የዋጀ ጥቅም አንጻር፣ ከጊዜ በኋላ የተደረጉ ተከታታይ ጥናቶች፤ ዳግም ዕድሜ ልኬት ማስፈለጉን ያነሳሉ። ይህ የመሰዊያ ድንጋይና ሌሎች ለመስዋዕት የቀረቡ ቁሳቁሶች፣ ቀደም ብለው በሌላ ሁኔታ ለስዕለት የዋሉና ከጊዜ በኋላ ወደ አካባቢው የመጡ ሳይሆን እንዳልቀረም ይገመታል። በሁለተኛ ደረጃ ቀደም ሲል የነበረው የዚህ መሰዊያ ክዳን መሰበሩ፣ቁርጥራጮችም በህንፃው ደቡባዊ ክፍል ግንባታ ወቅት ጥቅም ላይ ውለው መገኘታቸው፣ ከዛ በኋላ የአልባስጥሮስ ክዳን በምትክነት እንደተሰራ ሲታሰብ፣ የዚህን መሰዊያ ዕድሜ ከ3ኛው–2ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ከተገነባው የጎቦቼላ መቅደስ ዕድሜ ጋር ከማነፃፀር ይልቅ፣ ከዛ በፊት በአካባቢው ከነበረ ጥንታዊ መቅደስ የመጣ ለመሆኑ የአርኪኦሎጂ ባለሞያዎች ይሞግታሉ። የተለያዩ የመስዋዕትና ስዕለት ቁሳቁሶች ደግሞ ጥቅም ላይ ውለው መገኘታቸው፣ ምናልባትም የጎቦቼላ መታሰቢያ ስፍራ የአንድ ቤተሰብ የመቃብር ስፍራ ሳይሆን እንደማይቀርና፣ ለእነርሱና ለዕምነታቸው መታሰቢያ ሲባል አገልግሎት እንደቀጠለ ይገመታል። ■ [የ.ገ.ስ፣ ሉ.ዴ]



**ባለጽሑፉ መሰዊያ** 2

ከ5ኛ–4ኛው መቶ ክ.ዘ (ቅ.ክ.ል)

ኖራ ድንጋይ፤ ቁ. 44.5 ሳሜ፤ ስ.

28 ሳሜ፤ ወ. 24 ሳሜ

ሽፋን ድንጋይ (አልባስጥሮስ)፤ ቁ.

4 ሳሜ፤ ስ. 34 ሳሜ፤ ወ. 25 ሳሜ

ጎቦቼላ፣ ኮድ Je 110

## የሐውልቲ የተቀረጹ ምስሎች
## ከ5ኛ-4ኛ ክ.ዘ (ቅ.ክ.ል)

1950ዎቹ ለየት ያሉና፣ በርካታ የተቀረፁ መታሰቢያ ቁሶች ወደ ብርሐን የመጡበት ወቅት ነው። በሴት አምሳል የተቀረፁ ሁለት ሐውልቶችና ዙፋን መሳይ የተቦረቦረ ድንጋይ ከነዛ ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው። በወቅቱ በኢትዮጵያ እያደገ የመጣው የሰው አምሳል ቅርጻ-ቅርጽ ሥነ-ጥበብ ከአጎራባች ሀገራት ጋር፣ የባህልና ዕውቀት ውርርስ ጋር የተገናኘ ነው (በተለይም ከደቡብ አረቢያና ከአባይ ሸለቆ ሀገራት ጋር)።

ሐውልቲ በትግራይ ክልል ከአክሱም በ10 ኪ.ሜ እርቀት ላይ የምትገኝ ቦታ ናት። በዚህ ስፍራ እ.ኤ.አ 1959 በሁለቱም ጎን እኩል 11 ሜትር ስፋት ያላቸው 2 ባለአራት ማዕዘን የህንፃ ቅሪቶች በቁፋሮ ተገኝተዋል። በተጨማሪ ብዛት ያላቸው የስዕለትና መስዋዕት ማቅረቢያ እቃ ቅሪቶች፣ የተለያዩ እንስሳት ምስል ጥንብሎች፣ የሸክላ፣ የነሐስና መስታወት ዕቃዎች የመሳሰሉት በዚሁ ህንጻ ሥር ተገኝተዋል። በዘመናት ከነበሩት የአካባቢ ለውጥና ጥፋቶች አንጻር ትክክለኛ ዕድሜ ለመገመት ቢያስቸግርም፤ ሐውልቲ ከክርስቶስ ልደት በፊት ባሉት 5ኛ-4ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ የነበረች ሐይማኖታዊ ወይም በእጅጉ የሚፈራና የተከበረ ሥፍራ እንደነበረች መናገር ይቻላል። በስፍራው በተገኙ 2 ህንፃዎች መካከል ብዙ የሐውልት ስብርባሪ ቅሪተ-አካላት ተለይተዋል፤ ስብርባሪዎቹንም በመገጣጠም ሦስት መታሰቢያ ቁሶችን፣ ማለትም ሁለት የሰው-መሰል ሐውልትና አንድ ዙፋን ቀድሞ ወደ ነበሩበት ቅርጽ መገጣጠምና መጠገን ተችሏል።

በሐውልቲ በመጀመሪያ የተገኘው ሐውልት 80 ሳ.ሜ ቁመት ያለውና ከኖራ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተቀረጸ ነው። የዚህ ሰው-መሰል ሐውልት አናት ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የተገኘና በጥንቃቄ ከዋናው አካል ጋር እንዲጣመር የተደረገ ነው። ሐውልቱ አንዲት ሴት እጇን በጉልበቷ ላይ ጭና ያመለክታል። ፀጉሯ በአጭሩ ቁጥርጥር የተሰራ፣ ሦስት የአንገት ሃብሎችን ያጠለቀች፣ ቀበቶ መሰል ጉንጉን መቀነት በወገቧ የታጠቀች ምናልባትም ሸማ ቀሚስ የለበሰችን ሴት ያሳየናል።

ሌላው ቀልብ የሚስብ ገፅታ ደግሞ ሐውልቱ ስሩ ሻካራ እና ጉጥ ያለበት መሆኑ ሲሆን ምናልባትም ይህ ሐውልት የተለየ መቀመጫ ሐውልት እንደነበረው ያሳብቃል። በቅርብ እርቀት ሌላ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ አንድ ዐይነት ገፅታ ያላት፣ በርጩማ ላይ የተቀመጠች ሴት ሐውልት ተገኝቷል። ነገር ግን አናቷ በቦታው አልነበረም።

እነዚህ በሴት አምሣል የተቀረፁ ሐውልቶች፣ የመጀመሪያ ግኝት ባይሆኑም ሌሎች ተምሳሌቶች ጥቂት ናቸው። በብሔራዊ ሙዚየም ስብስብ ውስጥ ያለውና ከአዲ ገላሞ የተገኘው ጥንታዊና ቀሚስ የለበሰች ሴት ሐውልት ከመሰል ቅሪቶች ተጠቃሽ ነው። ቀሚሷ ያማረና አበባ መሰል ጌጣጌጦች ያሉበት፣ በርጩማ ላይ የተቀመጠችና፣ በሁለቱም እጆቿ የፈሳሽ ነገር መያዣ ወይም መስፈሪያ የያዘች ናት። የተቀረጸው ምስል ደረጃ መሰል መቀመጫና፣ በላዩ ላይ አዲስ ለሚወለድ ህፃን መልካም ምኞትን የሚገልጽ ጽሑፍ የተቀረጸበት ነው። እ.ኤ.አ 2007 ዓ.ም. ለአልማቃህ መታሰቢያ የተሰጠ ተመሣሣይ ሐውልት ውቅሮ አካባቢ፣ መቃብር ጋእዋ መቅደስ፣ ውስጥ የተገኘ ሲሆን ዕድሜውም ከክርስቶስ ልደት በፊት 8000 ዓ.ዓ ገደማ እንደሆነ ተገምቷል። ሌላው በዚህ ስፍራ ትንሽ የኖራ ድንጋይ ላይ አራት ማዕዘን መስመሮች ውስጥ የተቀረጸና በሐውልቲ የተገኙ ቁሳቁሶች ጋር ተመሳሳይነት ያለው አነስተኛ ሞዴል ቁስ ተገኝቷል።

**የሐውልቲ የተቀረጸ ምስል** 3

ከ5ኛ-4ኛው መቶ ክ.ዘ (ቅ.ክ.ል)

የሴት ምስል ሐውልት

ኖራ ድንጋይ፤ ቁ. 82 ሳሜ፤

ስ. 26 ሳ.ሜ፤ ወ. 80 ሳሜ

ሐውልቲ፣ ኮድ Je 1657





በሐውልቲ የተገኘው ሦስተኛው የመታሰቢያ ሐውልት በመጀመሪያ ዙፋን ተብሎ ይገለፅ ነበር። ከአንድ ወጥ ኖራ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሰራ፤ እንደቤት ዕቃ እግሮቹ በበሬ እግር አምሳል የተቀረፁ፣ ሳጥን መሰል ቅርጽ የተላበሰ ነው። ከእግሮቹ ቀጥሎ 1.4 ሜትር ቁመት ያላቸውና ቀጥ ብለው የተቀረፁ 3 ቋሚ ግድግዳዎች፤ ወረድ ብሎ ካለው አነስተኛ ጣራ ጋር በመገናኘት ዝግ ገፅታን ፈጥረዋል። በሶስቱም ግድግዳ በኩል ያጌጠ፣ ከፊት ባሉ ማዕዘናት ላይ ደግሞ፣ በትይዩ ያሉ የሜዳ ፍየል ቅርጾች፣ ከላይ ወደሚገኝ የህይወት ዛፍ በመገስገስ ሲገናኙ የሚያመለክት ትዕይንት ይዟል። በጎን ያሉት ግድግዳዎችም ታሪካዊ ጭብጥ እንዳለው የሚገመት ቅርጻ-ቅርጽ ይስተዋልባቸዋል። በአንደኛው ግድግዳ ምናልባት ታዋቂ የሆነ ረጅም ቁመናና ፂም ያለው፤ ከደረቱ ጋር የተያያዘ ጨርቅ ያገለደመ፣ በአንድ እጁ ማራገቢያ መሰል እቃ፣ በሌላኛው እጁ አናቱ ተለቅ ያለ ዘነዘና መሰል ዱላ ይዟል፤ ከጎኑም አነስተኛ ቁመት ያላት፣ መጎናፀፊያ መሰል ረጅም ልብስ የለበሰችና፣ በእጇም ረጅም በትር የያዘች ሴት ምስል ተቀርጾበታል። በተቃራኒው ጎንም፣ ከሴቷ ቅርጽ በላይ ከሚታይ ጽሑፍና በአጠገቧ ያለው ሰው ከያዘው ረጅም ና በውል ያልታወቀ ቁስ በስተቀር፣ ከሌላኛው ጎን ትዕይንት ጋር ተመሣሣይ ገጽታ አለው።

ይህን ቅርስ በተመለከተ፣ ቀልብን የሚስበው ጉዳይ፣ በስዕላዊው ጥበብና አቀራረፅ ስልቱ፣ በተለይም መሰል የሴት ገፅታን ከማሳየት አንጻር የደቡባዊውን አረብ የተለመደ ጥበብ ማሳየቱ፤ እንዲሁም የወንዱ ምስል ገፅታ ማሪብ በሚገኘው የአዋም መቅደስ ከታየው ሐውልት ቅርጽ ጋር ተመሣሣይ መሆኑ ነው። በእርግጥ የአባይ ሸለቆ ሀገራት ቅርጻ-ቅርጽ ጥበብም ሳይጠቀስ አይታለፍም። በተለይ በትግራይ የተገኙት የሜሮይ ሳህኖች፣ በሐውልቲ የተገኙት ጥቃቅን ነፍሳት መሰል ቅርጻ-ቅርጾችና የግብፃውያንን አማልክት ፕታህን የሚወክለው ቅርፅ፣ ለዚህ ማሳያ ናቸው።

ከጥቅሙ አንጻር ይህ ዙፋን የተቀረጸ አማልክት የሚቀመጥበት ሳጥን ወይም መቅደስ ሊሆን እንደሚችልና ምናልባትም አንድ ላይ ለተገኙችው ሴት ሐውልት መቀመጫ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። ሌላው በሴት አምሳል የተሰሩ ሐውልቶች በተለያዩ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ቅሪተ-አካል ስፍራዎች፣ በተለይም በመቅደሶችና፣ የተለያዩ ሥርዓቶች ሲከናወኑባቸው በነበሩ ቦታዎች መገኘታቸው፣ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የነበራቸው የላቀ ማህበራዊ ደረጃ፣ እስከ ምስለ-አማልክትነት የዘለቀ እንደነበር ለመገመት ያስችላል። በጠቅላላው ግን በእነዚህ ቅርጻ-ቅርጾች የተመለከቱት ሁኔታዎች፣ በአካባቢው ለነበሩ ባህላዊ እሴቶችና ማህበራዊ እምነቶች ነፀብራቅ እንደሆኑ መናገር ይቻላል። ■ [ተ. ሐ፣ ሉ. ዴ]

**የሐውልቲ የተቀረጸ ምስል 4**

ከ5ኛ-4ኛው መቶ ክ.ዘ (ቅ.ክ.ል)

ጉልላት

ኖራ ድንጋይ፤ ቁ. 140 ሳሜ፤

ስ. 67 ሳሜ፤ ወ. 57 ሳሜ

ሐውልቲ፣ ኮድ Je 1658

## የሜዳ ፍየል ቅርጽ-አዘል ገንቦ

ከሸክላ የተሰሩ ቁሶች የአንድን ማህበረሰብ እድገትና ለውጥ በቅጡ ለመረዳት ከሚሰጡት ጥቅም አንጻር በቅሪተ-አካል ጥናት ባለሞያዎች ዘንድ ተፈላጊ ናቸው። የሸክላ ሥራ ውጤቶች ከክርስቶስ ልደት በፊት 1ኛው ሺህ ዘመን ጋር ከመዛመዳቸው አንጻር፣ በዘርፉ ያለው ቅሪተ-አካል ጥናት በአብዝሃኛው ከኢትዮጵያ ሳባውያን ቦታዎች ከተገኙ መገልገያዎች ጋር ይገናኛል። እነዚህ የሸክላ ዕቃዎችም የዕደ ጥበብ ሽግግርና ቅብብሎሽ የተስተዋለባቸው ናቸው። ይህ ሂደት እ.ኤ.አ በ1960 ዓ.ም በየሃ በተደረገው ቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮ ወቅት በተገኘው ጥቁርና የተዋበ ገንቦ ላይ ተስተውሏል።

ይህ ቅሪተ-አካል ለፈሳሽ መያዣነት በአካባቢው የተመረተ ሲሆን፣ ባጠቃላይ መሰል ገንቦዎች ከታች ሰፋ ከአንገታቸው ደግሞ ጠበብ ብለው ይሰራሉ። በአክሱማውያን ዘመን ይሁን ከዛ በፊት እነዚህን ዕቃዎች የማግኘቱ እድል እጅግ ጠባብ ሲሆን፤ ይልቅስ አንገታቸው ሰፊ፣ አንድ ወይም ከዛ በላይ እጀታ ያላቸው ሸክላዎች ይዘወተሩ ነበር። ይህ አንፀባራቂና ጥቁር ሸክላ (ገንቦ) ይህን መሰል መልክ እንዲኖረው ያስቻለው በሚቃጠልበት ወቅት ያገኘው ጭስና በመጨረሻ ለማለስለስ የተጠቀሙት ቅባት ድምር ውጤት ሲሆን፣ ይህም በአፍሪካ ቀንድ የሚስተዋል የሸክላ ሥራ መገለጫ ነው።

ሸክላው ተጭረው በተቀቡ ጌጣጌጥ ምስሎች የተዋበ ነው። እርስ በርሳቸው በቋሚ መስመሮች የተያያዙ ሁለት ክብ መስመሮች፣ ሌሎች ሁለት ቀጥታ መስመሮች ከክብ መስመሮቹ እስከ አንገቱ ጫፍ፣ እንዲሁም ግማሽ ክብ ዐይነት መስመር ቅርጾች ከታች ወደ ክብ መስመሮቹ ተስለውበታል። የገንቦው ሆድ ላይ 3 ጥንድ የሜዳ ፍየል ቅርጾች ተቀርጸውበታል። ይህ የእንስሳት ቅርጽ በተለያዩ እቃዎች ላይ መታየት ያለውን እውነተኛ ትርጉም ለማወቅ ቢያዳግትም ከደቡብ አረቢያ የተወረሰ ባህል ለመሆኑ ግን ጥርጥር የለውም። መሰል ቅርጾች በታላቁ የሃ መቅደስ ግድግዳ፣ በሐወልቲ ዙፋን፣ እንዲሁም የማንነት ማረጋገጫ ንሃስ ቁሶች ላይ ተስተው ለዋል። ነገር ግን የዚህ እንስሳ በሸክላ እቃዎች ላይ ተቀርጾ የታየው በዚህ ገንቦ ብቻ ነው።

ከተዋበበት ጌጣጌጥ፣ ከአገልግሎቱና የእቃው ጥራት አንጻር ምናል ባትም ለአምልኮ ሥርዓት የተሰጠ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። የተገኘበት ሁኔታ ደግሞ ይህን ግምት ሊያጠናክር ይችላል። ሸክላው የተገኘው ከ2.8 እስከ 3.2 ሜትር ጥልቀት ባለው የመቃብር ጉድጓድ ከሌሎች ብዙ ሸክላዎች፣ የሸክላ ስብርባሪዎችና የሰው አፅሞች ጋር ነው። የብዙ ነገሮች መቀላቀልና መመሰቃቀል፣ እንዲሁም አንዳንድ የሸክላ ዕቃዎች በአፍ ተደፍተው መገኘታቸው፣ የመቃብር ጉድጓዱ በዘራፊዎች ጥቃት ሳይደርስበት እንዳልቀረ ያሳብቃል። አብዝኃኛው የቀብር ቦታዎች ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው ይገኛሉ፤ ከዚህ አንጻር ምናልባትም የተለየ የቀብር ሥነሥርዓትና መታሰቢያ የማድረግ ሁኔታ፣ እንዲሁም የሟች መገልገያ ንብረቶችን በልዩ ሐይማኖታዊ ደንብና ጸሎት በመቃብር የማስቀመጥ ባህል እንደነበረ ይታሰባል። በመቃብር ጉድጓድ እንደመባ የተቀመጡ ቅሪተ-አካላት፣ ስለ ሟችና፣ በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ስለተሰበሰበው ማህበረሰብ፣ የተወሰነ መረጃ ይሰጣሉ። ማህበ ረሰቡ የራሱ የሆነና ከደቡብ አረቢያ የተወረሰ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ያለውና ሁለቱንም የሚተገብር ሊሆን ይችላል። ■ [ሕ. በ]

**የሜዳ ፍየል ቅርጽ-አዘል ገንቦ 5**

ሸክላ፤ ቁ. 22.5 ሳሜ፤

ወ. 12.5 ሳሜ

የሃ፤ ቀብር 4፣ ኮድ JE 2132



## **አክሱም፤** በቀይ ባህር አካባቢ የነበረ የአፍሪካ አስተዳደር

የአክሱም ዘመን ፖለቲካዊ መዋቅር መነሻ ውልደትና፣ ቀደምት እድገት እስካሁን ግልፅ አይደለም። ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ የተነሱ ፃህፍት በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አክሱም የሚለውን የቦታ ስም የያዘ ጠንካራና ኃያል ሥርዎ መንግሥት፣ ግዛቱም ከትግራይ ከፍተኛ ቦታዎች እስከ ኤርትራ ባህር ዳርቻዎች የተዘረጋ እንደነበረ ፅፈዋል። የፐርሺያው ታሪክ አዋቂ ማኒም የአክሱም መንግሥትን ኃያልነት ከሮማውያን፣ ፐርሺያ እና ከቻይና ሥርዎ-መንግስታት ጎን ለጎን ጠቅሶታል። በወታደራዊ ዘመቻዎች አኳያ በጎረቤት ሀገሮች ግዛት የሚገኙ የሜሮ (ሱዳን) እንዲሁም የሂምያር (ደቡብ አረቢያ) ጎሳዎችን ማስገበርና መግዛት እንደ ቻለም ተጠቅሷል።

ንጉሥ፣ ማሊክ ወይም ባሲሊየስ የሚሉ መጠሪያዎች ቢጠቀሱም፤ የአክሱም ግዛት በአንድ ንጉሥ ለመተዳደሩ ጥርጣሬ አለ። ስለ አክሱም መንግሥት የሚጠቀስ የመጀመሪያ የግዕዝ ጽሑፍ በአዲ ገላም የሚገኝ ሲሆን እሱም በ200 ዓ.ም አካባቢ የተፃፈ ሲሆን በውስጡ፣ ግድር የአክሱም ንጉሥ የሚል መረጃ ያሳያል። ሌሎች ጽሑፎች ለጦር ነትና ለአክሱም ንጉሥ ግዛት አምላክ ለሆነው ማህሬም (በግሪክ አሬ) ለተባለው ጣኦት በተሰጠ ዙፋን ላይ ተገኝተዋል። በንጉሥ ኢዛና ዘመን 340 ዓ.ም. የንጉሳውያን ጽሑፎች ድምፀት ወደ ተላበሰ የግዕዝ ቋንቋ ማደግ የቻሉ ሲሆን አገልግሎታቸውም ለክር ስቶስ ክብርና አምልኮ እንዲውል ታስቦ ነበር። በንጉሥ ኢዛና ትክል ድንጋዮች ላይ በግሪክ፣ በሳባና ግዕዝ የተቀረፁ ጽሑፎች ንጉሱ የክር ስትናን እምነት እንደተቀበለ ሲያመለክቱ ቀስ በቀስም አክሱማውያን የክርስትና ሐይማኖት ተከታይ ለመሆን ችለዋል።

የአክሱም ዘመን ገዢዎች የመቃብር ቦታ አመላካች ትልልቅ ትክል ድንጋዮችን ብሎም ግዙፍ ቤተ-መንግስቶችን ለኃያልነታቸው ማሳያ አድርገው ሰርተዋል። በአካባቢው አንድና ጉልህ የሆነ ትክል ድንጋይን ከመሬት በታች ላለ የመቃብር ስፍራ አመላካችነት መጠቀም ከ3ኛ-4ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ እንደነበረ ተገምቷል። በትክል ድንጋዮቹ ላይ የሚስተዋሉት፣ ጌጣጌጦችና የአሰራር ጥበባት፣ ለሌሎች መታሰቢያዎች ደግሞ ምስልና ንድፍ ቀረጻ አገልግሎት ተጠቅመው ባቸዋል። የአክሱማውያንን ህንፃዎች ውብና ተወዳጅ ያደረጋቸው የጣውላ እና ድንጋይ ጥምር የሆነው ግንባታ ጥበብ ሊታወስ ይገባል፤ ይህ የጥበብ ባህል የተስተዋለባቸውና ማዕከላዊ በረንዳ ወይም ሰገነት ያላቸው ግዙፍ ህንፃዎች ቅሪት በአክሱምና መጠራ የተገኙ ሲሆን ቤተ-መንግሥት እንደነበሩ ጥርጥር የለውም።

የቅሪተ-አካል ጥናቶች፣ ስለ አክሱማውያን ስልጣኔ የሚያወሱት ምን ያህል ውስብስብና የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች ድምር እንደነበር ነው። የገዢዎች ማንነት በመጠለያቸው ወይም በመቃብር ስፍራ ዎቻቸው ሁኔታ ይገመታል። በከተሞች ብዛት ያላቸው መታሰቢያ ሐውልቶች፣ ሐይማኖታዊ ህንፃዎችና የልሂቃን ወይም ገዢዎች ግዙፍ አዳራሾች፣ ቤተ-መንግስቶች፣ እንዲሁም መጠነኛና ጥቀጥቀ ያሉ የመኖሪያ መንደሮች ይገኛሉ። በተመሳሳይ የገጠሩ ህዝብ አሰፋፈር የአርሶአደሩ ድጋፍ አስፈላጊ እንደነበር፤ ብሎም በእደ ጥበብ የጎለበቱ ባለሞያዎችም ሚናም ተመሳሳይ መሆኑን የሚጠቁሙ ቤተ-ሙከ ራዎች ይገኛሉ። ምንም እንኳን አክሱም የንጉሳዊው አስተዳደርና፣ የሐይማኖት ማዕከል ብትሆንም ሌሎች ጠቃሚ ከተሞች እንደነበሩ እርግጥ ነው። ለምሳሌ ወደ ቀይ ባህር በሚወስደው የሲራራ ንግድ መተላለፊያ ላይ የምትገኘው መጠራ ሁሌም ተጠቃሽ ናት።

ከጽሑፍ ማስረጃዎች በተጨማሪ፣ በአክሱም፣ መጠራና በቅርብ ጊዜ ደግሞ በዋካሪዳ የተከናወኑ ቅሪተ-አካል ጥናት ውጤቶች እንደሚ ጠቁሙት በህንድ ውቅያኖስና በሜድትራኒያን ባህር፣ ወይም በአፍ ሪካና አረብ ሀገራት፣ ይደረጉ ለነበሩ ረጅም የንግድ እንቅስቃሴዎች አክሱም ማዕከላዊ ጠቀሜታ ነበራት። የአክሱም ሲራራ ነጋዴዎች እንደ ባሪያ፣ ወርቅ፣ የዝሆን ጥርስና የዱር እንስሳትን በአዶሊስ ወደብ በኩል ሲያቀርቡ በምላሹ ከሮማውያን፣ አረቦችና ህንዶች ጌጣጌጦ ችንና ቅመማ ቅመምን ይገበዩ ነበር።

ከውጭ የሚገቡት ሳህኖች፣ የፈሳሽና ደረቅ ነገሮች መያዣ እንዲሁም አልባሳት፣ ተወዳጅና አድናቆት ይቸራቸው ነበር፤ ለዚህም ገዢዎችና ታዋቂ ግለሰቦች፣ ከዓለም አቀፍ ልሂቃን ጋር የፈጠሩት ጠንካራ



የዱንጉር ቤተ-መንግስት መወጣጫ ደረጃዎች፤ እ.ኤ.አ 1968 ዓ.ም

ግንኙነት፣ አስተዋጽኦ ሳይኖረው አልቀረም። ከውጭ ከሚገቡት ተፈላጊ ዕቃዎች በተጨማሪ በአክሱም የነበሩ የዕደ-ጥበብ ባለሞያዎች ከውስጥም ከውጭም በካበተው ጥበብ በመስታወት፣ በከበሩ ማዕድናት፣ በሸክላና በዝሆን ጥርስ የተለያዩ የቅንጦት ዕቃዎችን ያመርቱ ነበር።

ይህ ድንበር ዘለል ወይም ዓለም አቀፍ ግንኙነት ከ3ኛ-7ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት በተሻለ መንገድ አድጎ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ ስለነበር ለመገበያያ ገንዘብ መፈጠር ምክንያት ሆኗል። ይህም የተማከለና በቁጥጥር ሥር የሆነ እንቅስቃሴ ይኖር ዘንድ የገዢዎች ፍላጎት ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። በእርግጥ እንደ አሞሌ ጨው የመሳሰሉ ሌሎች የመገበያያ ዘዴዎች፣ ቀደም ሲልና በኋላም ከሳንቲሞች ጋር ጥቅም ላይ ይውሉ እንደነበር ይታሰባል። የአክሱም ሥርዎ-መንግሥት በ4ኛውና 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት መካከል በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ፣ ከዛ በኋላ እየተዳከመ እንደመጣ ሲወሳ፣ ለዚህም በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የእስልምና ሐይማኖት በአረብ ባህረ-ገብና በቀይ ባህር አካባቢዎች መስፋፋት ቁልፍ ሚና እንደተጫወተ ማሰብ አይከብድም።

ቀደምት ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት በ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የዳህላክ ደሴቶች በአረብ ሃይላት ከተያዙ በኋላ፣ የአክሱም የውጭ ንግድ እጅጉን ቀንሷል። በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ በኩል እንደ ቤጃ ባሉ የተገፉ ህዝቦች ውስጥ የተነሣ ግጭትና አመፅ ወይም በደቡብ በኩል የተነሣችው ንግስት በመንግስቱና ዋና ከተማይቱ ላይ የሰነዘረችው ጥቃት የመንግስቱ መዋቅር እንዲፈርስ ምክንያት ሁነዋል የሚል የሀሳብ ማስረጃ ይቀርባል። በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ የአረብ ሥነ-ምድርና ታሪክ ፀሐፍት አዳፋ ወይም ኩባር የሚባል አዲስ የስልጣን መቀመጫ እንደነበር ጠቅሰዋል።

የቅሪተ-አካል ጥናት መረጃዎች የአክሱማውያን ቦታዎች በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ እንደተተዉና ጥቅም አልባ እንደሆኑ ያመለክታሉ። የገንዘብ ህትመት ቆሟል፣ ከውጭ የሚገቡ ግብአቶች እጥረት ገጥሟል፣ ብሎም የመገልገያ ቁሳቁስ ባህል ለውጥ መጥቷል። የመቃብር ቦታዎች ተዘርፈዋል፣ አንዳንድ ትክል ድንጋዮችም ተገፍተው ሳይወድቁ አልቀረም። በጠቅላላው አዳዲስ የባህል ዐውዶች መታየት ጀምረዋል፤ ለምሳሌ የከተሜው ነዋሪ ህዝብ ሲቀንስ የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ በርክቷል፤ የተጎዱ ህንፃዎች በዕንጨት መዋቅሮች ተጠግነው በሌሎች ተወስደዋል። የዚህ ሁሉ ለውጥና ሽግግር ክሥተት መንስኤ አከራካሪ ቢሆንም፣ ከእስልምና መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመጣው የንግድ መቋረጥ፣ እና ተፈጥሯዊ ቀውሶች እንደ ምክንያት ሊቀመጡ ይችላሉ። ■ [ሉ.ዶ]



የዙፋን ታችኛው ክፍል፣ ሃፃኒ ዳኒኤል ከሚል የተቀረፀ ፅሁፍ ጋር፤ በ1950ዎቹ ዓመታት

## የአክሱም ሳንቲሞች
## ከ3ኛ-7ኛው መቶ ክ.ዘ

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ ፖርቱጋላዊ ተጓዥ በጉዞ ማስታወሻው ላይ የወርቅ ሳንቲም በአክሱም ማግኘቱን ጠቅሷል። ኀይለኛው የክረምት ወቅት ካለፈ በኋላ ሳንቲሞችን በየአመቱ በአክሱም አካባቢ እርሻ ማሳዎች ላይ ማግኘቱ የተለመደ ነው። ነገር ግን የታሪክ እውቀታችንን ሙሉ ለማድረግ ከቅሪተ-አካል ጥናት፣ ዓላማና መርህ ጋር ሲገኙ ለቁሳቁስና ቅሪተ-አካል ባለሞያዎች አስደሳች ይሆናል።

ሳንቲሞችን በመጠቀም ረገድ ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት የአክሱምን ሥርዎ መንግሥት የቀደመ የለም። ይህ የመገበያያ ገንዘብ ከዘመን ቀደም ተከተል ልኬት ጥቅሙ በተጨማሪ ስለ ማህበረሰቡ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና እምነት ታሪካዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። የአክሱም ሳንቲሞች ከ3ኛው እስከ 7ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ለ300 አመታት አገልግለዋል። ሳንቲሞች ጥቅም ላይ ይውሉ ዘንድ ቀደም ሲል የነበረው የንግድና ግብአት ልውውጥ ሂደት በደንብ የተስፋፋና የዳበረ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። ለዛ ደግሞ የሀገር ውስጡም ሆነ የውጪ ንግድ የዳበረና ለመንግስቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። የሮማውያንና የደቡብ ምዕራብ አረብ ሳንቲሞች ለአክሱም ሳንቲሞች መመረት ተሞክሮ ሳይሆኑ አይቀርም። ምክንያቱም የሮማውያን ክብደት መለኪያ (ሚዛን) በስፍራው ጥቅም ላይ ይውል ነበርና፣ ምናልባትም የአክሱማውያን ሳንቲሞች ከነሱ አንጻር የተቀረፁ እንደሆነ ይታሰባል።

በሳንቲሙ ፊተኛው ክፍል የንጉሱን ስዕላዊ ገፅታና መጀመሪያ በግሪክ ከዛም በግዕዝ የተፃፈውን ስሙን ይዟል። ጀርባው ድጋሜ የንጉሱን ወይም ሌላ ሰው ገፅታ፣ የስንዴ ዘለላና ሐይማኖታዊ ምልክት አለው። ጦር፣ ካባና ዘውድ፣ ኃያልነትን እንደ ግማሽ ጨረቃና በንጉሥ ኢዛና መንግሥት ደግሞ የነበሩ የመስቀል ቅርጾች የማህበረሰቡን (የግዛቱን) እምነት፣ ማሳያ ምልክቶች ናቸው። በሳንቲሞቹ ላይ የሚስተዋሉት ስሞች እንዲሰሩ ያዘዙትን ነገስታት ታሪካዊ ዝርዝር ለማየት ይጠቅማል። የመጀመሪያው ሳንቲም የተሰራው በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ በንጉሥ እንዱቢስ ሲሆን የመጨረሻው የአክሱም ሳንቲም ደግሞ በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በንጉሥ አርማህ ትዕዛዝ ነው። ዝርዝራቸውም እንዱቢስ፣ አፊላስ፣ ዋዜባ፣ ኦሳናስ፣ ኢዛና፣ ምህዲስ፣ ኦዜባዝ፣ ኤኦን፣ ኢባና፣ ነዛና/ነዙል፣ ኦሳስ፣ ኦሳናስ፣ ካሌብ፣ ኤላ አሚዳስ፣ ዋዜን፣ ኢዮኤል፣ ሐታዝ፣ እሥራኤል፣ ገርስም እና አርማህ ነው። ይህ የሳንቲሞች ስብስብ ከነዚህ በተጨማሪ ስም አልባ የሆኑትንና የትኞቹ ነገስታት እንዳሳተሟቸው መለየት ያልተቻሉትን ያካትታል። የቁሳቁስ ታሪክ ባለሞያዎች በነዚህ ሳንቲሞች ላይ ተመሥርተው የአክሱም ግዛት የዘመን ልኬትን በአጭሩ ለማስቀመጥ ሞክረዋል። ይህ የዘመን ልኬት ሳንቲሞች ከተፈጠሩ በኋላ የሚጀምር ከመሆኑ አንጻር ወደዛ ደረጃ እስከሚቃረብ ያለውን አስተዳደር ከግምት ውስጥ ያላስገባና ከመጨረሻው ሳንቲም ምርት በኋላ ያለውን ቀጣይነት ያላገናዘበ መሆኑ ሊሰመር ይገባል።

ለሳንቲሞቹ ምርት ግብአት 3 ዐይነት ማዕድናት፣ በመጀመሪያ ወርቅና ብር፣ በመቀጠልም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ሥርጭት ሲጨምር ነሐስ ጥቅም ላይ ውሏል። ሳንቲሞች ይመረቱ የነበረው በአክሱም ገንዘብ መስሪያ ቤቶች ውስጥ እንደሆነ ይታመናል። የአክሱም ሥርዎ-መንግሥት እየተዳከመ ሲመጣ (በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ) በገበያው ውስጥ የነበሩት ሳንቲሞች በይዘትም ሆነ በመጠን እያነሱና ተፈላጊነታቸው እየቀነሰ ሄዷል። በመጨረሻም በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ፣ ምናልባትም የገንዘቡ ግሽበት ለሳንቲም ምርት መቆም ምክንያት ሆኗል። ይህም የኪልዋ ሱልጣኔት በምሥራቅ አፍሪካ ተነስቶ ሳንቲም ማምረት እስከ ጀመረበት 9ኛ ወይም 10ኛው ክፍል ዘመን ድረስ ዘልቋል። ■ [አ. ታ]

**የአክሱም ሳንቲሞች** 6

ከ3ኛ-7ኛው መቶ ክ.ዘ

- ■ እንዱቢስ (270-300 ዓ.ም)፤ ብር፤ ወርድ 15-16 ሚሜ
- ■ ኢዛና (320-360 ዓ.ም)፤ የወርቃማ ሳንቲም ቅጂ፤ ወርድ 17 ሚሜ
- ■ አርማህ (600-630 ዓ.ም)፤ መዳብ ቅይጥ፤ ወርድ 17 ሚሜ






# የአክሱማውያን ባለ ሦስት እግር ማሰሮ
## 2ኛ-4ኛው መቶ ክ.ዘ

በአክሱማውያን ባህልና ኑሮ ውስጥ የሸክላ ውጤቶች የዕለት ከዕለት ጠቀሜታና በሁሉም የህይወት አውድ ውስጥ ስፍራ የነበራቸው ግብዓቶች ነበሩ። ዕለት ከዕለት ብዙና ጠንካራ ቁስ ከሚያስፈልገው የምግብ ማብሰያ ስፍራ፣ እስከ ገዢዎች ቤተ-መንግሥትና መቃብር ድረስ፣ ውብና ጥራት ያላቸው የሸክላ ውጤቶች የፍላጎት ጎራ እንደነበሩ መገንዘብ ተችሏል። አብዛኃኛው የሸክላ ውጤቶች ባለ መቀመጫና እጀታ፣ ጎድጓዳ ሳህን ዐይነት ቅርጽ ያላቸው፣ ወይም ከአንገታቸው ቀጠን ከታች ደግሞ ክብና ሰፊ የሆኑ ማሰሮ መሰል ቢሆኑም፤ የአክሱማውያን የሸክላ ውጤቶች ስብስብ ከነዚህ በዘለለ የተለያዩ ቅርጽ ያላቸውና ልዩ የሆኑ መገልገያ ሸክላዎችን ያመርቱ እንደነበር ያስረዳል።

ይህ በምስሉ ላይ የሚታየው ባለ ሦስት እግር ጎድጓዳ ሳህን እ.ኤ.አ በ1958ዓ.ም ከአክሱም የሁለት ሰዓት እርቀት ደቡብ ምዕራብ፣ ባናደር አውራጃ፣ ኩሂ በተባለ ቦታ በግንባታ ወቅት ከሌሎች ሸክላ ሣህኖች ጋር የተገኘ የሸክላ እቃ ነው። በስፍራው ክዳን መሰልና ትክል ድንጋይ መኖሩ፣ ምናልባት ከመቃብር ስፍራ የተነሣ ይሆናል የሚል ግምት አለ። ከሶስቱ አንዱ እግር ከጊዜ በኋላ ጥገና ተደርጎለታል፤ ሶስቱም ወደፊት ወጣ ያሉና የሰው እግር ቅርጽ ያላቸው ናቸው። ሁለት እጀታ፣ እነሱም ጠንካራ እንዲሆኑ፣ ብሎም ጥሩ ገፅታን እንዲላበሱ ከዋናው ክፍል ጋር በደንብ እንደተያያዙ የሚጠቁም አሻራ አላቸው። መሀል ለመሀል በመስመር የተለዩ (የሴት) ጡት መሰል ጌጦች ተሰርቶባቸዋል። የዚህ ሸክላ የላይኛው ክፍል እስከ አንገቱ፣ ያልተገኘ ከመሆኑ አንጻር ትክክለኛ ቅርፁንና አገልግሎቱን መረዳት አልተቻለም።

በአክሱም በሚገኘው የዮዲት ጉዲት ትክል ድንጋይ ቦታ በተካሄደ የቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮ ተመሳሳይ ሦስት እግር፣ ተጨማሪ አጭር አንገትና ክዳን፣ ያለው ሸክላ ሳህን መቃብር ውስጥ ተገኝቷል። ሌሎች መሰል የሸክላ ውጤቶች በአክሱምና መጠራ የተገኙ ሲሆን፣ የግኝታቸው አውድ ግን ግልፅ ስላልነበረ፣ እነዚህን መሰል ሸክላዎች ከቀብር ሥነ-ሥርዓት ጋር የተገናኘ አገልግሎት ነበራቸው፤ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አልተቻለም። በሌላ በኩል ከእጀታና አንገታቸው አንጻር ለአገልግሎት የተሰሩ ቢመስልም፣ ለጌጥ ወይም ለፈሳሽ ነገር ማቅረቢያ፣ ያገለግሉ ነበር ብሎ እንኳን ለመናገር የሚያስችል መረጃ አልተገኘም። በቅርጻቸውም እጅግ የተለያዩ ሲሆኑ አንዳንዶች የወፍ ቅርፅ፣ ሌሎች ደግሞ የሰው ፊት ገፅና፣ ክብ አንገት ቅርጽ አላቸው። እነዚህ ሰውና እንስሳት መሰል ቅርፀት የተላበሱ የሸክላ ውጤቶች በአክሱም ዘመን ከ2ኛው እስከ 4ኛው ሺህ ዓመታት ማብቂያ የነበሩ ናቸው።

በአንድ በኩል የአክሱማውያን ሸክላ ጥበብ ወጥና ቀጣይነት የተላበሰ እንደሆነ ሲታይ የቅርብ ጊዜያት ጥናቶች ግን በየአካባቢው የተለያየ አሰራር ባህል እንደነበረ ያሳያሉ፤ ለምሳሌም እንደ መጠራ፣ አክሱም፣ ዋካሪዳ፣ አዶሊስ ያሉ አካባቢዎችን በመጥቀስ። የአክሱማውያን ሸክላ ውጤቶች በበቂ ሁኔታ እሳት (ሙቀት) ያገኙ ናቸው፤ ምናልባትም ከሮማውያን ወይም ሜዲትራንያን አካባቢ በወሰዱት ልምድ የግድግዳ ሸክላም ያመርቱ እንደነበርና ለአዳዲስ የአሰራር ዘዴዎችም በራቸው ክፍት እንደነበር መናገር ይቻላል። እንደ አምፎራ፣ አብለጭላጭ ሰማያዊ፣ እንዲሁም የአፍሪካ ቀይ ቅብ ሸክላ እቃዎች (ቴራሲጊሳታ)፣ የመሳሰሉት በእርግጠኛነት በአክሱም የባህልና ንግድ ልውውጥ ሂደት ውስጥ ገናና ነበሩ።እናም የኋለኛው የነሀስ ሳህኖችን በማስመሰል የተሰራና፣ ከቀዩ ቅብ ሸክላ በተጨማሪ ሌሎች አማራጮችን (ዐይነቶችን) ከማስፋት ፍላጎት የመነጨ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል።

በጠቅላላው ባለ ሦስት እግሩ ሸክላ፣ ሳህኑና ማሰሮው የአክሱም አስተዳደር ጠቢባንን የፈጠራ ብቃትና ክህሎት ከማሳየት አልፎ ብርቱና ሁሉን አቀፍ ግዛት እንደነበር ማስረጃ ነው። ■ [ሕ. በ፣ ሉ.ዬ]

**የአክሱማውያን ሸክላዎች** 7

ባለ ሦስት እግር ማሰሮ

2ኛ-4ኛው መቶ ክ.ዘ

ሸክላ፤ ቁ. 21.5 ሳሜ፤

ወ. 19 ሳሜ

ኩሂ፣ ኮድ JE 502





## የአደን ተምሳሌት መቅረዝ
## ከ2ኛ-3ኛው መቶ ክ.ዘ

ከመጠራ የተገኘው ይህ መቅረዝ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ወቅት ከውጭ ለሚገቡ የቅንጦት እቃዎች ድንቅ ምስክር ነው።

ከመዳብ ቅይጥ የተሰራው ይህ የአቮካዶ ቅርጽ የተላበሰ ጎድጓዳ መቅረዝ፣ በአንድ በኩል የባህር እንስሳ ቅርፊት የሚመስል፣ በሌላ በኩል የገዢዎችን አደን ችሎታ የሚገልጽ እጀታ ያለውና፣ ባጠቃላይ የተለያዩ ጉዳዮችን ወይም ትዕይንቶችን መግለጽ የሚችሉ ቅርጻ-ቅርጾች የተላበሰ ነው። ከጀርባው የበሬ ራስ ቅልና፣ ወደ እጀታው የሄደ ፍርግርግ ገጽታ፣ ያለው ሲሆን ከእፅዋቶች መስከ የተነሣ መልክዓ-ምድራዊ ገፅታን የሚያመለክት ይመስላል። ከዛ ቀጥሎ፣ አዳኝ ውሻ የሜዳ ፍየልን ኋላ እግር ጡንቻ ነክሶ እንደያዘ ያመለክታል። ክፍተት ያለው ፀጥር መሰል ፍርግርግ ለመቅረዙ መቀመጫነት ተሰርቶለታል። ይህ ልዩ ጥበብ የፈሰሰበት መቅረዝ እንደሌሎች የነሐስ መቅረዞች ተንጠልጣይ ላለመሆኑ ማረጋገጫ፤ ቀለበቶች የሉትም። ምናልባትም ከመጠኑና ክብደቱ አንጻር ማንጠልጠሉ ከባድ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

መቅረዙ በደቡብ አረቢያ ጥቅም ላይ ይውሉ ከነበሩ የሜዳ ፍየል ቅርጽ ያላቸው መቅረዞች ጋር ሊነፃፀር ይችላል። በአብዝሃኛው የቅርብ ምሥራቅ ሀገራት ጥበብ ሞዴል ከሆነው አካሜኒድ ጋር የተዛመደ ነው። ይህን መሰል መቅረዞች ከክርስቶስ ልደት በፊት 5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ እስከ 3ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ባሉ ጊዜያት እንደነበሩ ይታወቃል። ይህ መቅረዝ ግን ከፈረንሳዩ ሉቭርና ከእንግሊዝ ብሔራዊ ሙዚየም ናሙናዎች ጋር ሲነፃፀር ከ2ኛ-3ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ባሉ ጊዜያት እንደተመረተ ተገምቷል።

መጠኑም ሆነ የአሰራሩ ጥበብ ይህ መቅረዝ ሌሎች ከሚታወቁ ቀደምት መቅረዞች የተለየ፣ የእቃው ክብርና የላቀ ባህሪም ጎልቶ ሊታይ በሚችል ደረጃ የተነደፈ ነው። ልዩ ክህሎት የነበራቸው ጠቢባን እንዳበጁትም መረዳት አይከብድም። በጥንታዊ የአክሱም ቅሪተ-አካል ስፍራዎች የተገኙ የወርቅ ጌጣጌጥ፣ የተዋቡ ሳህኖች፣ ከነሐስ የተሰሩ የአበባ ማስቀመጫዎች፣ አንፀባራቂ የፋርስ ሸክላ ዕቃዎች፣ የተለያየ ቀለም የተላበሱ መስታወት ጾቃዎች፣ እንዲሁም በተለያዩ ትዕይንቶች ያጌጡ ከዝሆን ጥርስ የተሰሩ ጌጣጌጥና ዕቃዎች ሌላ ተጠቃሽ ግኝቶች ናቸው። በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጭ የገቡ ይሁን፤ የአክሱም ሥርዎ-መንግሥትን ብልፅግና፣ ብሎም ነገሥታቱ ከሜዲትራ ንያንና ህንድ ውቅያኖስ አካባቢ ባህል ጋር የነበራቸውን ቁርኝት እንድ ንገነዘብ ያስችለናል።

የዚህ መቅረዝ ግኝት አውድ እስካሁን ያልተፈታ እንቆቅልሽ ነው። እ.ኤ.አ በ1965 በመጠራ በተደረገ የቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮ የተገኘ መንደር ውስጥ በፀጥር የተከበበ ምናልባትም የመሪዎች ሊሆን በሚችል ህንፃና አዳራሽ ቅጥር ይህ መቅረዝ ሊገኝ ችሏል በቅጥሩ ከጊዜ በኋላ ሌሎች አገልግሎታቸው ያልታወቀ ክፍሎች እንደ ተጨመሩ የተስተዋለ ሲሆን ባልተለመደ መልኩ ከቋሚዎች ውጭ ግድግዳው በጡብ የተሰራ ክፍል ነበር። ይህ መቅረዝ በዚህ ክፍል በነበረ ፍልፍል ድንጋይ ውስጥ ተገኘ። የዚህ ክፍል አገልግሎት ምን ነበር? የመቅረዙስ ጥቅም በተገኘበት አውድ ነበር? ወይስ ለመደበቅ ወይም ከዝርፊያ ለመከላከል ተብሎ ተቀመጠ የሚሉ ጥያቄዎች እስካሁን ምላሽ አላገኙም። ምናልባት የተዘረፈ፣ ከሌሎች ነገስታት በስጦታ የተበረከተ፣ ወይም በተወደዱ ዕቃዎች ንግድ ልውውጥ ወቅት የተገኘ? የሆነው ሆኖ የዚህ መቅረዝ ምንጭ፣ ደቡባዊው የአረብ ክፍል ለመሆኑ ከፍተኛ ግምት አለ። ይህም ለዘመናት የዘለቀና የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ዘመን ማብቂያ ድረስ በቀይ ባህር በኩል የነበረ የሁለቱ ክልሎች ግንኙነት እውነተኛ ማሳያ ነው። ■ [ሉ.ዬ]

**የአደን ተምሳሌት መቅረዝ 8**


ከ2ኛ-3ኛው መቶ ክ.ዘ

መዳብ ቅይጥ፤ ቁ. 41 ሳሜ፤ ስ. 39 ሳሜ፤

ወ. 14.5 ሳሜ፤ ክብደት 7.5 ኪግ

መጠራ፤ ኮድ JE 3439





የመጠራ (በኤርትራ የሚገኝ ቦታ) መቅረዝ ግኝት ዓውድ፣ እ.ኤ.አ 1964 ዓ.ም

# የመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያ፤

## በእምነትና ንግድ

## መንታ መንገዶች ላይ

**በኢትዮጵያ «መካከለኛው ዘመን»** ተብሎ የሚጠራው ከአክሱም ሥርዎ-መንግሥት ውድቀት እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ያለውና መቀመጫውን በሐረር አድርጎ የነበረው ሱልጣኔት ከሰሜናዊው የክርስቲያን መንግሥት ጋር ያደረገውን የጦርነት ወቅት ይጨምራል። በዚህ ረጅም ና ወደ አሥር ክፍለ ዘመናትን ባካተተ ጊዜ ውስጥ የዛሬዋን ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ጂቡቲና ሶማሌላንድን ባጠቃለለ ሰፊ መልከዐ-ምድራዊ ክፍል የክርስትና፣ እስልምናና ከነዚህ በተቃራኒ እምነት የነበራቸው ህዝቦች በአንድነት ይኖሩ ነበር። ይህ የሐይማኖት ብዝኀነት የተለያየ ፖለቲካዊ አደረጃጀትና አስተዳደር እንዲኖር አድር ገዋል። ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የኦሮሞ ኃይል በመነሳቱ በሙስሊም ሱልጣኔትና በክርስቲያን መንግሥት ተይዘው የነበሩ የተወሰኑ አካባቢዎችን ሲቆጣጠር፣ ለተለያዩ የፖለቲካ ሃይላት መልሶ መቋቋምና መጠናከር ምክንያት ሆኗል።

ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ጠንካራ የክርስቲያን መንግሥት የነበ ረበት ጊዜ ሲሆን በመጀመሪያ በዛግዌ (11ኛ-13ኛ መቶ ክፍለ ዘመናት) ኋላም በሰለሞናዊው ሥርዎ-መንግሥት የበላይነት ሰፊ ግዛትን በመቆ ጣጠር ይገዛ ነበር። በተጨማሪ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይህ መንግሥት ኃያል የነበረበትና አብዛኃኛውን የአፍሪካ ቀንድ ከፍታማ ቦታዎች በስሩ ያደረገበት ወቅት እንደነበር ይወሳል። ይሁንና የእስልምና ሐይማኖት ተከታዮችና ከሁለቱ ሐይማኖቶች ውጪ የሆኑ ህዝቦችም በመንግስቱ ግዛት መሐልና ዳርቻ በጋራ ይኖሩ ነበር። ከዚህ በዘለለ ክርስቲያኑ ህዝብ ከሚኖርበት በምዕራብና ደቡብ በኩል የነበሩ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢዎች ሐይማኖት አልባ በሆኑ ህዝቦች ቁጥጥር ሥር ነበሩ። ከ13ኛ-14ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ከነበረው የዳሞት ሥርዎ-መንግሥት ውጪ ሌሎቹ ሐይማኖት አልባ ህዝቦች፣ በጽሑፍ የሚገኝ ማስረጃ አልተገኘላቸውም። በሌላ በኩል ከፊል ደቡብና ምሥራቁ እስከ ኤደን ባህረ-ሰላጤ በሙስሊም ሱልጣኔት እነሱም የሸዋ ሱልጣኔት (ከ12ኛ-13ኛ መቶ ክፍለ ዘመናት)፣ የኢፋት ሱልጣኔት (ከ13ኛ-14ኛ መቶ ክፍለ ዘመናት)፣ የአዳል ሱልጣኔት (ከ15ኛ-16ኛ መቶ ክፍለ ዘመናት) ግዛት ሥር ቆይተዋል።

በጽሑፍ ታሪክና በአርኪኦሎጂ መረጃዎች መካከል ያለው የነዚህ ማህበረሰቦች ታሪክ የተለያየ ነው። እስከ ቅርብ ጊዜያት ያሉ የአፍሪካ ቀንድ መካከለኛው ዘመን የጽሑፍ ታሪኮች በአብዝሃኛው በክርስ ቲያኑ መንግሥት ተፅዕኖ ውስጥ እንደነበሩ መናገር ይቻላል። ይህ ደግሞ የክርስቲያኑ መንግሥት እንደ አሌክሳንድርያ፣ እየሩሳሌምና ሮም ካሉ ሀገራት ጋር የነበረው ግንኙነትና፣ ከዛም በላይ የግዕዝ ቋንቋ ዕድገት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስና አብዝኃኛው ታሪክ በቋንቋው ሊፃፍና በአብያተ-ክርስቲያናትና ገዳማት ሊጠበቅ መቻሉ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል። በተቃራኒው በሙስሊሙ ማህበረሰብ ጥቂት የመቃብርና የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ሲስተዋሉ፤ ሐይማኖት አልባ የነበረው ማህበረሰብ ጭራሽ ምንም ዐይነት የጽሑፍ ባህል ያልነ በረውና በሌሎችም ጽሑፎች ያን ያህል ያልተጠቀሰ ነበር። የፅህፈት ቋንቋ አለመመጣጠን እንዲሁ የክልሉን ታሪክ ግንዛቤ ተመጣጣኝ እንዳይሆን አድርጎታል ማለት ይቻላል።

ባለፋት ሃያ አመታት በሙስሊም ሱልጣኔት (ይፋት፣ ሃርላና ሶማሊ ላንድ)፣ እንዲሁም በድንጋይ ዘመን ማህበረሰብ ቅሪት (ጨርጨርና የስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች) የተደረጉ የአርኪኦሎጂ ጥናቶች ሚዛናዊና የተሻለ የታሪክ መረጃ ማሳየት ችለዋል። በዚህም እነዚህ ህዝቦች በጣም የተደራጁና በጠንካራ መንግሥት ግዛት ሥር እንደ ነበሩ፣ በከተሞችም ይኖሩና በሲራራ ንግድ ተሳትፎ እንደነበራቸው መገንዘብ ተችሏል።

እንደ ሸክላ፣ የባህር እንስሳት ቅርፊት፣ የሰጎን እንቁላል ቅርፊቶች፣ የመስታወት ዶቃዎች የመሳሰሉ ቅሪተ-አካላት የነዚህን ህዝቦች ባህልና ኢኮኖሚ ብሎም በቀይ ባህርና በሙስሊሙ ዓለም መካከል የነበራቸውን ንግድ ልውውጥና ተሳትፎ ማስረጃ ናቸው። በእርግጥ የነበራቸው ሚና ከሌሎች ጋር ተመጣጣኝ ላይሆን ይችላል። አልባሳት፣ የኢንዶ-ፓስፊክ ዶቃዎች፣ የቻይና ሸክላ ዕቃዎችንና መሰል ሸቀጦችን የማጓጓዙ ሥራ የሙስሊሙ ሱልጣኔት ሲሆን ከዛም ከክርስቲያኑ መንግሥት ወይም ሌሎች ህዝቦች ጋር በመገበያየት በምላሹ ወርቅ፣ የዝሆን ጥርስና ባርያ ይወስዱ ነበር። ከዚህ አንጻር በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከናወን ቅሪተ-አካል ጥናት ከነጠላ ቤተ-ክርስ ቲያን መገንት በዘለለ የህንፃውን አሰራርና የማስዋብ ጥበብ ከግምት ያስገባ መሆን የጥንቱን ማህበረሰብ በተሻለ ለመረዳት እንደሚያስችል ይታመናል። በተያያዘ ሌሎች የባላባት መኖሪያዎች፣ ቀደምት ሰፈራ አካባቢዎችና የቀብር ስፍራዎች ማህበረሰቡን ለመረዳት ጠቃሚ

ግብአቶች ናቸው። እንደ ቅሪተ-አካል ጥናት መረጃ፣ በተሐድሶ ላይ የነበረው የመካከለኛው ዘመን ታሪክ፣ ከጽሑፍ ምንጮች በዘለለ በውስብስብና በብዙ መረጃዎች ትዕይንት የተሞላ እንደነበር መናገር ይቻላል። የባህልና ሐይማኖት ብዝኀነትን በጋራ እሴቶች አዋህዶ ከ7ኛ-16ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ይኖር የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ከሌላው ዓለም ጋር የነበረው ግንኙነት የዚሁ ነፀብራቅ ለመሆኑ ጥርጥር የለም። ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የነበረው ጦርነት ግን የተለየ ፖለቲካዊና ማህበረሰባዊ ባህል ብሎም ሐይማኖት ተኮር መልክዓ-ምድር እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል።

ከቁሳዊ ባህል አንጻር፣ በ16ኛና 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት መካከል ባለው ጊዜ የሚያጠነጥኑና በተለያዩ ዘርፎች የተደረጉ ጥናቶች አንድ ወጥ አልነበሩም። በአንድ በኩል በዋነኛነት የሙስሊሙ ማህበረሰብ የተቀደሰ ቦታ ለመሆን የበቃችው ሐረር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዋና መቀመጫውን ወደ ጣና ሐይቅ አካባቢ ያዛወረው የክርስቲያኑ መንግሥት የወቅቱ የትኩረት አቀጣጫዎች ነበሩ። በ17ኛውና 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ጎንደር የክርስቲያኑ መንግሥት መቀመጫ ሆናለች። ብዛት ያላቸው ህንፃዎች በተለይም የነገስታቱን መቀመጫ ቤተ መንግሥትና ቤተ-ክርስቲያን ያጣመሩ ግንባታዎች በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በጣና ሐይቅ ዙሪያ ባሉ አካባቢዎች ተመሥርተው ነበር። ይህ ወቅት በኢትዮጵያና ፖርቱጋል መካከል የነበረውን ግንኙነት የሚያሳብቅና አዲስ የግንባታ ጥበብና ንድፍ የተስተዋለበትም ነበር። ሆኖም እነዚህ ታሪካዊ ክንውኖችና ቅሪቶች በቁጥር ከመታወቅ በዘለለ በቂ ክትትልና ጥናት አልተደረገባቸውም። ከነዚህ ውስጥ በቅሪተ-አካል ጥናት ሽፋን ያገኘው ከአፄ ሱሱኒዮስ መኖሪያና ቤተ-መንግሥት አጠገብ አዘዞ የሚገኘው የእየሱሳውያን ህንፃ ብቻ ነው። ■ [አ. ሼ፣ ማ.ሎ. ዴ]

# አብያተ-ክርስቲያናት

ከአክሱም ሥርዎ-መንግሥት ውድቀት (7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን) መባቻ ጀምሮ የአብያተ-ክርስቲያናት ግንባታ እንደቀጠለና በኢትዮጵያ ከፍታ ቦታዎች እንደተስፋፋ ይታወቃል። የቀደምት መንግስታት ቁሳዊ ባህል በቤተ-መንግስታቸው፣ በመቅደሶች፣ በአብያተ-ክርስቲያናትና በመቃብር ቦታዎች እንደተቀመጠና እንደተገኘ ሁሉ የክርስቲያኑ መንግሥትና ህዝብ ቁሳዊ ሀብት ደግሞ በአብያተ-ክርስቲያናት ተጠብቋል። ይህ ምናልባትም በ8ኛውና 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መካከል ለተገነቡና ለተመሰረቱ አብያተ-ክርስቲያናትና ገዳማት ዐይነተኛ ምክንያት ሆኖ ሊታሰብ ይችላል። በመካከለኛውና ደቡብ ኢትዮጵያ የአብያተ-ክርስቲያናት መተከልና መስፋፋት በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተከናወነ ነው።

በዚህም እ.ኤ.አ ከ1270 ዓ.ም ጀምሮ የተነሣው የሰለሞናዊው ሥርዎ-መንግሥት ከክርስቲያኑ ግዛት ጋር የሚጣጣም ገዳማትን በመፍጠር ረገድ አዲስ ምዕራፍ ይዞ መጥቷል። ይህ የአብያተ-ክርስቲያናትና ገዳማት ጥምረት ክርስትና በሌሎች አዳዲስ ግዛቶች እንዲስፋፋና እንዲጎለብት ለቀጣዮቹ መቶ አመታት መሰረት ሆኗል። ከገዳማት በተጨማሪ የነገስታቱ አብያተ-ክርስቲያናትም በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እድገት ያሳዩ ሲሆን የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊ ቅርስ ከመጠበቅ አንጻርም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። የአብያተ-ክርስቲያናቱ ገንዘብ ድጋፍ ከንጉሳውያን ግምጃና የግላቸው ልገሳ የመነጨ መሆኑም ይወሳል።

በመካከለኛው ዘመን የነበሩ የኢትዮጵያ አብያተ-ክርስቲያናት ታሪክ የተለያየ መልክ አላቸው። የቅሪተ-አካል ጥናት ይደረግባቸውም አይደረግባቸው አንዳንዶቹ በነበር ያሉ ቅሪቶች ናቸው፤ ለምሳሌም በአሸንጌ ሐይቅ ዳርቻ የሚገኘው የሚፍሳስ ባህሪ ቤተ-ክርስቲያንና ከመቀሌ በስተደቡብ የሚገኘውን የማርያም ናዝሬት ቤተክርስቲያን ቅሪቶች መጥቀስ ይቻላል። በሌላ በኩል እስካሁን የዘለቁና አገልግሎት የሚሰጡ በዋሻዎች ውስጥ የተቆረቆሩ እንደ ይምርሐነ ክርስቶስና እመኪና መድሃኒዓለም ብሎም የላስታ አካባቢ ውቅር አብያተ-ክርስቲያናት ተጠቃሽ ሲሆኑ በዘመናት የከፋ ለውጥና፣ ጥቃት ያልተ

ስተዋለባቸው ናቸው። ከዚህ አንጻር የገርዓልታ ሸለቆና የላሊበላ አብያተ-ክርስቲያናት የዘመን ተሻጋሪ ተቋም ተምሳሌት ተደርገው ይቆጠራሉ። ከአንድና ከፊል አንድ ቋጥኝ የተቆረቆሩ አብያተ-ክርስቲያናት በሰሜን ኢትዮጵያ የሚበዙ ቢሆንም በደቡብ ምዕራብ ወሎ የወለቃ እንዲሁም በጉራጌ አካባቢ የአዳዲ ማርያም አብያተ-ክርስቲያናት በሌላው የአገሪቱ ክፍል ከሚገኙት ጥቂት ምሳሌዎች ውስጥ ይጠቀሳሉ። በተመሳሳይ በሸዋ የአርሲ ዮሐንስ ቤተ-ክርስቲያን በዋሻ ከተቆረቆሩት ውስጥ ተጠቃሽ ምሳሌ ነው።

የተገነቡና ከቋጥኝ የተቆረቆሩ አብያተ-ክርስቲያናት አሰራር ጥበብ የተለያየ ቢሆንም ምድባቸው አንድ ነው። የእነዚህ አብያተ-ክርስቲያናት አሰራር በአብዝሃኛው አራት ማዕዘን ሲሆን በጣም ጥቂቶች መስቀል ቅርጽ ንድፍ በመያዝ ይታወቃሉ። በኢትዮጵያ በአሁን ወቅት በብዛት የሚስተዋሉት ክብ ቅርጽ ያላቸው አብያተ-ክርስቲያናት ዐይነት እስከ ፲6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ያልተስ ተዋለና የወቅቱ ምህንድስና ጥበብ ከአክሱም ሥነ-ህንፃ ጥበብ ጋር በእጅጉ የተዛመደ ነበር።

የዕንጨትና ድንጋይ ስብጥር የግንባታ ዘዴና ቋሚዎች ላይ ዝንጀሮ-መሰል ቅርጽ ማዋሃድ አንዱ ተጠቃሽ ምሳሌ ነው። በተጨማሪ ከአንድ ወጥ ድንጋይ የተቀረፁ ምሰሶዎች ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር። በሌላ በኩል ከ፲፲ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በመቅደስ ውስጥ ግማሽ ክብና ሞላላ ዐይነት ጉልላት ጥበብ የተስተዋለ ሲሆን ይህም ቀደምት የነበረውን አሰራር የማሻሻልና የማዘመን እርምጃ ተደርጎ ተወስዷል። ከአክሱም ሥነ-ህንፃ ጥበብ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ በድንጋይ ወይም ዕንጨት ክፍሎች ላይ እንደ መስኮትና ዘንባባ መሰል ቅርጾችን መሥራት አልፎም ማራኪ ቅርጾችና ንድፍ ማካተት ሌላው ተዛማጅ አሰራር ነው።

የመካከለኛው ዘመን ነገስታት አብያተ-ክርስቲያናትን የመገንባትና የገንዘብ ድጋፍ የማድረግ ባህል የነበራቸው ከመሆኑ አኳያ እያንዳንዱ ንጉሥ ቢያንስ አንድ ቤተ-ክርስቲያን እንዲገነባና እንዲተክል ምክንያት ሆኗል። ለምሳሌም በላስታ አውራጃ በአፄ ይኩኑ-አምላክ የታነፀው ገነተ-ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ሲጠቀስ፤ በቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ ላይ ባለው ስዕል ግርጌ የተፃፈው መረጃም ንጉሱ ከሁለቱ አማካሪዎቹ ጋር እንደሆነ በመግለጽ እውነታውን ያጠናክራል። በመካከለኛው ኢትዮጵያም መሰል ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን በነገስታቱ ከሚታነፁ አብያተ-ክርስቲያናት ውስጥ አንዳቸው የግል የመቃብር ቦታም እንዲሆኑ የማድረግ ባህል ነበር። ከዚህ በዘለለ እነዚህን የንጉሳውያን ቤተ-ክርስቲያናት የዋና ከተሞች አመላካች ወይም መሸጋገሪያ እንዲሁም ለክብረ-በአላትና (እንደ ፋሲካ፣ መስቀል፣ ዘመን መለወጫና የድል ባዕላት ላሉት) አመታዊ የሐይማኖትና ሌሎች ጉባኤዎች ማስፈፀሚያ በመሆን ያገለግሉ ነበር።

እነዚህ አስደናቂ የንጉሳውያን አብያተ-ክርስቲያናት በመካከለኛው ዘመን በነበሩ የግዛት ወሰኖች በተለይም በአማራ አካባቢዎች በብዛት ይገኛሉ። አትሮንሳ ማርያም፣ ደብረ-ብርሃን፣ መርጦ ለሚካኤልና አፀደ ሚካኤል በሰሜኑ ሲጠቀሱ የነዚህ አብያተ-ክርስቲያናትን ህንፃ አሰራር ዘዴ የተጠቀሙ ሌሎች አብያተ-ክርስቲያናት በዳዋሮ (አሩሲ) ብሎም በጋሞ ጎፋ አካባቢዎች ተስተውለዋል። ሌሎች ሁለት ቅሪት አብያተ-ክርስቲያናት (ቴዎድሮስ ግንብ በመባል የሚታወቁ የረር ተራራና እንስላሌ አጠገብ) እ.ኤ.አ በ፲970ዎቹ በቁፋሮ ተገኝተዋል። እነዚህ ቅሪተ አብያተ-ክርስቲያናት ውብና ተገጣጣሚ በሆኑ የድንጋይ ሥራዎች የታነፁ ሲሆን ጥቂት የግንባታ ናሙናዎች በብሔራዊ ሙዚየም ይገኛሉ። የንጉሳውያን አብያተ-ክርስቲያናት በልዩ የግንባታ ጥበብ የታነፁና በተለያዩ ቅርጾች፣ ማለትም የተጠ ላለፉ መስመሮች፣ ዚግዛግ ቅስቶች፣ ቀስት መሳይ ቅርጾች፣ አበባ መሰል ገፅታዎች፣ የተቆላለፉና መስቀል መሰል ቅርጾች፣ ውበት የተላበሰ አሰራር ነበራቸው።

አብያተ-ክርስቲያናትና ገዳማት የምስሎች፣ የግድግዳ ስዕሎች፣ የሐይ ማኖታዊ ሥርዓት ቁሶች፣ ብሎም ጥንታዊ የብራና መፃህፍት ማዕከል ከመሆናቸው አንጻር የነገሥታቱንና የነዋሪውን ህዝብ ታሪክ ለመሰነድ እጅግ ጠቃሚ ማዕከላት ናቸው። ጥንታዊ ከሆኑትና ከታወቁት አብያተ-ክርስቲያናትና ገዳማት መሐል የሐይቅ እስጢፋኖስ ቤተ-ክርስቲያን እና ገዳም ተጠቃሽ ነው። ይህ ገዳም በ፲3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተደረገ ቆጠራ ከ85 በላይ በጣም ተፈላጊና ጥንታዊ የብራና መፃህ ፍትን ጠብቆ ማቆየት የቻለ ሲሆን እስካሁንም በገዳሙ መሥራች



የሚካኤል አምባ ውቅር ቤተ–ክርስቲያን መግቢያ፤ የቅርብ ጊዜ ፎቶ



በጉንዳ ጉንዴ የሚገኝ ቤተ-ክርስቲያን፤ በ1950ዎቹ ዓመታት

አቡነ እየሱስ ሞአ ከተበረከቱ ወንጌላት በተጨማሪ የንጉሳውያን ስጦታዎችም ተጠብቀው ይገኛሉ። በሌላ በኩል በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአንዳንድ መነኮሳት አነስተኛ አርማ መሰል ምስሎችና የጸሎት ጥቅሎችን የመሥራት ጥበብ እንደዳበረ መረዳት ተችሏል። ለምሳሌ ከገውግወበን ገዳም ፈረ–ፂዮን የተባለው ሰዓሊ ስም በደጋ እስጢፋኖስና ሬማ መድሃኒዓለም በሚገኙ ምስሎች ላይ ተጠቅሶ የሚገኝ ሲሆን እኒህን መሰል ቅሪቶች አሁንም በክርስቲያኑ መንግሥት ግዛት የነበሩ የባህልና ሐይማኖት ትውፊቶችን ለማጥናት የመረጃ ምንጭነታቸው ከፍተኛ ነው። ■ [ማ.ሎ. ዴ፣ ደ. አ]


## የአዋጅ መስቀል

ይህ የብረት መስቀልና ዘንግ አንድ ወጥ ሆኖ የተሰራ፣ ከረጅሙ ዘንግ ወደ ጫፍ አጠር ያለ አግዳሚ እጄታ (መስቀል) የተሰራበት በጫፉ ላይም ክብ ወይም ግማሽ ክብ የሆነ ቅርጽ የተሰራለት ነው። በመሰል መስቀሎች ላይ ከሚስተዋሉ ጌጦች አንጻር ምናልባት ቀደም ሲል በስሱ የተቀረፁ ጌጦች የነበሩት ሳይሆን አይቀርም፤ ሆኖም በዕድሜና ዝገት ምክንያት የተበላሸ እንደመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። የግኝቱ ዓውድ መረጃ የጠፋ፣ ከ1973 ዓ.ም በፊት በነበሩ ጊዜያት መች ወደ ሙዚየም እንደገባ መረጃ አልተገኘለትም፤ ምናልባትም ከመሬት ወለል በታች ተቀብሮ ሳይገኝ እንዳልቀረ ይታሰባል።

በተጨማሪ ምንም ዐይነት ሳይንሳዊ ጥናት ስላልተደረገበት ስለብረቱ ቅንብር፣ መገኛ፣ አሰራር ወይም ሥርጭት በቂ መረጃ የለም። በአብዝሃኛው ግን ጥንታዊ የመስቀል ዐይነት እንደነበረ ይነገራል።

ከ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ባሉት ጊዜያት ረጅም ዘንግ ያላቸው መስቀሎች በአክሱም መንግሥት ሳንቲሞች ላይ ተስለዋል። በሌላ በኩል በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በገነተ ማርያም ቤተ–ክርስቲያን በተሳሉ ስዕሎች ላይ መሰል መስቀል ተስተውሏል። 15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከቀላል እስከ ውስብስብ ቅርጾች ያላቸውና በአብዝሃኛው ከመዳብ ቅይጥ የተሰሩ የመስቀል ዐይነቶችን ይዞ ከመምጣቱ እንዲሁም አንዳንዶች የለጋሹን ግለሰብ ስም ስለሚይዙ ዕድሜያቸውን ማወቁ አዳጋች አልነበረም። ከዚህ አንጻር የዚህ መስቀል ዕድሜ ከዚህ ወቅት በፊት እንደነበረ መገመት ይቻላል።

ረጅም ዘንግ ያላቸው መስቀሎች ለተለየ ሥርዓትና አገልግሎት አልፎ አልፎ የሚስተዋሉ እንደሆኑ ባለንበት ዘመንም በዋናነት በቀሳውስትና መነኮሳት እጅ የሚያዙና በንግስ ወይም በወንጌል ንባብ ወቅት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይነገራል። ■ [C.B.-T.]



በረድፍ የተተከሉ የዓዋጅ መስቀሎች፤ በኡራ መስቀል፣ ጊዜው ያልታወቀ ፎቶ





**የአዋጅ መስቀል** 9

ብረት፤ ቁ. 144 ሳሜ፤ ስ. 14.5 ሳሜ

ያልታወቀ ቦታና ጊዜ

## የቤተ-ክርስቲያን ካስማ
### ከ8ኛ-12ኛው መቶ ክ.ዘ?

የግማሽ ክብ ቅርጽ ያለው፣ ከአንድ ወጥ ዕንጨት የተቀረጸና በውብ ጌጥ የተሞላ ነው። የግሪካውያን ጠበብት ወጣ ገባ ያሉ ከፊል ክብ ቅርጽ ያላቸው ጣራዎችንና መግቢያ በሮችን እጅግ ያደንቃሉ። በተለይም እርስ በርስ ተሰካኪ የሚመስሉ የመስቀል ቅርጽ ንድፎች ሲታከሉበት ውብ ነው። ይህ ቅሪተ-አካል ከየሃ ጥንታዊ ቤተ-ክርስ ቲያን የመጣ ሲሆን ይህ ቤተ-ክርስቲያን አሁን ለቅዱስ አፍፀ (እንዳ አባ አፍፀ) መታሰቢያነት የተሰጠ ነው።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በመጀመሪያው ሺህ አመት ይህ ቦታ ምናል ባትም የደቡብ አረቢያ ደአማት ሥርዎ-መንግሥት መናገሻ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክርስትና መስፋፋት ጋር ተያይዞ አብያተ-ክርስቲያናት በቀደምት ቅሪት የአል ማቃህ ቤተ ጣኦታት ላይ ይገነቡ እንደነበረ ሲገመት፣ ከቀደምት ቅሪት ውስጥ የመጠመቂያው ገንዳ ብቻ በዚህ ቤተ-ክርስቲያን ይገኛል። ቤተ ክርስቲያኑ የተለያዩ ለውጦችን ያስተናገደ ከመሆኑ አንጻር በአንድ ጎን በአክሱም ዘመን ከ4ኛ-7ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት እንደ ተገነባ በሌላ በኩል ግን ግንባታው ከ12ኛ-13ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል።

እ.ኤ.አ በ1520ዎቹ፣ በንጉሥ አፄ ልብነ ድንግል ዘመን (1508-1540 ዓ.ም) የፖርቱጋል ኤምባሲ ቄስ፣ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ በቅርብ እርቀት ሌላ ቤተ-ክርስቲያን መገንባቱንና ይህም ቤተ-ክር ስቲያን በተመሳሳይ ብዙ ጊዜ የቅርፅና ይዘት ለውጥ እንደተደረገበት ጠቁሟል። እ.ኤ.አ 1906 ዓ.ም በጀርመን-አክሱም ጥናት ተልዕኮ ቡድን በተወሰደ ፎቶግራፍ በመስኮቱ ላይ ተመሳሳይ የዕንጨት ካስማ የተስተዋለ ሲሆን በአሁን ሰዓት በብሔራዊ ሙዚየም ካለው ናሙና ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖም በመሀል ያሉ ቅርጾች ላይ ልዩነት ያለው ነበር። ከዚህ አንጻር እነዚህ ካስማ ቅስቶች ከመጀመሪያው መቅደስ ወደ ኋለኛው ቤተ-ክርስቲያን ከዘም በአቅራቢያ ለተገነባው ዳግም ጥቅም ላይ ዋሉ የሚያስብል መላምት እንዲነሳ ምክንያት ሆነዋል።

የደብረ ዳሞ፣ የአራሞ፣ እንዲሁም የሚካኤል አምባ አብያተ-ክርስቲያናት ይህን መሰል ዕንጨት ካስማ ይዘው ከሚገኙ ህንፃዎች ተጠቃሽ ናቸው። ብቸኛው ልዩነት መሐል ላይ ያሉት የክብ ነገሮች ቅርጽ በደብረ-ዳሞ ያለመኖር ነው። ስለሆነም መሰል የዕንጨት ሥራዎች በጥንታዊ አብያተ-ክርስቲያናት መገኘት የዚህን ካስማ ዕድሜ ግምት ከ8ኛ-12ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ያደር ገዋል። ትናንሽ አብያተ-ክርስቲያናት ውስጥ መሰል ቅርጽ ቢስተ ዋልም ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን መግቢያ በር ብቻ የተወሰነ ነበር። በትላ ልቆቹ አብያተ-ክርስቲያናት በግልፅ በሚታይ ሁኔታና ብዛት ሲስተዋሉ በሚካኤል አምባ ቤተ-ክርስቲያን ባለ ሁለት መዝጊያ አንድ በር አናት ላይ ሁለት መሰል ቅርጾች ይገኛሉ።

እ.ኤ.አ 1949 ዓ.ም የየሃ ቤተ-ክርስቲያን ዳግም ግንባታ ሲደረ ግለት ብዙ የዕንጨት ምሰሶዎችና ካስማዎች ተወግደዋል። ከ5 ዓመታት በኋላ በጆን ለክላንትና ጆን ዶርሴ በስፍራው የዳሰሳ ጥናት የተደረገ ሲሆን ቦታውን በተመለከተ የቅሪተ-አካል ስብስብ በሙዚየም መኖር እንዳለበትና ስለአተገባበሩ በአቶ ከበደ ሚካኤልና ጆን ለክላንት አማካ ኝነት በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ጥናት ማዕከል ዓመታዊ መፅሐፍ ላይ ተገልጿል።

የጥናት ባለሞያዎቹም ለሙዚየም ስብስብ የሚመጥን የዕንጨት ካስማ በመምረጥ ወደ ተቋሙ ግምጃ ቤት እንዲገባ አድርገዋል። ይህ ካስማ (የዕንጨት ቅስት) ከዓመታት በኋላ እ.ኤ.አ 2022 ዓ.ም ወደ ቋሚ ዓውደ-ርዕይ በመምጣት ለተመልካች በመቅረቡ ይህ አነስተኛ ገለፃ ሊፃፍ ቻለ። ■ [ክ. ቦ.ቴ]

**የቤተ-ክርስቲያን ካስማ** 10

ከ8ኛ-12ኛው መቶ ክ.ዘ?

ዕንጨት፤ ቁ. 70 ሳሜ፣ ስ. 149 ሳሜ፣ ርዝ. 30 ሳሜ

የሃ፣ ኮድ Je 16





## የዕጣን ማጨሻዎች
## ከ13ኛ-16ኛው መቶ ክ.ዘ

እጣን ከሀገር ውስጥና ውጭ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጋር የተቆራኘ ጠቃሚ የሀብት ምንጭ ሲሆን ከጥንት ጀምሮ በቀይ ባህር፣ ሜድትራ ንያንና ህንድ ውቅያኖስ አካባቢ ሲደረግ ለነበረው የንግድ ልውውጥ አንዱ ግብዓት ነው። ነጭ ዕጣንና ከርቤ በዋነኘነት ለውጪው ንግድ ሲቀርቡ ባለመዓዛ እፅዋትና ሙጫ ለአካባቢ ገበያ ይውሉ ነበር። ለሙታን መስዋዕት ዕጣን የማቅረብ ልማድ ሐይማኖት በሌለውም ሆነ በክርስቲያኑና በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ የነበረ ሁኔታ ነው። ሆኖም የእጣን ማጨሻን ከሙታን ጋር በመቃብር ማስቀመጡ ያልተለመደ ከመሆኑ አንጻር በመንዝ ከፍታማ ስፍራ አምባ ገብርኤል ተብሎ በሚታወቅ ቦታ በተደረገ ቅሪተ አካል ጥናት የተገኙት እነዚህ እጣን ማጨሻዎች ሆን ተብለው በመቃብር አካባቢ ለመቀመጣቸው እርግጠኛ መሆን አልተቻለም። ምን አልባት በቀብር ሥነ-ሥርዓት ወቅት በቦታው ተትተው የነበሩ እንደሆነ ይገመታል።

በአምባ ገብርኤል የተገኙት ዕጣን ማጨሻዎች በዐይነት ሦስት ሲሆኑ አንዳቸውም ጌጥ አልነበራቸውም። የመጀመሪያው ወፍራምና ቀጥ ያለ ጠርዝ ያለው የተቃጠለ ሳህን ይመስላል። ሁለታኛው ከላይና ታች ክብ፣ መሃሉ ሞላላና የገበታ ቅርጽ ያለው አሰራሩ ወፍራምና ወጣ ገባ ያለ ከመሆኑ አንጻር ለውበቱ ቦታ ያልተሰጠው ሥራ ነው ማለት ይቻላል። ሶስተኛው ከሁለተኛው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የአበባ ማስቀመጫ መሰል ቅርጽ አለው። ሁሉም ማጨሻዎች ከታች የተሰበሩ፤ ከአሰራር አንጻር ሁለቱ ከመጀመሪያው ጋር በአንድ ሰው ተሰሩ ብሎ ለመናገር የማያስ ደፍሩ ናቸው። ምክንያቱም የመጀመሪያው ልምድ ባለው የሸክላ ሰሪ እጅ እንደተሰራ መገመት ይቻላል። ሌላው በጥያቄ መልክ ሊነሱ የሚችሉና መልስ የሚሹ ጉዳዮች፤ በማጨሻዎቹ ላይ ተጣብቆ የሚስተዋለው የዕጣን ወይም ሌላ ነገር ቅሪት ግብዓት፣ ፈሳሽ ነበረ? ከሥርስ ለማቃጠል ኩራዝ ወይስ ሌላ ነገር ጥቅም ላይ ዋለ? የሚሉ ናቸው።

እጣን ማጨስ፤ በአምባ ገብርኤል በነበሩ የተለያዩ ዘመናት የመን ደሮች ምስረታ ሂደት ውስጥ የነበረ ልማድ መሆኑ ተስተውሏል። ትክል ድንጋዮች ከመቃብር ቦታ አመላካችነት ጋር በሚቀመጡበትና ከክርስትና በፊት ከ13ኛ-14ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት፣ የመጀመሪ ያዎቹ ሁለት ዐይነት እጣን ማጨሻዎች ጥቅም ላይ ይውሉ እንደነበር በአካባቢው በተደረገ ጥናት ከተገኙት የሸክላ ቁሳቁሶችም አንድ አስረ ኛውን ብዛት እንደሚሸፍኑ ተረጋግጧል።

በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከታነፀውና በውስጡም አምስት የመቃብር ቦታዎችን ያካተተው የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያንን ተከትሎ ሶስተኛው ዐይነት እጣን ማጨሻ ሥራ ላይ እንደዋለ ይታሰባል። በዚህ ወቅት እጣን ማጨሻዎችን መጠቀሙ የጨመረ ይመስላል። ከዛም በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በመቶዎች የሚቆጠሩ የመቃብር ስፍራዎች በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ መሰራት ሲጀምሩ ሁኔታው ወደ አመፅ እንደተለወጠና ቤተ ክርስቲያኑ ጭምር በእሳት የመቃጠል ዕጣ እንደገጠመው ይገመታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ እጣን ማጨሻዎች ቁጥር እጅጉን ቀንሶ ተስተውሏል። ይህ ሁኔታ እንግዲህ ቀደም ሲል በሐይ ማኖት አልባ ህዝብ ውስጥ የነበረው የእጣን መስዋዕት ባህል በክርስ ቲያኑም ቀጥሎ እንደነበር ማሳያ ለመሆኑ አመላካች ነው።

ከዕጣን ማጨሻዎቹ አንዱ የተቆረጠና ሾጣጣ ቅርጽ ያለው ሲሆን ምናል ባትም የአንድ ትልቅ ጣባ ወይም ገበቴ መሳይ ሸክላ ስባሪ ሳይሆን አይቀርም። ይህ ዕቃ በአራት ማዕዘን ቅርጽ በተሰራና በቤተ ክርስቲያኑ ህንፃ ውስጥ ከሚገኝ የመቃብር ቦታ የተገኘ ለየት ያሉ ጌጦች ያሉት፣ ከውጭ ከገቡ ቅሪት ቁሶች ጋር ባንድነት የነበረ ነው። ጌጦቹ ከ10ኛው-14ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ይኖሩ ከነበሩ የድንጋይ ጠበብት ማህበረሰቦች ሥራ ጋር የሚመሳሰልና ከሌሎቹ ቅሪቶች በተቃራኒ ሀገር በቀል ዕውቀትን የሚያመለክት ነበር። ■ [አ.ሊ. ጉ፣ ማ.ሎ. ዬ]

**የዕጣን ማጨሻዎች** II

ከ13ኛ-16ኛው መቶ ክ.ዘ ሸክላ፤ ወ.

■ ቁ. 6 ሳሜ፤ ወ. 10.5 ሳሜ፤ ኮድ 8023.9

■ ቁ. 6 ሳሜ. 10.5 ሳሜ፤ ኮድ 8049.1

ገብርኤል



## የኢትዮጵያ ሱልጣኔቶች

የኢትዮጵያና የሙስሊሞች ግንኙነት ከእስልምና ሐይማኖት መነሻ ጊዜ ጋር ይጀምራል። እ.ኤ.አ በ615 ዓ.ም (የመጀመሪያው ሂጅራ) የነብዩ ሙሐመድ (ሱ.ዐ.ወ) ተከታዮች በአክሱም ጥገኝነት እንደ ተሰጣቸው በሙስሊሙ ወግ ይጠቀሳል። ይህ ጊዜ ማለት ደግሞ ከመዲና ሂጅራ ሰባት ዓመት ይቀድማል። በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን ተጨማሪና በቂ ማስረጃ ባይገኝም የመቃብር አመላካች ድንጋይ ላይ የተመለከቱ የአረብኛ ጽሑፎች ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ864 ዓ.ም ገደማ በኤርትራ ዳህላክ ደሴቶች፣ ከዛም በቢለት (ትግራይ) አካባቢ እ.ኤ.አ በ972 ዓ.ም ገደማ እንደተቀረፁ የታሰቡ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እንደሚጠቁሙት የሙስሊሙ ማህበረሰብ ከ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአካባቢው ኑሮውን እንደመሰረተ ማስረ ጃዎች ናቸው። በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች ግን ከ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ እስከ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ባሉ አመታት እንደተስፋፋ የቅሪተ-አካል ጥናት ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። በይፋት የሚገኘው የኖራ መስጂድ ቅሪት እንደሚያሳየው የመጀመሪያው ህንፃ ጅማሮ ይህን ወቅት ሲያሳይ በሌላ በኩል ድሬዳዋ አካባቢ የሚገኘው የሃርላ ቅሪተ-አካል ስፍራም በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ የሙስሊሙ ማህበረሰብ መገልገያ እንደነበረ መረዳት ተችሏል።

ያሉት የጽሑፍ መረጃዎች ጥቂት ቢሆኑም እነዚህ ቦታዎች በኢትዮጵያ መካከለኛው ዘመን ታሪክ ውስጥ ከተለያዩ የሙስሊም ሱልጣናትና ከሌሎች ግዛቶች ጋር የተቆራኘ አሻራ ያላቸው እንደነበር ይታወቃል። በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በምሥራቅ ኢትዮጵያ የሚገኙ ክልልሎች ወይም ከተሞች ተብለው የተጠቀሱ እንደ ሸዋህ፣ ጂዳያህና ካልድጂር የመሳሰሉ ስፍራዎች በአንድ የአረብ ጽሑፍና በየመን ሰነድ ውስጥ የተገኙ ቢሆንም ምናልባት ኋላ ላይ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በይፋት ሱልጣኔት የተዋጡ ሳይሆኑ እንዳልቀረ ይገመታል። ከዛ በኋላ ባሉ ጊዜያት የሙስሊሙ መረጃ እየተጠናከረ የመጣበት እንቅስቃሴ ተስተውሏል። የካይሮው ፀሐፊ ኢብን ፋድል አሏህ አል ኡማሪ በተለይም ይፋትን ከሰባቱ የሙስሊም አካባቢዎች (ይፋት፣ ዳዋሮ፣ አረባብኒ፣ ሻርካ፣ ባሊ፣ ዳራህ፣ እና ሃድያ) አንዱ እንደሆነና በክርስቲያኑ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚገኝ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ፅፏል። በይፋት ያሉ ኖራ እና ፋቂ ዳቢስ የተባሉ ቦታዎች ላይ የቅሪተ-አካል ጥናት የተከናወነ ሲሆን ምናልባትም ከዋነኛ ከተሞች ውስጥ ተጠቃሽ እንደሆኑ ይታሰባል። በሌላ በኩል የቅሪተ-አካል ጥናት ማዕከል የሆነው ሌላው አካባቢ፣ ሃርላ፣ የይፋት (ሃርላ ሱልጣኔትን) ዋና መናገሻ ስፍራ እንደሆነና ሁባት ወይም ሀባት የሚል ቀደምት መጠሪያ እንደነበረው ይገመታል። ከዛ በዘለለ ስለሌሎቹ አካባቢዎችና አጠቃላይ ስለ ሱልጣናቱ አደረጃጀት፣ ደንብ እንዲሁም የባህል ሁኔታ ያለው ዕውቀት እጅጉን ውስን ነው።

በዘመኑ የነበረው ተዛማጅ ሀገር በቀል መረጃ አናሳ መሆን፤ ስለ ሙስሊሙ ሱልጣኔት ብዙ ለመናገር ባያስደፍርም በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውም፣ ሆነ በማህበራዊው ዘርፍ በክርስቲያኑና በሙስሊሙ ኃይል መካከል የነበረው ግንኙነት ከጥቂት ግጭቶች በስተቀር በብዙ መደጋገፍ የሚገለጽ ነው። የ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ የተለያዩ ግዛታዊ ይዞታ ለውጦች የተስተዋሉበትና አብዝሃኛው የሙስሊሙ አካባቢ፣ ይፋትን ጨምሮ በክርስቲያኑ መንግሥት መተዳደር የጀመ ረበት ወቅት ነው። ይህ ሁኔታ ለክርስቲያኑ መንግሥት ከመገበር በዘለለ በሙስሊሙ መስፋፋትና ይዞታ ላይ ያመጣው ተፅዕኖ አልነ በረም። በኋላ ላይ ከምሥራቃዊ ስምጥ ሸለቆ ከፍታዎች አንስቶ እስከ ዘይላ ወደብ (ኤደን ባህረ-ሰላጤ) ያለውን አካባቢ ያዋሰነ ኀይለኛ ሱልጣኔት እንደተነሳና፤ በክርስቲያኑ የግዕዝ ጽሑፎች አዳል በሙስሊሙ የአረቢኛ ሰነዶች ደግሞ ባር ሳዐድ አድ-ዲን የሚል መጠሪያ እንደነበረው ለማወቅ ተችሏል፤ መቀመጫውም ዳካር የሚባል ቦታ እንደሆነ ቢገለጽም የዚህን ቦታ ትክክለኛ መገኛ እስካሁን ማመላከት አልተቻለም። ከ1520 ዓ.ም ጀምሮ ግን ሐረር የሱል ጣኔቱ ዋና መናገሻ እንደሆነችና ኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚም (በተለምዶ አጠራር ግራኝ) ከዚችው ከተማ በመነሳት በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ጦር እንዳዘመተ የፋትህ አል-ሀበሻ መረጃ ይጠቁማል። ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ የሱል ጣናቱ ግዛትና ኃይል እየተዳከመ መጥቶ በመጨረሻም የመካከ ለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሱልጣኔት ታሪክ ሊጠፋ ችሏል።

የመካከለኛው ዘመን ሲራራ ንግድ ኢትዮጵያን ከአረብ ሰርጥ፣ ግብፅና ህንድ ውቅያኖስ ጋር በቀይ ባህር በኩል የሚያገናኛት ቁልፍ እንቅስቃሴ ሲሆን ይህም እንቅስቃሴ በሙስሊሙ ማህበረሰብ አማካኝነት ይተገበር

ነበር። በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተፃፈ የየመን የንግድ መመሪያ እንደሚያትተው ይህ የንግድ ልውውጥ በብርና ነሐስ ሳንቲሞች ወይም በብረት መርፌዎች የሚከናወን እንደሆነ በምላሹ ደግሞ ወርቅ፣ ጥርኝ፣ አልባሳት ወይም ጃንደረባዎችን መውሰድ እንደሚቻል ያስረግጣል። በሌላ በኩል እንደ ኢብን ፋድል አሏህ አል ኡማሪ ዘገባ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቀንድ ከብቶችና አዝዕርት ለገበያ ልውውጥ ይውሉ እንደነበር ነገር ግን በሌሎች አምስት የሙስሊም አካባቢዎች ማለትም፣ በይፋት የወርቅና ብር ሳንቲሞች፣ በዳዋሮ፣ አራባኒ፣ ሻርካና ሃዲያ አካባቢዎች ደግሞ ሃኩና ተብሎ የሚታወቅ የሳንቲም ዐይነት (የብረት መርፌ) ለመገበያያ ይጠቀሙ እንደነበር ገልጿል። በተጨማሪ ገንዳቤሎ በሚባል ይፋት ውስጥ በነበረ ቦታ ከፍተኛ የገበያ ልውውጥ እንደነበረና ብዛት ያላቸው ግመሎች እንዲሁም የሲራራ ነጋዴዎችን ከተለያዩ የህንድ የቤት ቁሳቁሶች ጋር እንደተመለከተ አንድ ቬኒሳዊ ተጓዥ እ.ኤ.አ በ1523 ዓ.ም በማስታወሻው አስፍሯል። በወቅቱ መገበያያ ገንዘቦች የሙር (የግብፅ) የብር ሳንቲም ወይም ድርሃም እንደነበር በመጠቆም ከተማዋን ታላቅ የነጋዴዎች ማዕከል ሲል ገልጿታል። በ19ኛው እና 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት አፈታሪክ ገንዳቤሎ «የዓለም ገበያ» እየተባለች ትወሳለች። በዚህ አቅጣጫና ዓውድ የተገኙ ቅሪቶች አናሳ ከመሆን አንጻር የቅሪተ-አካል ጥናት ባለሞያዎች የታሪክ መልሶ ምስረታ ሂደት ላይ ገና ብዙ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል። የድንጋይና መስታወት ጨሌዎች ከህንድ ወደ መሀል ኢትዮጵያ ይመጡ የነበሩ ሲሆን ውብና ጠንካራ የሸክላ ውጤቶች ደግሞ ከግብፅ፣ የመንና ቻይና በመግባት በመንደሮች ይሸጡ ነበር። በሀገር ውስጥ የሸክላ፣ የብረት፣ እና አልባሳት ምርት በየገበያዎቹ ይስተዋሉ የነበሩ ሲሆን የብርና ነሐስ ሳንቲሞች ለመገበያያነት ከዛም አልፎ ለጌጣጌጥ መስሪያነት አገልግሎት ነበራቸው። ■ [አ. ሼ፣ ቲ. ኢ.]



በኖራ፣ መስጂድ ውስጥ የተደረገ ስነ-ቅርስ ቁፋሮ፤ እ.ኤ.አ 2008 ዓ.ም


## አረቢኛ ጽሑፍ አዘል የመቃብር ላይ ድንጋይ 10ኛው መቶ ክ.ዘ

ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ በምሥራቅ ትግራይ (ጨርቆስ ኪውሃ) አካባቢ ጥንታዊ የሙስሊም መቃብር አመላካች የነበሩና የአረብኛ ፊደላትን የያዙ ድንጋዮች ተገኝተዋል። የመጀመ ሪያው መረጃ በእንግሊዛዊው ተጓዥ ናታኒኤል ፒርስ የተጠቆመ ነው። ያጌጡ የመቃብር ቦታዎችን መመስረት ወይም መገንባት ሐይማ ኖታዊ ክልከላ ቢኖረውም ትክል ድንጋዮችን ለመታሰቢያ ማስቀመጥ በሙስሊሙ ማህበረሰብ የተለመደ ነበር። በቢለት (ትግራይ) መቃብር አካባቢ በሚገኙ ባዛልት (ጥቁር ድንጋይ) ወይም አሸዋማ ድንጋይ ላይ የተቀረፁ ወይም ያለ ቅርጽ የተዘጋጁ ድንጋዮች በመቃብር አንደኛ ጫፍ ወይም ሁለት ጫፎች ላይ የቦታው አመላካችና መሰረት ይሆኑ ዘንድ ይተከሉ ነበር። በቅርብ ጊዜ በዚህ አካባቢ በተደረጉ የቅሪተ-አካል ጥናት ቁፋሮዎች ከቀደሙት በተለየ መልኩ ከትናንሽ የድንጋይ ንጣፎች የተሰሩ ባለአራት ማዕዘን የመቃብር አመላካች ቅርጾች ተገኝተዋል። በአንድ የመቃብር ስፍራ ቀደምት ጽሑፍ ያለበት ትክል ድንጋይ በራስጌ በኩል ጽሑፉ ወደ ውጭ ሆኖ የተገኘ ሲሆን፣ በርካታ የመቃብር ቦታዎች ግን ምንም ዐይነት ትክል ድንጋዮች አልነበራቸውም። ምናልባትም መሰል መታሰቢያ ድንጋዮች ለታዋቂ ቤተሰብ ወይም ግለሰቦች መታሰቢያነት ብቻ ሳይውሉ አልቀረም። በእርግጥ በቢለት የተገኙ የመቃብር ትክል ድንጋዮች በጥንታዊ ስፍራቸው ሳይሆን ከስፍራቸው ለቀው የመቃብር አናት አካባቢ፣ የመስክ ጠርዞችን ለመለየት በሚመስል መልኩ ተተክለው የተገኙ ናቸው። አንድና ብቸኛ ቀደምት ስፍራውን ይዞ የሚገኝ ድንጋይ በጨርቆስ ቤተክርስቲያን መቅደስ ውስጥ ይገኛል። የአረብ ቀብር ላይ ሐውልቶችንና ከ40 በላይ ቅሪት ቁሳቁሶችን የተመለከተ ታሪክ ከማስመዝገብ አንጻር የቢለት መቃብር ስፍራ በኢትዮጵያ ቀዳሚው ነው። ቦታውም በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሂጅራ ወይም 11ኛው ክ.ዘ ጥቅም ላይ ይውል እንደነበር የዕድሜው ልኬት ያስረዳል።

በአውደ ርዕዩ የቀረበው የመቃብር ላይ ድንጋይ በቢለት ከተገኙ ቀደምት ቅሪቶች አንዱ ሲሆን፤ በተዋበ የኩፊክ አፃፃፍ ዘዬ የተቀ ረጸና እንደ ሌሎቹ ጌጣጌጥና ባለ 6 ቀስት ኮከብ የሌለው ነው። ጽሑፉ በዱልቃዳ 9/396 (ነሐሴ 7/1006 ዓ.ም) ያረፈች ካሳሙዋ የተባለች የኢብራሒም ልጅ፣ ኢብራሒምም የኒዛር ልጅ፣ ኒዛርም የሐፍስ ልጅ፣ ሐፍስም የዑመር አል ያማሚ ልጅ በሚል የሚያስረዳ የአንዲት እንስት መታሰቢያ ሲሆን በዚህ ስፍራ የተገኙ ትክል ድንጋዮች አርባ በመቶው ከሴቶች የመቃብር ቦታ ጋር የተገናኙ መሆናቸው ታውቋል። ካሳሙዋ የሚለው ቃል ከአካባቢ ማህበረሰብ ስም ጋር ተዛማጅነት ያለው ቢሆንም ከአባት ጀምሮ ያሉት 4 የትውልድ ዘር ሀረጓ ግን ከአረብ ይመዘዛል። በቢለት የተቀበሩ ሰባት ግለሰቦች ከያማማ (አል ያማሚ ከሚለው ጋር ተቀራራቢ የሆነ) ጋር የተገናኙ እንደሆነ መረጃ አለ። ይህ ያማማ የሚለው ቃል በመካከለኛው አረብ ሰርጥ ያለ አንድ አካባቢ ነው። ከዛ ውጪ ከመካ፣ ግብፅና ኢራን ዘራቸው የሚመዘዙ ብዙ ግለሰቦች በቦታው ሥርዓተ-ቀብራቸው ተፈፅሟል። ከላይ ከተገለፀው አካባቢያዊ መጠሪያ መሰረት፣ የቤተ ሰቧን እርግጠኛ መሆን ባይቻልም ካሳሙዋ በኢትዮጵያ እንደተወ ለደች ግን መናገር ይቻላል።

ጥንታዊ የሙስሊሙ የመቃብር ላይ ጽሁፎችና ጥቅሶች የሟችን ሙሉ ስም፣ የአረፈበት ቀንና ዘመን እንደ ሂጅራ የዘመን ቀመር፣ በተጨ ማሪም የቅዱስ ቁርዓንን ምዕራፍና ቁጥር በማካተት ይይዙ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ቢስሚላሂ (በአላህ ስም፣ መሐሪ በሆነው፣ ምህረት በሚሰጠው) የጥቅሶች መክፈቻ በመሆን ያገለግላል። የነብዩ መሐመድን ተልዕኮ የሚገልፀው ቁርዓን 9÷128-129 እና ስለ ሞትና ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት የሚያትተው መዕራፍ 3÷185 ሁሉም የሚስተዋሉ ጥቅሶች ናቸው። በሌላ በኩል ለነብዩ፣ ለስሃቦቻቸውና ለመላው ሙስሊም ህዝብ የመልካም ምኞት ማጠቃለያ ፀሎት እንደሚካተት ቢታወቅም በዚህኛው የመቃብር ላይ ጽሁፍ ግን ይህ ፀሎት አልተካተተም።

ከቀይ ባህር የንግድ አውታሮችና የዳህላክ ደሴቶች ጋር በተያያዘ ከ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ እስልምና በትግራይ አካባቢ ጥንታዊ የታሪክ መሰረት እንዳለው የቢለት የመቃብር ቦታ ምስክር ነው። ከ10ኛው-13ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት የውጭ ነጋዴዎች ብቻ ሳይሆኑ የአገሬው ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሴቶችን ጨምሮ ይህን የመቃብር ቦታ ተጠቅመዋል። ይህ ደግሞ እስልምና በኢት ዮጵያ የቆየ ታሪክ ያለው ለመሆኑ ለመገንዘብ በቂ ማስረጃ እንደሆነ ይጠቁማል። ■ [ዡ. ሎ]



**አረቢኛ ጽሑፍ አዘል የመቃብር ላይ ድንጋይ 12**

10ኛው መቶ ክ.ዘ፤ ጥቁር ድንጋይ፤ ቁ. 45 ሳሜ፤ ስ. 40 ሳሜ፤ ወ. 21 ሳሜ. ቢለት

## ፊደላት-አዘል የጌጣጌጥ ቅርጽ-ማውጫ
## 14ኛው-16ኛው መቶ ክ.ዘ

ይህ ከለስላሳና ጠቆር ካለ ሳሙና ድንጋይ (steatite) የተዘጋጀ ድንጋይ የተለያዩ የወርቅና ብር የጣት ፈርጦችንና ኒሻኖችን ቅርጽ ለማስያዝ ወይም ለማምረት የተዘጋጀ ነው። ይህን መሰል ቅርጸ–አካል ድንጋዮች በመካከለኛው ዘመን በነበሩ የሙስሊም አካባቢዎች በብዛት ተገኝ ተዋል። በሃርላ የጌጣጌጥ መስሪያ ቦታ፣ በኪውሃ (ትግራይ) መቃብር ቦታ፣ እንዲሁም ከ1520 ዓ.ም በፊት ለነበረው የባር ሳድ አልዲን ሱልጣኔት መቀመጫ ተብሎ ለተጠቀሰውና በውል ላልታወቀው ዳካር አንድ አካል ሳይሆን እንደማይቀር በሚገመተው ዳርቢጋ (በአሁኑ ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኝ) መሰል ቅርጽ ማውጫዎች መገኘ ታቸው ይጠቀሳል።

እነዚህ ድንጋዮች ለሁለትና ከዛ በላይ ለሆኑ ጌጣጌጦች ቅርጽ ማውጫ የሚሆኑና በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጁ ፍልፍል ቦታዎችን የያዙ፣ የቀለጡ ማዕድናትን ማንቆርቆሪያ ቦይ ያላቸው እንዲሁም የረጉ ጌጣጌጦችን ለማሳመር ብዙ ጊዜና ጉልበት በማያስወጣ ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው።

የፈረዋንዳ ቅርጽ ማውጫ ድንጋይ የተሰበረ ቢሆንም ምናልባት ከተፈላ ጊነቱና እንደልብ ካለመገኘቱ አንጻር በሁለቱም ገፅ ጥቅም ላይ ሳይውል እነዳልቀረ አመላካችና ማረጋገጫ አሻራዎችን ይዟል። በአንድ ጎን ሦስት በጥንቃቄ የተቀረፁና ወጥ የሆኑ የእጅ ጣት ጌጦችን ማውጣት የሚችሉና አናታቸውም በተለያዩ የመስመር ንድፎች የተዋቡ ቅርጾችን ይዟል። ከሶስቱ በአንዱ ላይ «ቢ ላህ» የሚል ጽሑፍ ተቀርጿል ይህም ከአላህ ጋር ወይም በአላህ በኩል የሚል ትርጓሜን ይሰጣል። የተወደደ እስላማዊ ጥቅስና ትንቢታዊ አገልግሎት ያለው ቃል ከመሆኑ አንጻር ቀለበቱን የሚጠቀመው አካል የተከበረ ሰው ሳይሆን እንደማ ይቀር ይገመታል። ተያይዞ በመጨረሻ የሚታየው lam የሚለው ቃል ለቅርፁ መሟያ የተጨመረ እንደሆነ ይታሰባል።

በሌላው ጎን ክብና ወጥ የኒሻን ቅርጽ ማውጫ ቡርቡር ሻሃዳ ከሚል ቃል ጋር ይዟል። ይህ ቃል የእስልምና ሐይማኖት እምነት መገለጫ ሲሆን «ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፣ መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው» የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል። ይህም ከአምስቱ የእስልምና እምነት ምሰሶዎች አንዱና የሙስሊሞች ህይወት በዚህ የተቃኘ እንዲሆን የሚመክርና በተወለደ ህፃን ይሁን በሟች አማኞች ጆሮ የሚታወጅ የቁርዓን መልዕክት ነው። ስለሆነም ይህን ቃል ዛሬም በሙስሊም ጌጣጌጦች ላይ በብዛት የማግኘቱ ዕድል አለ። የመካከ ለኛው ዘመን ማብቂያ አካባቢ እንደነበር በሚታወቀውና ፌዲስ በተባለ ቦታ ሐረር ውስጥ የተገኘና ኋላም የጠፋ ቀለበት ጋር የተያያዘ ክብ የካርኔሊያን ድንጋይ ፈርጥ ይህን ጽሑፍ ይዞ እንደነበር ተጠቁሟል።

የፈረዋንዳ ቅርጽ ማውጫ ድንጋይ በቅሪተ–አካል ጥናት ባለሞያዎች የይፋት ሱልጣኔት መቀመጫ ተደርጋ በምትቆጠረው በሪ ይፋት፤ እ.ኤ.አ 2010 ዓ.ም ተገኘ። ግኝቱም በተመሳሳይ ድንጋይ ከተቀረፁ የተለያዩ ቁሳቁሶች ጋር በተዛማጅ ሲሆን መሰል ለስላሳ ድንጋዮችን በመጠቀም የጠረጴዛ ዕቃዎችን፣ ጌጣጌጦችን እንዲሁም ለሥርዐተ አምልኮ የሚውሉ መገልገያዎችን ማምረቻ ቤተ ሙከራ በስፍራው እንደነበርም ለማረጋገጥ ተችሏል። ከነዚህ ቁሶች በተጨማሪ ከእስያና ከሙስሊም ሀገራት የገቡ ከሸክላ፣ ከባህር እንስሳት ቅርፊት እንዲሁም ከመስታዎት ግብዓቶች የተሰሩ ዶቃዎች ተገኝተዋል። ይህም የከተማ ዋንና ህዝቧን ኢኮኖሚያዊ እድገት ያንፀባርቃል ቅርጽ ማውጫው በራሱ ከሙስሊሙ ባህልና ሐይማኖት ጎን ለጎን በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሹማምንትና ልሂቃን እንደነበሩ ማስረጃ መሆኑ ይወሳል። በጠቅላላው ከውጭ የሚገቡ ቁሳቁሶችን የመጠቀም ባህል ጋር በተዛማጅ የአረቢኛ ፊደላትን በበሪ ይፋት የግል መገልገያ ዕቃዎችና የመቃብር ድንጋዮች ላይ መመልከቱ የሱልጣናቱና ሰፊው የሙስሊሙ ዓለም በጋራ ልማዶችና እሴቶች ዙሪያ የነበራቸውን ቁርኝት ማሳያ ነው። ■ [ሲ. ዶ]

**ፊደላት-አዘል የጌጣጌጥ ቅርጽ-ማውጫ** 13

14ኛው–16ኛው መቶ ክ.ዘ

ሳሙና ድንጋይ፤ ቁ. 4 ሳሜ፤ ስ. 3 ሳሜ፤ ወ. 1.5 ሳሜ

በሪ ይፋት፤ ፈረዋንዳ



## ሀኩናዎች
## 14ኛ-16ኛው መቶ ክ.ዘ

የአውፋት ሱልጣኔት አንድ አካል በነበረችው የመካከለኛው ዘመን ከተማ ኖራ በተካሄደ የቅሪተ–አካል ጥናት ቁፋሮ ወቅት በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደነበረ በተገመተ የቤት አካል ውስጥ ሦስት ተመሳሳይ የቀጫጭን ብረቶች ጥምር አካላት ተገኝተዋል። እያንዳንዳቸው 50 የሚጠጉ የቀጫጭን ብረቶች ጥምር፣ ብረቶቹ ከ40-50 ሚሜ እርዝማኔና ከ1-2 ሚሜ ወርድ ያላቸው፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ጥቅል 23 ግራም የሚመዝን ክብደት ነበረው። የነዚህ ብረቶች ታሪክ የወቅቱ የአረብ ጸሃፊ ኢብን ፋድል አላህ አል ዑማሪ በ1349 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ከገለፃቸውና በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክልሎች ጥቅም ላይ ይውሉ ከነበሩ መገበያያ ብረቶች ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው ያመለክታል። የጸሐፊው ገለፃ እንደሚከተለው ተቀምጧል።«ከአምስቱ የሙስሊም አካባቢዎች ማለትም የብርና ወርቅ ሳንቲም ከሚጠቀመው የአውፋት ከተማ እንዲሁም መርፌ መሰል ብረት ሳንቲም ከሚጠቀሙት ዳዋሮ፣ አራባኒ፣ ሻርክሃና ሃዲያ ውጪ አብዝኃኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ግብይቱን ይፈፅም የነበረው እንደ በግ፣ ላምና አዝዕርት የመሳሰሉ ነገሮችን ለለውጥ በማቅረብ ነበር። ረዘም ያለ መርፌ መሰሉ የብረት መገበያያ ሃኩና ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ሦስት ሺህ ሃኩናዎች የአንድ ድርሃም ዋጋ አላቸው። አንዱ ሃኩና የሦስት መርፌ ውፍረት አለው። ከዚህ አንጻር ለገበያ የሚቀርቡ ግብዓቶች ያን ያህል ዋጋ (ትርፍ) አላቸው ብሎ ለመናገር አያስደፍርም ለምሳሌ አንድ ጥሩ ላም በ5000 ሃኩናዎች አንድ ጥሩ በግ ደግሞ በ3000 ሃኩናዎች ይሸጡ ነበር።»

በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ኑር አል–ማዓሪፍ በተባለው ጉባኤ የራሱሊድ አስተዳደርና ንግድ ስምምነት ላይ እንደተገለፀው ሃኩናዎች ወይም መሰሎቻቸውና ጂካዎች ተብለው የሚታወቁት የመገበያያ ገንዘቦች ቀደም ብለው አገልግሎት ይሰጡ ነበር። ሰነዱም «የሙስሊሙ ሀገሮችና ግዛቶች ከሆኑት ዋላ፣ አስማ፣ ካልጁርና በሥራቸው ካሉ ክልሎች በተጨማሪ የክርስቲያኑ ሥርዎ–መንግሥት ወይም አምሃራ ግዛቶችም ጂካ (መርፌ መሰል ብረት) ለመገበያያነት ይጠቀሙ ነበር። እያንዳንዱ ጥቅልም መቶ ጂካዎችን ይይዛል። ይህ እንግዲህ የብር፣ የመዳብና የወርቅ ሳንቲማቸው ነው። በሀገራቸው በሱልጣናቱ ግምጃ ቤቶች ከሚገኙት ውድ ዕቃዎች ውስጥ ጂካዎችም ይገኛሉ።»

ከመዳብ ቅይጥ የተዘጋጁ መሰል መገበያያዎች በሌሎች የመካከለኛው ዘመን አፍሪካ ሀገራት ይገኙ እንደነበር የታዋቂው ተጓዥ ኢብን ባቱታ (1362 ዓ.ም) ማስታወሻ ይጠቁማል። በአንዳንድ ሀገራት የተከናወኑ የቅሪተ–አካል ቁፋሮዎችም ይህን አመላክተዋል፤ በሞሪታንያ ኮምቢ ሳለህ በተባለ አካባቢ አንድ የነጋዴ መኖሪያ ቤት ውስጥ 106 ሃኩናዎች በማሰሮ ውስጥ የተገኙ ሲሆን ሌሎችም በተለያየ ሁኔታና ቦታ እንደተገኙና ዕድሜ ልኬታቸውም ከ11ኛው እስከ 15ኛ ክፍለ ዘመን መባቻ ተገምቷል።

የባህል ብዝሃነት በሚንፀባረቅባት የመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያ በተለይም ክርስቲያን፣ ሙስሊሙና፣ ከነዚህ የተለየ እምነት ያለው ማህበረሰብ በሚኖርበት የይፋት ከተማ አካባቢ ለነበረው የንግድ ግንኙነት የኖራ ሃኩናዎች የመገበያያ ገንዘብን ፍላጎት ተክተው እንዳገለገሉ መናገር ይቻላል። ምንም እንኳን የመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያና እንዲሁም ሌሎች በሙስሊሙ ግዛት ሥር የገቡት ክልሎች፣ በቀይ ባህርና ህንድ ውቅያኖስ በኩል በነበረው የረጅም እርቀት ንግድ የተሳሰሩ ቢሆንም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከባህላዊው የግብይት ሥርዓት በዘለለ ገንዘብ የመጠቀም ሁኔታው አነስተኛ እንደነበር መናገር ይቻላል። በእርግጥ ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት የሳንቲሞች ምርት ያን ያህል እድገት አልነበረውም። እንደ ግብፅ፣ ቢላድ አል–ሻም (ታላቋ ሶሪያ)፣ እንዲሁም የመንን በመሳሰሉ የሙስሊም ሀገራት የተመረቱ ሳንቲሞች በሃርላ፣ ደርቢጋ፣ ራሳ (ሶሬ ቀበናዋ) ተገኝተዋል፤ ይሁንና ከሌላው ዓለም ጋር በሚደረጉ የንግድ ልውውጦች ላይ ከመጠቀም ወይንም እንደውድ ዕቃና ጌጣጌጥ መስሪያነት ከመገልገል በዘለለ በማህበረሰቡ ውስጥ ለግብይት የተሰራጩ አልነበሩም። ■ [ሲ. ዶ፣ አ. ሼ፣ ሮ. መ]

**ሀኩናዎች** 14

14ኛ-16ኛው መቶ ክ.ዘ

ብረት፤ ስ. 4-5 ሳሜ፤ ወ. 1.2 ሳሜ፤ ክ. 23 ግራም

ኖራ፤ ኮድ ■ Nor-08-2-B05-2038-005 እና ■ Nor-08-2-B05-2038-006



## የቻይና ሸክላ ስባሪዎች
### 6ኛ-15ኛው መቶ ክ.ዘ

በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ፣ የቻይና የሸክላ ዕቃዎች በህንድ ውቅያኖስ በኩል በመላው ዓለም ተሰራጭተው ነበር። እነዚህ ምርቶች ከደቡባዊ ቻይና ግዛቶች ወደ ደቡብ እስያ ከዛም በመቀጠል ወደ ምዕራብ እስያና አፍሪካ እንዲሁም ወደ ደቡብ ምዕራብ አውሮፓ ባህረ-ገብ መሬት (ኢቤሪያ) ይጓጓዙ ነበር። በነዚህ አካባቢዎች በበርካታ ቅሪተ-አካል ጥናት ስፍራዎች ላይ ተገኝተዋል።

የእነዚህ ሸክላ ስባሪዎች መገኛ ከ6ኛ-15ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ የመኖሪያ አካባቢ በነበረችው ሃርላ ሲሆን ከ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ባሉ ጊዜያት ደግሞ የሙስሊም ማህበረሰብ መቀመጫ እንደነበረች ታውቋል። በስፍራው በተደረገ ቁፋሮ መስጊዶች፣ የመኖሪያ መንደሮች፣ በተጨማሪም የጌጣጌጥ ቤተ-ሙከራዎች የተለዩ ሲሆን በውስጣቸውም የብርጭቆ ስባሪዎች፣ ከሰሜን አፍሪካና እስያ የገቡ ጨሌዎች፣ የባህር እንስሳት ቅርፊቶች፣ የድንጋይና የመስታወት ጨሌዎች፣ የጌጣጌጥ ቅርጽ ማውጫዎች፣ የድንጋይ መሳሪያዎች፣ ሳንቲሞች (የቻይናን ሳንቲም ጨምሮ) እና በአካባቢው የተመረቱና ከየመን፣ ኢራን፣ ግብፅ፣ ህንድና ቻይና የገቡ የሸክላ ውጤቶች ተገኝተዋል። በሃርላ ከ200 በላይ የቻይና የሸክላ ሥራ ውጤቶች ከሆኑትና ሴላዶን ተብለው ከሚታወቁት እቃዎች የተሰባበሩ ቅሪቶች ተገኝተዋል። አነስተኛ መጠን ያላቸው ጎርጓዳ ሳህኖች፣ ነጫጭ ሳህኖች፣ በቡናማ ብረት-ቅብ የተለበጡ የፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገሮች ማጠራቀሚያ (ምናልባት ከደቡባዊ ቻይና ወይም ደቡብ ምሥራቅ ስስያ ሀገራት የመጡ)፣ ግራጫ ብረት-ቅብ ሸክላ ስባሪ (ምናልባት ከማይናማር) ከግኝቶቹ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። ይህም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውና በዕድሜ ቀደምት የሆኑ ቁሳቁስሶችን ያስመዘገበ (ከ12ኛ-14ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት የተገመቱ) የመካነ-ቅርስ ቦታ ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት አስችሏል።

ሁለቱ አረንጓዴ የሸክላ ስባሪዎች ሴላዶን ናቸው። ሴላዶን የሚባሉት የሸክላ ዕደ-ጥበብ ውጤቶች የደቃቅ ድንጋይና ሸክላ ውህድ ሥራዎች ሲሆኑ በተለያዩ ማዕድናት የሚለሰልሱና በከፍተኛ ሙቀት የሚበስሉ ናቸው። በአረንጓዴ ቅብ የለሰለሱት ሸክላዎች በአብዝሃኛው በህንድ ውቅያኖስ አጎራባች ሀገራት ውስጥ ከ9ኛ-15ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት የውጭ ንግድ እንቅስቃሴ ግባዓት ነበሩ። ነጩ ስባሪ ዲንግ ተብሎ ይታወቅ ከነበረ የሰሜናዊ ቻይና ባለ እግር ጎድጓዳ ሳህን የተገኘ ሲሆን ከ10ኛ-12ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ጥቅም በመስጠት የሚታወቅና የዝሆን ጥርስ የመሰለ ነጭ ብረት-ቅብ እንዲሁም ጥቅል ወረቀት የመሰለ ማስዋቢያ ቅርጽ የተላበሰ ሥራ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ቦታ ከ75% በላይ የሆኑት ሸክላ ውጤቶች እንደገና በተለያየ ቅርጽ ተሰርተው ጥቅም ላይ እንደዋሉ ተስተውሏል።። ከነዚህ ውስጥ በክብ፣ በጠፍጣፋና በባለብዙ ጎን ቅርጾች የተዘጋጁ በብዛት ሲኖሩ ይህን መሰሉ ዳግም ቅርጽ የመስጠት ወይም ለሌላ አገልግሎት የማዋል ሂደት ያልተለመደ ነገር ግን በዚህ ስፍራ የታየ ክሥተት ነው። ብዙዎቹ ከቤተ ሙከራ አካባቢ የገተኙ ሲሆን ልክ እንደ ድንጋይ ጠረባና ቀረፃ ዐይነት ተግባር ይከናወንበት የነበረ ቦታ እንደሆነ ከተገኙ ጥራቢ ቅሪቶች መረዳት ተችሏል። የተለያዩ ጌጣጌጥና ጨሌዎች፣ እንዲሁም ማኅተሞች፣ ከውጭ በሚገቡ የካሜሊያን (camelian)፣ ውሃማ ድንጋይ (quartz) እና የባህር እንስሳት ቅርፊት (ዛጎል) ግብዓቶችን በመጠቀም በሃርላ ቤተ-ሙከራዎች ይመረቱ እንደነበር መረዳት ተችሏል። ከዚህ አንጻር በስፍራው ውድ ከሆኑ የጌጣጌጥ ማዕድናት ጋር የሚመሳሰሉ የተለያዩ ጌጦችን የማምረት (cabochons) ተግባር ነበር የሚል እሳቤ አለ።

በኢትዮጵያ የቻይናውያን ሸክላ ቁሶች በመካከለኛው ደጋማ አካባቢዎች፣ ማለትም በበረ-ይፋት፣ አፅባሪና ተጨኖ እንዲሁም በምሥራቃዊው ክፍል በሃርላ፣ ሐረርና ጂልዳሳ ባሉና ከሱልጣኔቶች ጋር ቁርኝት በነበራቸው አካባቢዎች ተገኝተዋል። እንደ እንስላሴ ቤተክርስቲያን ባሉ የክርስቲያን አካባቢዎችም ሰማያዊና ነጭ ሸክላ ስባሪዎች የተገኙ ሲሆን፣ ከነዚህ ማስረጃዎች በመነሳት የቻይና ሸክላዎችን ማስገባትና በሰፊው ጥቅም ላይ የማዋሉ ሁኔታ በኢትዮጵያ ከ800 ዓመታት በላይ የሆነ ጥንታዊ የታሪክ አንድምታ እንዳለው መረዳት ይቻላል። የሸክላ ውጤቶች በኢትዮጵያና ሌላው ዓለም መካከል የነበረውን የንግድ ልውውጥ ከማሳየት በዘለለ ተመሳሳይ የሆነ ቁሳዊ ባህል ለመኖሩ ማስረጃ ናቸው። በቁጥር የበዙ ለምሳሌ ለመመገቢያ፣ ለእቃ ማጓጓዣና ማስቀመጫ፣ ለተለያዩ ዕደጥበባት ሥራ ጥሬ ዕቃነት፣ ለሐይማኖታዊ ግልጋሎት፣ ለውበት፣ ለስጦታ ማቅረቢያና ለነገስታት እጅ መንሻነት ብሎም እስካሁን ለዘለቀው የቡና ማቅረቢያ ሲኒ አገልግሎት ጭምር የሸክላ ውጤቶች ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ጠቀሜታ ነበራቸው። ■ [ሃ. ፓ. ሞ]







## የቻይና ሸክላ ስባሪዎች 15

6ኛ-15ኛው መቶ ክ.ዘ

ሴላዶን፤ ሎንግኩዋን ኪልን ኮምፕሌክስ

ዜጂያንግ አውራጃ፣ ቻይና

የጣባ ወይም ጎድጓዳ ሳህን መቀመጫ ስባሪ

- እግር 6 ሳሜ አጠቃላይ ስፋት 75×40×25 ሳሜ፤ ኮድ Har 18 (M) 1a
- አነስተኛ ባለ ስምንት ጠርዝ ስባሪ፤ 8.7×7.6 ሳሜ፤ ኮድ Har 15 (B) 9a

ነጭ ሳህን፤ የዲንግ ኪልን (Ding kilns) ምርት፤ ኼቤ አውራጃ፣ ቻይና

- የጎድጓዳ ሳህን ስባሪ፤ 15.3×22.3 ሚሜ፤ ኮድ Har 19 (E) 28b

ሃርላ



## የግዙፍ ድንጋዮችና ሐውልቶች ባህል

በመላው የኢትዮጵያ ግዛቶች በሚባል መልኩ፣ ባለቅርፅና ቅርጽ አልባ የሆኑ ግዙፍ የድንጋይ ሐውልቶችንና መታሰቢያ ስፍራዎችን የማቆም ሥራ ከሁለት ሺህ ዓመተ-ዓለም ጀምሮ ሲከናወን የነበረና እስካሁን የሚስተዋል ጥበብ ነው። የወቅቱ ማህበረሰብ የድንጋይ ሐውልትና መታሰቢያዎችን ለሙታን ክብር፣ ለግዛት መለያ ወይም ለህያልነት ማሳያ እንደ ምልክት አድርጎ ይጠቀማቸው ነበር። እነዚህም መታሰቢያዎች በዐይነትና በቅርጽ ደረጃ ክምር፣ ትክል፣ ጠረጴዛ ወይም ኮፍያ ቅርጽ ድንጋዮች ተብለው ተለይተዋል። ስለ አሰራራቸውና አቀማመጣቸው ስናነሳ ጠንካራ አመራር፣ ጠቢባንና ብዛት ያለው የሰው ኃይልን እንድ ናስብ እንገደዳለን። ድንቅና ለእይታ ማራኪ የሆኑ፣ ከመልክዐ-ምድራዊ አቀማመጥ ጋር የተጣጣሙ፣ እንዲሁም ተፈጥሮን ባማከለ መልኩ የተሰሩ ውድና ብርቅዬ የኢትዮጵያ መካከለኛ ዘመን መገለጫ ቅርሶች እንደሆኑ ልብ ሊባሉ ይገባል።

ምንም እንኳን በራሳቸው የተመዘገበ ምንጭ ባይኖርም በታሪካዊ መዛግብት እንደተጠቀሱበት አግባብ፣ የዚህ ጥበብ ባልቤቶች፣ ከአብርሐማዊ እምነቶች በተለየ ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ይኖሩ የነበረና፣ በቅድመ-ታሪክና በታሪክ ዘመን ውስጥ መካከለኛ ስፍራ የሚሰጣቸው (proto-historical) ማህበረሰቦች እንደሆኑ ይታሰባል። የሥራዎቻቸው ቅሪቶችም በዕድሜ፣ ስደት፣ በባህል መበረዝ፣ በሐይማኖት ለውጥና መቀያየር፣ ያልተበገሩና ዘመን ተሻግረው ለእኛ የተላለፉ ናቸው። ይሁንና የትክል ድንጋዮችና ሐውልቶች አፈ-ታሪካዊ አሳቤ ከአንድ ግዙፍ፣ በኃያልነቱ አስፈሪ ከሆነ ምናባዊ ግለሰብ ጋር የተቆራኘ መሆኑን ልብ ይሏል። እነዚህ ቅርሶች በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ በነበሩ ብዙ ተጓዦች ማስታወሻ ላይ ተጠቅሰዋል፤ ኋላም በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ በሰሜኑና ደቡብ የአገሪቱ ክፍል የዳሰሳ ጥናቶች ሊደረጉ እንደቻሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ፍራንስዋ አዛይስ በደቡብ በኩል ለነበሩት ጥናቶች ሁሌም ተጠቃሽ ነው። በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ መካከለኛውንና ደቡብ ኢትዮጵያን ጨምሮ የቅሪተ-አካል ጥናት ለነዚህ ቅርሶች ትኩረት መስጠት የጀመረበት ሲሆን የወቅቱን ማህበረሰብ ታሪክ፣ ባህላዊ እንቅስቃሴና ጥበብ ለመረዳት አግዟል። በዕድሜ ታላቅና ጥንታዊ የሆኑት ባለባርኔጣ ቅርጾቹ (ደጋ ኮፍያ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው) ሲሆኑ፣ እነዚህም እንደ ግድግዳ በቆሙ ድንጋዮች ላይ አግዳሚ ወይም ክዳን ድንጋዮችን በማስቀመጥ የሚሰሩ ናቸው። በሐረር ተራራዎች ላይ የሚገኙና፣ በ2ኛው ሺህ ዓመተ-ዓለም አካባቢ ለመቃብር ቦታዎች መታሰቢያነት እንደተመሰረቱ ታውቋል። የ24 ሜትር ከፍታ ያለውና በዓለም ትልቁ የአክሱም ሐውልትና በአቅራቢያው የሚገኙ ብዛት ያላቸው ትክል ድንጋዮች በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራን ይዘዋል። በመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያም፣ በስምጥ ሸለቆ አካባቢ በተለየ መልክና ቅርጽ ዳግም ተተግብሯል። ይህም በብዙ አካባቢዎች የሚገኙትን ልዩ የድንጋይ-መር መታሰቢያዎችንና የቀብር ሥርዓቶችን በመመርኮዝ ተመሳሳይ ባህል የተንፀባረቀበትን ዘመን ለመለየት ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

በመካከለኛው ኢትዮጵያ መንዝ፣ ሻይ ወንዝ አካባቢ «የሻይ ባህል» የሚል ስያሜ የተሰጠው፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ መቃብሮችን የያዘና በድንጋይ ክምችት የተፈጠሩ ጉብታዎች የሚስተዋሉበት ስፍራ ይገኛል።በቦታው የተደረገ ቅሪተ-አካል ጥናት እንደሚያሳየው በክምር ድንጋዩ ሥር፣ ክብ ክፍልና እንደ ደጋ ኮፍያ ባሉ ግዙፍ ድንጋዮች የታነፀ ኮሪደር፣ ያለው የቀብር ማዕከል ሆኖ ተለይቷል። ቦታው ከ10ኛው-14ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ እንደተመሰረቱ ከሚገመቱት፣ በስምጥ ሸለቆ ምሥራቃዊ ጥግ፣ በጨርጨር ተራሮች ላይ ከተገኙት የመቃብር ስፍራዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታን ይጋራል። እነዚህ የብዙሃን መቃብር ቦታዎች ብዛት ያላቸው ቁሳቁሶች ተከማችተው የተገኙባቸው ጥናት ማዕከላት ሲሆኑ፣ በተለይም የሀገር ውስጥና የውጭ ጨሌዎች ተጠቃሽና በቦታው ለነበሩ ህዝቦች ማስረጃ ናቸው። በሌላ በኩል በአገር ውስጥ ሆነ ከውጪ ሀገራት ጋር ለሚደረጉ ቁሳዊ ልውውጦች በማዕከልነት ማገልገሉ ጥርጥር የለውም። በመካከለኛው ኢትዮጵያ መንዝ፣ ሻይ ወንዝ አካባቢ «የሻይ ባህል» የሚል ስያሜ የተሰጠው፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ መቃብሮችን የያዘና በድንጋይ ክምችት የተፈጠሩ ጉብታዎች የሚስተዋሉበት ስፍራ ይገኛል።በቦታው የተደረገ ቅሪተ-አካል ጥናት እንደሚያሳየው በክምር ድንጋዩ ሥር፣ ክብ ክፍልና እንደ ደጋ ኮፍያ ባሉ ግዙፍ ድንጋዮች የታነፀ ኮሪደር፣ ያለው የቀብር ማዕከል ሆኖ ተለይቷል። ቦታው ከ10ኛው-14ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ እንደተመሰረቱ ከሚገመቱት፣ በስምጥ



የጢያ ትክል ድንጋዮች፣ የመቃብር ጉድጓድ አቃፊ ድንጋዮች ጋር፤ በ1990ዎቹ ዓመታት




ክምር እና ትክል ድንጋይ ቦታዎች፤ ሰሜን ሸዋ፣ እ.ኤ.አ 1978 ዓ.ም

ሸለቆ ምሥራቃዊ ጥግ፣ በጨርጨር ተራሮች ላይ ከተገኙት የመቃብር ስፍራዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታን ይጋራል። እነዚህ የብዙሃን መቃብር ቦታዎች ብዛት ያላቸው ቁሳቁሶች ተከማችተው የተገኙባቸው ጥናት ማዕከላት ሲሆኑ፣ በተለይም የሀገር ውስጥና የውጭ ጨሌዎች ተጠቃሽና በቦታው ለነበሩ ህዝቦች ማስረጃ ናቸው። በሌላ በኩል በአገር ውስጥ ሆነ ከውጪ ሀገራት ጋር ለሚደረጉ ቁሳዊ ልውውጦች በማዕከልነት ማገልገሉ ጥርጥር የለውም።

በስምጥ ሸለቆ ምዕራባዊ ተራሮች ግርጌ፣ ከአቀራረፃቸው ጥበብ፣ ከጌጥና ቅርጻቸው አንጻር በስድስት ዐይነት የተከፈሉ ትክል ድንጋዮች ይገኛሉ። እነዚህም ጎራዴ አዘል፣ ማበጠሪያ መሰል፣ ንፍቀ ክብ ወይም አታሞ መሳይ፣ ምስል አዘል፣ ጭንብል አዘልና ብልት መሳይ በሚል መጠሪያና መለያ የሚገለጹ ናቸው። በጢያ ዓለም አቀፍ ቅርስ (1980ዓ.ም የተመ ዘገበ) ስፍራ የሚስተዋለው የድንጋይ ላይ ቅርጽ ለጎራዴ አዘል ትክል ድንጋዮች ታዋቂ ምሳሌ ነው። ከምንና ለምን ዕሳቤ እነዚህ ትክል ድንጋዮች እንደተፈጠሩ እስካሁን በቂ እውቀት የለም። መልክዐ-ምድራዊ ሥርጭ ታቸው ድግግሞሽ ሊኖረው ይችላል። ከዛም አልፎ በዐይነት የተለያዩ ትክል ድንጋዮች በአንድ መታሰቢያ ስፍራ ሊገኙ ይችላሉ። በደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍል ከሚስተዋሉት ምስል አዘል ትክል ድንጋዮች ጋር ሊነፃፀሩ የሚችሉ ጥቂት ትክል ድንጋዮች በጥቂቱ በኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎችም ይገኛሉ። በምስል አዘል ትክል ድንጋዮች ላይ የተለያዩ ቅርጾች በተለያዩ አካባቢዎች የተስተዋሉ ቢሆንም አብዛኞቹ አንድ የጋራ የሆነ ማስጌጫ ቅርጽ አላቸው፣ ይህም «ሹካ» ወይንም «አትክልት» የመሰለ ቅርጽ አለው። አሰራሩ ወደ ውስጥ ተፈልፍሎ ወይንም ከዋናው ዐለት ወጣ ብሎ ሲሆን በአብዝሃኛው በትክል ድንጋዩ ታችኛው ክፍል ወይም እንደ እምብርት ዝቅ ብሎ ከተቀረጸ ቦታ ዙሪያ ይገኛል። የዚህ ምልክት አንድምታ «ከህይወት ምንጭ» ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ለምግ ብነት፣ ለመድሃኒትነትና ለእንስሳት መኖነት አገልግሎት ከፍተኛ ጠቀሜታ ከሚሰጠው የ«እንሰት» (Ensete ventricosum) ተክል ጋር ተዛማጅ ሳይሆን እንዳልቀረ ይታሰባል።

የትክል ድንጋዮች (ሶዶ) ዐይነትና ሥርጭት ተመሳሳይ ባህላዊ ልማድ የነበረው አስተዳደራዊ መዋቅር ወይም ማህበረሰብ እንደነበር ማሳያ ነው። ያ ማለት ከክርስቲያኑና ዳማት ሥርዎ መንግሥት፣ ከሸዋና ይፋት ሱልጣኔት ጋር ከ11ኛው እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ በጋራ ኖረዋል ብሎ ማረጋገጥ ይቻላል። በአፍሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ትክል ድንጋዮች በዐይነትና ይዘት ተከማችተው ከሚገኙባቸው አካባቢዎች አንዱ ከአባያ ሐይቅ በስተምሥራቅ ያለው የስምጥ ሸለቆ መልክዐ-ምድር ነው። በዚህ ክልል 150 ኪ.ሜ አየር ወሰን፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ግዙፍና ብልት መሳይ ትክል ድንጋዮች የመልክዐ-ምድሩን ጉብታዎች በሚያጎላ ሁኔታ ተሰራጭተው ይገኛሉ። ትክል ድንጋዮቹ በአሥርና በመቶዎች በሚቆጠር ብዛት፣ መስመር ጠብቀው የተሰለፉ፣ በአንድ አንድ ስፍራዎች በተለይም በጨልባ-ቱቱቲ መካነ-ቅርስ ስፍራ በሺዎች የሚስተዋሉ፣ ጥቂቶች ከ8ኛው-12ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ለሙታን መታሰቢያና ለመቃብር ምልክትነት ሌሎች ደግሞ ለአምልኮና ምስጋና ወይም ለሌላ መታሰቢያ አገልግሎት እንደቆሙ ይነገራል።

ከአባያ ሐይቅ በስተምሥራቅ መካከለኛ አካባቢዎች ቀደም ሲል ብልት መሳይ የነበሩ ትክል ድንጋዮች ወደ ሰው ምስል አዘል ቅርጽ ተቀይረው በመቃብሮችና በመሰል ድንጋይ ክምሮች ስፍራ ይስተዋላሉ። የድንጋይ ክምሮቹ አካባቢው የቀብር ቦታ ከመሆኑ አንጻር ለእያንዳንዱ ቀብር በሚደረገው የድንጋይ ክምችት የተፈጠሩ ጉብታዎች መሆናቸው የተረ ጋገጠ ሲሆን ለዚህ ጥሩ ማሳያ የቱቱ ፈላ መካነ-መቃብር ተጠቃሽ ነው። ይህ ስፍራ ከ12ኛ-15ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለና ከ300 በላይ ትክል ድንጋዮችን የያዘ በክምር ድንጋይ ጉብታ የታጀበ ነው። ይህ ክምር ድንጋይም በተለያዩ ዘመናት ጥቅም ላይ የመዋል ውጤት መሆኑ በተደረጉ ጥናቶች ሊለይ ችሏል። በዚህም በመጀመሪያ ቀደምት ጥልቅና ዋሻ መሰል መቃብሮች ከሥር እንደነበሩ ከጊዜ በኋላ በድንጋይና አፈር ክምችት በመሸፈናቸው ምክንያት ከበላያቸው ሌሎች የቀብር ቦታዎች እንደተመሰረቱባቸው ታውቋል። በተያያዘም ቀደም ቶቹና ከሥር ያሉት ስፍራዎች በብልት መሳይ ትክል ድንጋዮች ምልክት የተደረገባቸው፤ የኋለኞቹ ግን ከብልት መሣይ ወደ ሰው ምስል አዘል ትክል ድንጋዮች ቅርጽ የተለወጡ ሐውልቶችን በመያዝ መገኘታቸውን የዘርፉ ተመራማሪዎች አረጋግጠዋል። ከድንጋይ ክምሮቹ ሥር በጣም ብዙ የሸክላ ስባሪዎች፤ እንዲሁም በእነዚህ ማህበረሰቦችና ሰሜናዊው ወይም በተቀረው የአገሪቱ ግዛት መካከል የነበረውን የመካከለኛው ዘመን ረጅም ርቀት ንግድና የኢኮኖሚ ትስሥር የሚያሳብቁ ጨሌዎች በስፍራው ተገኝተዋል። ■ [አ.ሊ.ጉ፣ አ. በ]

## የትክል ድንጋይ ስባሪ

ይህ ከአንድ ዐለት ክፋይ የተሰራ ትክል ድንጋይ ካልታወቀ ስፍራ ወደ ሙዚየም ስብስብ የገባ ሲሆን ከላይና ከታች የነበሩት ክፍሎቹ ተሰብረው እንደተወገዱ ያስታውቃል። የፊት ለፊቱ ገፅታ የተለያዩ ቅርጾችን የተላበሰና ጀርባው ግን ተፈጥሯዊ ማንነቱን እንደጠበቀ የተገኘ ነው። ከዚህ አንጻር ምስል አዘል ከምንላቸው ትክል ድንጋዮች ጎራ የሚመደብ፤ በተጨማሪም ከመሰሎቹ መገኛና አካባቢያዊ መጠሪያ አንጻር «የደቡብ ሶዶ» የሚል መለያ የተሰጠው ነው።

ሁለቱም ጎኖቹ የተጠረቡና ያማሩ ናቸው። ሦስት ሰው መሰል ቅርጾችንና ጥቂት ግልፅ ያልሆኑ ዕቃዎችን ቅርጽ በላዩ ይዟል። አንድ ወይም ሁለት የፈረስ ጌቶች፣ በእኩል ቁመት ያሉ አንድ እንስሳና አንድ ሰው፣ ዘንቢል ወይም ደወል መሰል ቁስ፣ የፈረስ ልጓም፣ ወደታች ያዘቀዘቀ ጦርና ሌሎች በግልፅ ያልታወቁ ቅርጾችን በገፁ ያመለክታል።

እነዚህ ንድፎች መሐል ላይ ከተቀመጠው የመስቀል ቅርጽ ዙሪያ የተዋቀሩ ሲሆን ባለአራት ማዕዘን ከታች ሰፊና ከላይ ጠባብ መቀመጫ ኩርሲ መሰል ዕቃ ላይ ቀጥ ብሎ የተቦረቦረ መስመር የያዘ፤ ከዚህም መስመር ላይ ሁለት ደረጃ ያላቸው የ V ቅርጾች ይገኛሉ። ይህ ቅርጽ ከሸዋ አንስቶ እስከ ጌዴኦ ድረስ ውስብስብ በሆነ ገፅታ የሚስተዋል፣ የሚበተን ወይም የሚሰራጭ ነገርን የሚወክል፤ ብሎም የተክል ወይም ዕፅ ከዛም አልፎ በጠቅላላ ህይወትን የሚወክል መግለጫ እንደያዘ ይገመታል።

የዚህ ትክል ድንጋይ መረጃ እ.ኤ.አ 1976 ዓ.ም እና 1982 ዓ.ም በፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል ዓመታዊ መፅሄቶች ላይ የቀረበ ሲሆን ወቅቱ ደግሞ የኢትዮጵያ አርኪኦሎጂ ኢንስቲቲዩት ቡድን የምርምር ትኩረት በስምጥ ሸለቆ አካባቢ ተሰራጭተው በሚገኙ ግዙፍ የድንጋይ ሐውልቶችና መታሰቢያ ቦታዎች ላይ ዳግም ተጠናክሮ የቀጠለበት ነበር። በዚህም የትክል ድንጋዩን አያያዝና ጥበቃ በተመለከተ፣ በአንድ ግለሰብ ቤት ወይም በተከለለ ቦታ ከቆየ በኋላ እ.ኤ.አ ሚያዝያ 1979 ዓ.ም ወደ ብሔራዊ ሙዚየም ስብስብ እንደተጠቃለለ ሪፖርቱ ያሳያል። ምንም እንኳን ቅርሱን የሰጠው ሰው ከማረቆ እንደተገኘ ቢገልፅም፣ በተጠቀሰው ቦታ ምንም አመላካች ፍንጭ ወይም ማረጋገጫ ማግኘት እንዳልተቻለ ተገልጿል። በብዙ ትዕይንቶች በተሞላው የጌጣጌጥ ንድፉ መሰረት ምናልባትም ይህ ቅርስ ከአዲስ አበባ 170 ኪ.ሜ እርቀት ከሚገኙትና ምስል አዘል ትክል ድንጋዮች ከሚስተዋልባቸው የስልጤና መስቃን አካባቢዎች የተገኘ ሳይሆን እንዳልቀረ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ። ሌላው መታወቅ ያለበት ሁኔታ እነዚህ ትክል ድንጋዮች ከቀላል ዐለት እንደመፈልፈላቸው እና ለተደጋጋሚ መፈናቀል ወይም በቀላሉ ለማጓጓዝ የማይከብዱ ከመሆናቸው አንጻር በመሰል ቅርሶች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት አዳጋች ነው። በወቅቱ 18 መሰል ድንጋዮች የተመዘገቡ ቢሆንም ዘጠኙ እስካሁን በቦታቸው እንዳሉ፤ ሦስቱ በሮም ጣሊያን የአፍሪካና እስያ ኢንስቲቲዩት ውስጥ እንደሚገኙ ታውቋል። ከነዚህ ውስንና መሰል መታሰቢያ ድንጋዮች ጠቅላላ ሁኔታ በመነሳት ይህ የትክል ድንጋይ አንድ አካል፣ እናትና መቀመጫ እንደነበረው፣ እስከ ሁለት ሜትር የሚረዝም ቁመት ሊኖረው እንደሚችልም ተገምቷል።

ምስል አዘል ትክል ድንጋዮች የዕድሜ ልኬት ጥናት አልተደረገባቸውም፤ ይሁንና በ1920ዎቹ መጀመሪያ ምናልባትም ብቸኛ የሆነ ጥናት በአባ ፍራንስዋ አዛይስ የተከናወነ ሲሆን በፎቶዎች የተደገፈ ገለፃም የታከለበት ሥራ ነበር። በወቅቱ የተከናወነው ቁፋሮ ትክል ድንጋዮቹ ከሥራቸው በትልልቅ የድንጋይ ድጋፍና እርከን መሳይ ማገጃ የቆሙ መሆናቸው ታውቋል። በተጨማሪ ሦስት ሜትር ጥልቀት ላይ የመቃብር ጉድጓድ የተገኘ ሲሆን በዘራፊዎች ጥቃት ሳይደርስበት እንዳልቀረ አመላካች ሁኔታዎች ተስተውለዋል። የመቃብሩ ግድግዳ፣ ስሌዳ በመሰሉ ሁለት ቋሚና በአንድ ክብ ክዳን ድንጋዮች የተሰራ ነበር። ከዛ አንጻር እነዚህ ትክል ድንጋዮች የተለየ ማህበራዊ ደረጃና ዝና ላላቸው ግለሰቦች መታሰቢያና የመቃብር አመላካች ሳይሆኑ እንደማይቀር ተገምቷል። በተጨማሪም እነዚህ ጥርጥር ንድፎች የተለየ ግለሰብን (አስፈላጊ ሰው) ሁኔታና ህይወት ጠቋሚ ወይም የማህበረሰቡ ልዩ መገለጫዎችን ወይም ዕሴቶችን አመላካች ሊሆኑ ይችላሉ። ■ [አ.ሊ.ጉ፣ አ. በ]

**የትክል ድንጋይ ስባሪ 16**

በሃ ድንጋይ፤ ቁ. 116 ሳሜ፤ ስ. 97 ሳሜ፤ ወ. 9 ሳሜ ፤ ያልታወቀ ቦታና ጊዜ



## ባለ-ዳሌ ገንቦ፤ የሻይ ባህል መገለጫ
## 10ኛው መቶ ክ.ዘ

ይህ የሸክላ ዕቃ ውብ ቅርጽ ያለውና በቅሪተ-አካል ጥናት ባለሞያዎች «በራሪ ሳህን» የሚል ስያሜ የተሰጠው ነው። በመካከለኛው ኢትዮጵያ አብርሐማዊ እምነት ውስጥ ሳልነበረው የሻይ ባህል ልዩ መገለጫ ሸክላ ሊሆንም ችሏል። በ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተ መረተ የተገመተና በመንዝ፣ ጠጠር ጉር በሚባል የመቃብር ክምር ድንጋይ ሥር የተገኘ ነው። ይህን መሰል ብዙ የመቃብር ቦታዎች በሻይ ወንዝ ዙሪያ የተገኙ ሲሆን ስሙም ለዚህ ታዋቂ የመካከለኛው ዘመን ባህል መጠሪያነት እንደዋለ ልብ ሊባል ይገባል።

ይህ የሸክላ ዕቃ ክብ በሆነ የታችኛው ክፍል፣ ቱቦ መሰል አንገቱ፣ እንዲሁም ሰልካካ የመሀል ጠርዙ (ዳሌ) ይታወቃል። የሰውነቱ ቁመት ከወርዱ አንጻር አጭር የሚባል፤ የጠርዙም መመለሻ ማዕዘን ከ40 ድግሪ በታች ነው። ይህ ንድፍ ሸክላው በሚሰራበት ጊዜ ባልተመ ጣጠነ ክብደትና ስበት ምክንያት እንዳይፈርስ ተጠንቶ የተደረገ እንደሆነ ለማሰብ እንገደዳለን። በሸክላው አጋማሽ ጠርዝ አካባቢ የሚታየው ንቃት (ስንጥቅ) ሥራው በሁለት ምዕራፍ እንደተጠናቀቀ ያሳየናል። የታችኛው ግማሽ አካል ጠፈፍ ካለ በኋላ የላይኛውን ግማሽ አካልና አንገት ቀጥሎ የመሥራት ዘዴ ያረፈበት ወይም በተቃራኒው ማለት ነው።

የውጪው አካል ሽፋን (ቅብ)፣ ጥቁርና ግርማ ሞገስ የተሞላ አንፀባራቂ መሆኑ፣ ትክክለኛ የኢትዮጵያ ሸክላ ሥራ ባህሪን ያሳያል። የዚህ ቅብና ማስዋብ ሥራ ሂደት በማልበስ፣ ቅባት በመቀባት፣ በማለስለስና በማጥቆር በመሳሰሉ የሸክላ ሥራ ተከታታይ ተግባራት የሚከናወን ሲሆን ማጥቆሩ ሸክላው ከተቃጠለ በኋላ ሳይበርድ በሳር ወይም ስጋቱራ በመሸፈንና በገለቱ የሚፈጠረውን ጭስ እንዲጠግብ (በዋነኝነት የተቃ ጠለው ካርበን ከአፈሩ ጋር የመዋሃድ ሁኔታ እንዲፈጠር) በማድረግ ይከናወናል። የጠጠር ጉር ክብ የቀብር ክፍል በአማካኝ 9.6 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን፣ ክብደት መሸከም በሚችል የድንጋይ ግንባታ ጥበብ የታነፀና መተላለፊያ ኮሪደር ያለው ነው። ቢያንስ 20 የተለያዩ የመቃብር ቦታዎች በክፍሉ ውስጥ የተገኙ ሲሆን ሁሉም በሁለት የተለዩ መቃብሮች ዙሪያ ጥምጥም የተመሰረቱ ናቸው።

በክፍሉ ውስጥ ከ70 በላይ የሸክላ ዕቃዎች በሙሉ ገጽታቸው ወይም ተሰብረው የተገኙ ሲሆን አንዳንዶች በሰዎች አፅም አካባቢ፣ አንዳንዶቹ በክፍሉ ግድግዳ ዙሪያ፣ አብዛኞቹ ግን በዋናው መግቢያ ግራ ቀኝ የተቀመጡ ነበሩ።

ይህ ሸክላ ከሌሎች የተለየ የጌጣጌጥ ቅርጽ የተላበሰ አይደለም ነገር ግን እንደሌሎቹ የተለያዩ ረቂቅ የመስመር ንድፎችና ቅርጾች አሉት። የሆነው ሆኖ ልዩና ድንቅ ስብስብ ከሚባሉ ቅርሶች ተርታ የሚመደብና የወቅቱን ዕደ-ጥበብ ችሎታ አመላካች ነው። ከዛ ባለፈ ግን በቀብር ሥነሥርዓት ሂደት ውስጥ በመገኘቱና ለፈሳሽ ነገሮች ማቅረቢያ ወይም መጠቀሚያ አገልግሎት ብቻ የተወሰነ ከመሆኑ አንጻር ሁሉንም የቤት ውስጥ መገልገያ ሸክላ ዕቃዎችን ሊወክል አይችልም። እነዚህ ሸክላ ቅሪቶች የሞቱት ሰዎች ንብረት ሳይሆኑ እንደማይቀር የሚያሳዩ፣ ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ እንደዋሉና አገልግሎት ይሰጡ እንደነበር የሚጠቁሙ የመሸራረፍና የመጋጋጥ ፀይነት አሻራ አለባቸው።

ከብዙ የሸክላ ዕቃዎች ባለፈ፣ ይህ የመቃብር ቦታ በሌሎችም ቁሶች ብዝሃነት ለየት ያለ ነው። በመቶዎች የሚቆጠሩና ከጨርቃ ጨርቅ በተሰሩ ክሮች የተሰካኩ መስታወት ጨሌዎች (ምናልባትም የአንገትና እጅ ጌጦች)፣ 52 የብረት፣ የመዳብና ብር አምባሮች፣ በከፊል ከከበሩ ድንጋዮች የተሰሩ ጌጦች፣ እጀታው ከዝሆን ጥርስ እንደተሰራ የተገመተ አነስተኛ የብረት ጦር፣ እንዲሁም ሌሎች ቅሪተ-አካላት በቦታው ተገኝተዋል። ይህም ባለፀጋና ከሩቅ አካባቢዎች ጋር የንግድ ልውውጥ የነበረው ማህበረሰብ በዚያ እንደነበረ አመላካች ነው።

ይህ በተለያዩ የቀብር ቦታዎች ላይ የተስተዋለው ልዩ ባለጠርዝ የሸክላ ውጤት በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢ ከ10ኛ-14ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የዕደ-ጥበብ ውጤት ነው። ይህን መሰሉ የሸክላ ሥራ ውጤት ከ13ኛ-15ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ባለው ጊዜ ውስጥ የቆመ ከመሆኑ የተነሣ ምናልባትም ያን ተከትሎ የባህልና አስተዳደራዊ ሽግግር ወይም ለውጥ እንደተከሰተ አመላካች ነው። ■ [አ.ሲ. ጉ፣ በ. ፖ]



**ባለ-ዳሌ ገንቦ፤ የሻይ ባህል** 17

10ኛው መቶ ክ.ዘ

ሸክላ፤ ቁ. 15 ሳሜ፤ ወ. 28.5 ሳሜ፤ የአፋ ወ. 7.5 ሳሜ

ጠጠር ጉር፤ ኮድ Inv. 7005-142a

## ጨሌዎች (ዶቃዎች) ከመንዝና ጨርጨር
## 10ኛ-12ኛው መቶ ክ.ዘ

ጨሌዎች ከጥንታዊውና ከመካከለኛው ዘመን ቅሪተ-አካል ጥናት ቦታዎች የተገኙ ውድና ታሪካዊ ቅርሶች ናቸው። በሁሉም የባህልና ሐይማኖታዊ አውዶች ውስጥ ይገኛሉ፤ ይህም ማለት ከክርስትና፣ እስልምና እንዲሁም በድንጋይ ጥበብ ከበለፀጉ ወይም ከአብርሐማዊ እምነቶች ውጪ ከሆኑ ማህበረሰቦች ጋር የተያያዘ ታሪክ አላቸው። ከኋለኛው ማህበረሰብ አንጻር ሁለት የክምር ድንጋይ ጥናታዊ ቦታዎች ልዩና ትኩረት የሚስቡ ናቸው። አንደኛው በመካከለኛው ኢትዮጵያ የሻይ ባህል አካል የሆነው ጠጠር ጉር ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከሐረር፣ ጨርጨር አካባቢ ከሚገኙ የራሬ እና ጋንዳ-ሚጁ መካነ-መቃብር ስፍራዎች ጋር ይገናኛል። እነዚህ ሁለት ቦታዎች በመካከላቸው ወደ 200 ማይልስ (20 ኪ.ሜ) ርቀት ቢኖራ ቸውም በተመሳሳይ ዘመን የኖሩ አንድ ዐይነት የመቃብር ስፍራ አስተ ናነፅና ቁሳዊ ባህል የነበራቸው መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል።

ጠጠር ጉር መካነ-መቃብር ብዛት ያላቸው ቁሶች ተከማችተው የተገ ኙበት ነው። በተለይም ጨሌዎች። ከ25 ዓመታት በፊት የቅሪተ-አካል ጥናት የተከናወነበትና ዕድሜውም ከ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሚጀምር ታውቋል። በዚህ ስፍራ የተገኙ ጨሌዎች አነስተኛ መጠን (2 ሚሜ) ያላቸውና የኢንዶ-ፓሲፊክ ጨሌ አሰራር ጥበብን የተላበሱ ሆነው ተለይተዋል።

የአሰራር ዘዴዎቹ፣ አንደኛ፣ ዝርግና የተቆራረጠ ቅርጽ ያላቸው ጨሌዎች፣ የቀለጠውን መስታወት በመሳብ የተመረቱ፣ የተቆራረጠ ቅርጽ ያላቸውን ጨሌዎች ለመፍጠር በመሳብ የተዘጋጁ የተለያዩ ትንንሽ መስታወት ቱቦዎችን ዳግም ሙቀት በመስጠት ቅርፀ-አካል ተጠቅመው የሰሯቸው እንደሆነ ይጠበቃል።

ሌላኛው ዘዴ ጥምዝ ጨሌዎችን ለማዘጋጀት፣ የሞቀውን መስታወት ቱቦ በማጠፍና በተመሳሳይ መጠን በመጠቅለል መሥራትን ያማከለ ነው። የተለያዩ ወጥ ቀለማት የያዙ ጨሌዎች የተገኙ ሲሆን፣ ሰማያዊ፣ ቢጫ፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ብርቱካናማ፣ ነጭ፣ ግራጫና አረንጓዴ ይጠቀሳሉ። አብዛኞቹ ጣሳ መሰል (cylinderical) ሲሆኑ በጣም ጥቂቶቹ ክብና የወይን በርሜል ቅርጽ ያላቸው ናቸው። የተቆራረጠ ቅርጽ ያላቸው ጨሌዎች በአብዝሃኛው አንድ ቀለም የተላበሱ (ሰማያዊ፣ ሐምራዊ ወይም ቢጫ)፣ ሌሎች ግን ውስብስብ አሰራር ሂደትን የሚወክሉ አንዳ ንዶችም በቀለጠውና ተጣርቶ ንፁህ በሆነው መስታወት ላይ ወርቅ ወይም ብር ማዕድን በመጨመር የተሰሩ ናቸው። ጥቂት ጨሌዎች ሞገድ መሰል ቀለማት አላቸው ለምሳሌም በሰማያዊ ገፅታ ላይ የተቀመጡ ነጭ መስመሮች፣ ጥምዝ ጨሌ ላይ፣ ክር መሳይ ቀጭን ቀይ ቀለምና፣ ሹል ጫፍ ይታያል፤ ይህም ጨሌው በሚሰራበት ወቅት ድንገት የተፈጠረ ገፅታ መሆኑን መገመት ይቻላል። ከመካከላቸው አንድ ጨሌ ቢጫ፣ ቀይ፣ ነጭና ሰማያዊ ቀለማትን የተላበሰና የደመቀ ነው። ሌላው በጠጠር ጉር ከተገኙት ጨሌዎች ውስጥ ከተለያዩ ድንጋዮችም የተሰሩ ይገኙባቸዋል። ከነዚህም ውስጥ ከካርኔሊያን (carnelian)፣ ከሳርዶንይካስ (sardonyx)፣ ካልታወቀ አረንጓዴ ድንጋይ፣ አማዞኒት (amazonite) እና ምናልባትም ከጃድ (jade) እንደተሰሩ ይገመታል። ከመስታወት፣ ከጃድና ካርኔሊያን ድንጋዮች የተሰሩ ጨሌዎች እንደመገ በያያነት ሳያገለግሉ እንዳልቀረ ይገመታል።

የራሬና ጋንዳ ሚጁ የመቃብር ቦታዎች በ1970ዎቹ ዓመታት የቅሪተ-አካል ጥናት የተደረገባቸው ሲሆን ከ10ኛ-12ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ተዘግቧል። በዚህ ቦታ ከ200 በላይ የመስታወት ጨሌዎች የተገኙ ሲሆን ቢጫ ወይም ሰማያዊ ቀለም የተረጨባቸው የሚመስሉ ጥቂት አሉ። ከመዳብና ከብረት የተሰሩ ጨሌዎችም በዚህ ቦታ ተገኝተዋል። አንዳንድ ከወርቅ የተሰሩ በሌላ በኩል ደግሞ ተመሳስለው ከአሸዋማ ድንጋይ የተሰሩ ጨሌዎች አሉ። ከጨሌዎቹ ደህንነት አንጻር ይህ ሁኔታ ግልፅ ያልሆነ እይታ እንዲኖር ሆን ተብሎ የተፈጠረ ማመሳሰል ወይም መሰል ጨሌዎችን የማባዛት ሁኔታ እንደሆነ ይታሰባል።

በሻይም ሆነ ጨርጨር ማህበረሰብ ውስጥ ከተገኙት ጨሌዎች ውስጥ፣ ከውጭ የገቡና ከመስታወት የተሰሩት ከብረቶቹና ድንጋዮቹ በተለየ የተመራማሪዎችን ቀልብ የሳቡ ነበሩ። በዚህም በጠጠር ጉርና አጎራባች መሻለ ማርያም ከተገኙት ጨሌዎች ውስጥ በ34ቱ ላይ ጥናት ያደረጉ ሲሆን ሶርያ፣ ኢራን፣ ኢራቅ፣ ግብፅና ፍልስጤም እነዚህ ጨሌዎች የተሰሩባቸው ሀገራት እንደሆኑ ይጠቁማሉ። ይህም በዓለም



**ጨሌዎች (ዶቃዎች)** 18

10ኛ-12ኛው መቶ ክ.ዘ

ከመስታወት የተሰሩ፣ የተለያየ መጠን ያላቸው

ጠጠር ጉር



ዓቀፍ የግግድ እንቅስቃሴና የህዝቦች ባህላዊ ትስሥር ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ መረጃ ሊሆን ችሏል። አፍሪካም ለጨሌ አምራች ሀገራት የገበያ ማዕከል እንደነበረች አስገንዝቧል።

በጠቅላላው በሻይና ጨርጨር ክምር ድንጋዮች የተሰበሰቡ ጨሌዎች በወቅቱ ለነበረው ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ እድገት ወይም አቅም እንዲሁም ባለፀጋ አስተዳደር እንደነበር ምስክር ናቸው። ከዛ በተጨማሪ በሌሎች ክልሎች ለሚደረጉ ንግድ ልውውጦች ይህ ማህበ ረሰብ ዋና አገናኝና ማዕከል እንደነበረ መገመት ያስችላል። በሌላ በኩል የሜድትራንያንና መካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች የገበያ ኢላማ ከነበሩት የአፍሪካ ቀንድ አካባቢዎች ውስጥ እነዚህ ሁለት ቦታዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሌላው ጉዳይ በስምጥ ሸለቆ ግራና ቀኝ የነበሩ የግዙፍ ድንጋይ ጠበብት ህዝቦች የዚህ ንግድ ቀጠናና ዱካ ተጋሪ እንደነበሩ በመሰል ቅሪቶች መረዳት ይቻላል። ስለሆነም ጨሌዎች እንደሌሎች ጥንታዊ ቁሶች ምናልባትም በበለጠ ሁኔታ የገበያ ፍላጎት እንደነበሩና በመካከለኛው ዘመን ውስጥ በአፍሪካ ቀንድ የነበረውን የንግድ ልውውጥ ለመረዳት ቁልፍ ደጋፊ መሳሪያዎች እንደሆኑ መናገር ይቻላል። ■ [አ. በ]



**ጨሌዎች (ዶቃዎች)** 18

10ኛ-12ኛው መቶ ክ.ዘ

ከመስታወት የተሰሩ፣ የተለያየ መጠን ያላቸው

ጠጠር ጉር፣ lot n° 3


# የአርኪኦሎጂ ሳይንስ

**አርኪኦሎጂ (ሥነ-ቅርስ)**፣ ስለ ቀደምት ማህበረሰብ ታሪክና አኗኗር ወቅቱን ያገናዘቡ ዘዴዎችንና አመላካች ዱካዎችን መሰረት በማድረግ የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ ነው። የአርኪኦሎጂ ጥናት ዘርፍ ከተለያዩ የሞያ ስብጥሮች ጋር የተጣመረና የብዙ ጠበብቶች ድምር ተግባር ነው።

የአርኪኦሎጂ ባለሞያዎች የቅሪተ-አካል ቁፋሮ በማከናወን ቀደምት መኖሪያ ወይም ማረፊያ አካባቢዎችን ግልፅ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። ይህም ሲሆን ስለአካባቢው መረጃ ከመሰብሰብ ጀምሮ በቁፋሮ የሚገኙ ማናቸውንም ቁሳቁሶችና ቅርሶች አቀማመጥና ቦታ ብሎም የደበቃቸውን ነገር ተፈጥሮና ይዘት ለመለየት ይሞክራሉ፤ ግኝቶቹንም ለማደራጀት፣ ለመጠገንና በቂ ጥናት ለማድረግ ረጅም ጊዜያቶችን በቤተ-ሙከራዎች ያሳልፋሉ። በአርኪኦሎጂ ጥናት ውስጥ የሚሰበሰቡ ቁሳቁሶች ጥንታዊውን ሁኔታ ለመረዳት ከሚያግዙ አመላካች ዱካዎች ውስጥ ተጠቃሽ ሲሆኑ ከመሬት ሥነ-ንብብሮሽ፣ የግንባታ ዘዴዎች፣ ከመኖሪያ ወይም የመቃብር ቦታ እንዲሁም ከሰውና እንስሳት ቅሪት አካል ጋር ተዛማጅነት ሲኖራቸው ታሪካዊ ፋይዳቸው የጎላ ነው።

ቅሪተ-አካል ስብስቦች እንደተፈጥሮአዊ ባህሪያቸው ወይም እንደተመረቱበት ጥሬ ዕቃ ይለያያሉ፤ በዚህም ምክንያት ለምሳሌ ድንጋይ ወይም ባልጩት፣ ሸክላ ወይም ብረት ቢሆኑ፣ በዘርፋ በቂ ዕውቀት ባካበቱ ተመራማሪዎች ጥናት ይከናወንባቸዋል። ይህም በመሆኑ የተመራማሪዎች ጥናት ለምሳሌ በጨሌዎችና ከሌላ ሀገር በገቡ የሸክላ ውጤት ስብስቦች፣ ወይም በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ብቻ ሊያተኩር ይችላል። በቁፋሮ የሚገኙ ቅሪተ-አካላት በምን ዐይነት ሁኔታና በየትኛው የመሬት ንብብሮሽ ክፍል እንደነበሩ፤ የእነዚህ ቁሳቁሶች አሰራር ዘዴና ዐይነት፤ ብሎም በዚህ ዘመን አለ ወይስ ጠፍቷል? ግኝቶቹ ጥቅም ላይ ለመዋላቸው አመላካች አሻራዎችን ይዘዋል? ከሆነስ ለዕለት ከዕለት ኑሮ ወይስ ለተለየ ሥርዓታዊ ጉዳይ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳትና ምላሽ በመፈለግ መረጃ ማጠናቀርን ጨምሮ፣ የዘመን ልኬት ሊደረግባቸው የሚገቡ ናሙናዎችን የማዘጋጀቱ ተግባራት የዘርፋ ተመራማሪዎች የቤት ሥራ ነው። ከዚህ በተጓዳኝ ጥንታዊው ማህበረሰብ ይገለገልባቸው የነበሩ ቁሳቁሶችን አሰራር ዘዴ ከአሁኑ ዘመን እውቀትና አሰራር ዘዴ ጋር በማነፃፀር ለማጥናት የማህበረሰብ ተኮር አርኪኦሎጂ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህም ከጥሬ ዕቃ ጀምሮ፣ ሙሉውን የአሰራር ሰንሰለት የማጥናት ሂደት ነው። ይህን መሰሉ የጥናት ዘርፍ የአሁን ጊዜ ዘዴዎችንና ግብዓቶችን መሰረት በማድረግ፣ ጥንት የነበረውን መፈተሽ ከማስቻሉ ባሻገር ለማህበረሰቡና ዕሴቶቹ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖር ያስችላል። ከዘርፋ ጥናት ጋር በተያያዘ የድንጋይ፣ የሸክላና ብረታ-ብረት ውጤቶች ዘመን ተሻጋሪ ሲሆኑ፣ በዚህ ዓምድ ሥር ሶስቱንም ከምርት፣ ግብዓትና ማስፈፀሚያ ዘዴዎች አንጻር በአጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል። ■

በላሊበላ፣ ቀዩት ተራራ ስነ-ቅርስ ስፍራ፣ ስስነ-ንብብሮሽ አመላካች፣ የፎቶ ላይ ንድፍ፤ እ.ኤ.አ 2019 ዓ.ም ሥነ-ንብብሮሽ በዘመናት የተፈጠሩ የድንጋይ፣ አፈርና ሌሎች ክምችቶችን ይመረምራል፣ ይህም በተለያየ ዘመን ውስጥ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማጥናት ይረዳል።



## የድንጋይ ሥነ-ጥበብ

የብዙ ታሪክና ባህላዊ ቅርስ ባለቤት የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከምትታወቅበት አንዱ ቅርስ የድንጋይ ሥነ-ጥበብ ነው። ይህ ሥነ-ጥበብ የአገሪቱን ጥንታዊ የዕድገት ደረጃ፣ ሐይማኖትና ሀገር በቀል እውቀት ብሎም ቁስን ወደ ግብዓት የመለወጥ ችሎታ ያሳያል። ከቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ-ክርስቲያናት እስከ ጥንታዊው የአክሱም ሐውልት ያሉ የድንጋይ ሥነ-ጥበብ ውጤቶች የህዝቡን የፈጠራ ጥበብ፣ መንፈሳዊና አካላዊ ጥንካሬን ይዘክራሉ።

በኢትዮጵያ ያለው የድንጋይ ሥነ-ጥበብ ጥንታዊና ረቂቅ ነው፤ ለዚህም የአክሱም ማህበረሰብ የተዋጣለትና በክህሎት የዳበረ እንደነበር፣ ሾጣጣና ባለብዙ ደረጃ ሆነው የተወቀሩ፣ እንዲሁም በበርና መስኮቶች ንድፍ የታጀቡት የግራናይት ድንጋይ ሐውልቶች ምስክር ናቸው። ጠንካራና ለዐይን ማራኪ የሆነው ግራጫ ግራናይት ድንጋይ መገኛ ቦታ ወይም ካባ ቅርበት ቢያንስ የማጓጓዝ ሁኔታውን አቅሎታል ብሎ መናገር ይቻል ይሆናል። ይሁንና ድንጋዩን ከአለቱ የመነጠሉ ተግባር ውስብ ስብና ከፍተኛ የሰው ሐይልን የሚጠይቅ፣ ተፈላጊውን የድንጋይ መጠን ከዓለቱ ለመለየት ደግሞ ተፈጥሯዊ የሆኑ ወይም በጊዜ ሂደት የመጡ ክፍተቶችን በመፈለግ አራት ማዕዘን ቀዳዳዎችን ፈጥሮ የዕንጨት ወይም የብረት ሽብልቆችን በማስገባት በሃይል መምታትን ይፈልጋል። የሚፈጠረውና የሚያርፍበት ኃይል ድንጋዩ ከአለቱ እንዲነጠል በር ይከፍታል። ከዚህ በኋላ ቅርጽ ማውጣትና ማምረት ሂደት የሚቀጥል ሲሆን የአክሱም ጠቢባን የብረት መሳሪያዎችን (እንደ መሮና መዶሻ ያሉ ነገሮች) በዚህ የሐውልት ሥራ ላይ እንደተጠቀሙ የአርኪኦሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህን ግዙፍ ሐውልት ማጓጓዙን በተመለከተ አክሱማውያን ልዩና የተራቀቁ ቁሳቁሶችንና ክህሎትን ተጠቅመዋል ብሎ መገመት ይቻላል፤ ጋሪ መሰል መጎተቻ፣ በርሜል መሰል ማንከባ ለያና ከፍተኛ የሰው ኃይል ተጠቃሽ ናቸው።


በኢትዮጵያ የድንጋይ-ሥነ-ጥበብ ሂደት ውስጥ የኦርቶዶክስ ሐይማኖት ሚና እንደነበረው በበርካታ አብያተ-ክርስቲያናትና ገዳማት ግንባታ ተስተ ውሏል። በአገሪቱ ድንጋይ ሥነ-ጥበብ ውስጥ ጉልህ ስኬቶች ተደርገው ከሚቆጠሩት ሥራዎች መካከል በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንጉሥ ላሊበላ የተሰሩት የላሊበላ ውቅር አብያተ-ክርስቲያናት ተጠቃሽ ሲሆኑ፣ ሥራዎቹ <<አዲሲቷ እየሩሳሌም>> በሚል ዕሳቤ የተገነቡና ከፍተኛ የዕደ-ጥበብ ሞያንና ከፍተኛ መሰጠትን ወይም የታማኝነት ደረጃን የሚያንፀባርቁ ናቸው። ለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስ ቲያን በጎ ተፅዕኖ ማሳያ ተደርገው ይቆጠራሉ። በስፍራው ያሉት 11 የተለያዩ ቤተ-ክርስቲያናት ልዩ የሥነ-ህንፃ ባህሪያት የተላበሱ ሲሆን፣ ውብና ጥልቅ ስዕላዊ ቅርጾችን ያካተቱ ናቸው። በመስቀል ቅርጽ ንድፍ የተገነባውና ለዘመናት በይዘቱ የዘለቀው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክር ስቲያን ለዚህ ተጠቃሽ ነው። በኢትዮጵያ የድንጋይ-ሥነ-ጥበብ ሂደት ውስጥ የኦርቶዶክስ ሐይማኖት ሚና እንደነበረው በበርካታ አብያተ-ክርስቲያናትና ገዳማት ግንባታ ተስተውሏል። በአገሪቱ ድንጋይ ሥነ-ጥበብ ውስጥ ጉልህ ስኬቶች ተደርገው ከሚቆጠሩት ሥራዎች መካከል በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንጉሥ ላሊበላ የተሰሩት የላሊበላ ውቅር አብያተ-ክርስቲያናት ተጠቃሽ ሲሆኑ፣ ሥራዎቹ <<አዲሲቷ እየሩ ሳሌም>> በሚል ዕሳቤ የተገነቡና ከፍተኛ የዕደ-ጥበብ ሞያንና ከፍተኛ መሰጠትን ወይም የታማኝነት ደረጃን የሚያንፀባርቁ ናቸው። ለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን በጎ ተፅዕኖ ማሳያ ተደርገው ይቆጠራሉ። በስፍራው ያሉት 11 የተለያዩ ቤተ-ክርስቲያናት ልዩ የሥነ-ህንፃ ባህሪያት የተላበሱ ሲሆን፣ ውብና ጥልቅ ስዕላዊ ቅርጾችን ያካተቱ ናቸው። በመስቀል ቅርጽ ንድፍ የተገነባውና ለዘመናት በይዘቱ የዘለቀው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ለዚህ ተጠቃሽ ነው።

በአካባቢው ያለው ድንጋይ ለግንባታ አመቺ የሆነና ግዙፍ የድንጋይ መጠንን በመለየት ግንባታ ማከናወን የሚቻል ቢሆንም በድርድር ድንጋይ የተሰራ ህንፃ የለም። የላሊበላ ቤተ-ክርስቲያናት ለዳገም ጥቅም ያልታሰቡ ቁርጥራጭ ድንጋዮችን በመፈልፈልና በማስወገድ የተሰሩ ሲሆኑ፣ በህን ፃዎቹ አካባቢ የቁርጥራጭ ድንጋዮች ክምችት ይስተዋላል። ይህ ክምችት የህንፃዎችን የተለያየ የግንባታ ሂደትና ደረጃ ለማጥናት ለአርኪኦሎጂ ባለሞያዎች ግብዓት ሁነው ያገለግላሉ። ከጥቂት ምንጫቸውና ጥቅማቸው ካልተለዩ የድንጋይ ህንፃዎች በስተቀር በአብዝኃኛው የኢትዮጵያ ደጋማና ከፍታ ቦታዎች የሚገኙ የድንጋይ ግንባታዎች በውል ካልታወቀ፣ እና ከ13ኛው መቶ ክ. ዘ በፊት ምናልባትም በዋሻዎች ውስጥ ይኖሩ ከነበሩ ማህበረሰቦች ጋር የተዛመደ መሠረት እን ከላሊበላ በተጨማሪ በትግራይ ተራራዎች የተመሰረቱት የደብረ ዳሞና ሌሎች ታዋቂ ውቅር

ኦብያተ-ክርስቲያናት የዘርፉ ሥነ-ጥበብ አካል ናቸው። እነዚህ ግንባታዎች ከአምልኮ ቦታነታቸው በዘለለ የጠንካራ ማህበረሰብ መገለጫ ብሎም ለውጫዊ ተፅዕኖ አይበገሬነት ማሳያ እንደሆኑ መናገር ይቻላል።

የኢትዮጵያ ከርሰ-ምድር ለሥነ-ጥበቡ ብዝሃነት የግብዓት ምንጭ በመሆን አስተዋፅኦ ሲያበረክት ባለሞያዎችም አካባቢው ያፈራውን የግራናይት፣ ባዛልትና አሸዋማ ድንጋዮችን ወደ ዘላቂ ምርት ከመቀየር አልፎ ከመልከዐ-ምድሩ ጋር የተወዳጀ ውበት እንዲላበስ አስችለ ውታል። ይሁንና የኢትዮጵያ የድንጋይ ሥነ-ጥበብ ውጤት፣ ከታሪካዊው ታላቅነት በተቃራኒ የተለያዩ ተግዳሮቶችንም እያስተናገደ እንዳለ ሳይጠቀስ አያልፍም። ይህም ተፈጥሮአዊ፣ አካባቢያዊ፣ የመኖሪያ መንደሮች መስፋፋት፣ የከተሞች እድገት እንዲሁም የቱሪዝም እንቅስቃሴ ተጠቃሽ ናቸው። ችግሮችን ለመቅረፍና ቅርሶቹን ለመጠበቅ መልሶ ማቋቋምን መሰረት ያደረጉ የጥገና ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ የቅርስ ቦታዎች ሁነው እንዲለዩና የደህንነት ሽፋን እንዲያገኙ የሚወሰዱት እርምጃዎች ተጠቃሽ የመፍትሄ እንቅስቃሴዎች ሲሆኑ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እንመክራለን። ■ [አ. ጋ]

ከበሀ ድንጋይ የተቀረጹ፣ ሰው መሰል ትክል ድንጋዮች አናት፤ ሲዳማ አካባቢ፣ ያልታወቀ ቦታ፤ ኮድ JE 001 እና JE 002፤ እ.ኤ.አ 1953 ዓ.ም



## የሸክላ ሥነ-ጥበብ

የሸክላ ዕቃ ግብዓቶች የተላበሱት ተለዋዋጭ ባህሪ፣ በተፈለገው ቅርፅና መጠን እንዲዘጋጁ ምቹ ያደርጋቸዋል፤ በተጨማሪ በቀላሉ የሚለ ጠጡና በሚደርቁበት ወቅትም ጥንካሬያቸው እየጨመረ የመሄድ ባህሪን የተላበሱ ናቸው። ከዚህም የተነሣ በሸክላ ጥበብ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ የሙቀት መጠንን መፍጠርና ጠንካራ ምርትን ማውጣት (ቢያንስ 600 °ሴ የሙቀት መጠን) ቁልፍ የዕድገት ደረጃ እንደሆነ ይታሰባል። የሸክላ ውጤቶች ብዙ ሁኔታን የሚቋቋሙ፣ ፈሳሽም ይሁን ጠጣር ነገሮችን መያዝ የሚችሉ፣ እና ሙቀት የሚያስተላልፉ ናቸው። ከነዚህ ባህሪያት የተነሣ ለምግብ ማብሰያ፣ የተለያዩ ውህዶችን ለማብ ላያና ለረጅም ጊዜ ለማቆያ ወይም ለማጠራቀሚያነት ተፈላጊ ናቸው። በተጨማሪ ሸክላ፣ ለማሞቂያ ማሽን፣ ለምድጃ፣ ለጣራ ክዳን፣ ለተለያዩ ቱቦዎችና ሌሎች ቁሶች መስሪያ ጥቅም ይሰጣል።

የሸክላ እቃዎች ምርት በየትኛውም ማህበረሰብ ክፍል ውስጥ ተመሳሳይ በሆነ ደረጃ፣ የተለያዩ የአሰራር ሰንሰለቶችን ይከተላል፣ እነዚህም የሸክላ ግብዓቶችን ማሰባሰብ እና ማሰናዳት፣ መቅረጽ (ቡኮውን ማዘጋጀት፣ በሚፈለገው ቅርጽ መሥራት እና ማጠናቀቅን ጨምሮ)፣ ውጫዊውን ሽፋን ማስተካከል ወይም ማለስለስ፣ ማስጌጥ እና ማቃጠልን ያካትታል። እያንዳንዳቸው እነዚህ ደረጃዎች የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም ሊከናወኑ ይችላሉ፣ እና እነዚህን ቴክኒኮችን ለመተግበር የሚያገለግሉ ብዛት ያላቸው ደጋፊ ቁሶችና ሂደቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ስለዚህ፣ የሸክላ እቃዎች የዘርፉ ባለሞያዎችን ክህሎትና ባህላዊ ልማዶችን ይገልጻሉ። የአርኪኦሎጂ ተመራማሪዎች የጥናቶቻቸው ማዕከል

የሆኑትን ማህበረሰቦች በተሻለ ለመረዳት፣ በጥናት ወቅት የሚገኙትን የሸክላ እቃዎች ቅርጽ እና ተግባር እንዲሁም የተጠቀሙትን ቴክኖሎጂ ለመለየት ይሞክራሉ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት 5ኛው ሺህ ዓመት ጀምሮ በኢትዮጵያ እንደነበሩ የሚገመቱት የሸክላ ውጤቶች በታሪካዊ ቦታዎች ውስጥ በጣም በብዛት የሚገኙ ዕቃዎች ናቸው። የሸክላ ዕቃዎች ተሰባሪ በመሆናቸው፣ ሊደቁ ወይም ሊጎዱ፣ በተፈጥሮ ክሥተት ስፍራቸውን ሊለቁ፣ እንዲያውም ሊጠፉ ይችላሉ። በጥናታዊው ቁፋሮ ዘዴና ሂደት፣ እንዲሁም በመሬቱ ንብብሮሽ ዐውድ ወይም ደረጃ መሰረት ጥቂት ወይም በሺህ የሚቆጠሩ የሸክላ ስባሪዎች ሊገኙ ይችላሉ። ያልተሰበሩ ወይም ጉዳት ያልደረሰባቸው ሸክላ ዕቃዎች ሊገኙ ወይም የዘርፉ ባለሞያዎች ስባሪዎችን በመገጣጠምና በማጣበቅ ቀድሞ የነበራቸውን ቅርጽ እንዲይዙ የማድረግ ሥራን ይሰራሉ። የሸክላ ቅሪቶችን መረጃ በጥንቃቄ በማጠናቀር እና ግኝቶችን በማነፃፀር፣ የዕቃውን ዕድሜ ቅደም ተከተል፣ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲሁም የቴክኖሎጂ መረጃዎችን መገንዘብ ይቻላል።

የአርኪኦሎጂ ምርምር ሂደቱ፣ በጥንቃቄ ከመሬት አፈር መነጠል እንዲሁም የተገኘበትን ቦታ መለያና ምልክት ማድረግን ያካትታል፣ ይህም ከጥናቱ ጋር የተያያዙትን መረጃዎች በደንብ ለመጠበቅ ይረዳል። ከዚያም የተገኙ የሸክላ ስብስቦችን በላብራቶሪ ውስጥ፣ በአርኪኦሎጂያዊ አውድ ወይም የመሬት ንብብሮሽ፣ በጥናቱ ዓላማና ቦታ ወይም በተመረቱበት ዘዴ ይሁን በዐይነታቸው እንዲለዩ ይደረጋል። የስብስቦቹ ብዛት በተገኙበት ዐውድ መለየት ይኖርበታል፣ ይህም ቦታው በተለያየ ጊዜያት ወይም ዘመናት ጥቅም ላይ ለመዋሉ መረጃ ለማጠናቀር ይረዳል። ዋና ዋና የሆኑና ለጥናቱ ጠቀሜታ የሚኖራቸው ዕቃዎች ወይም ስባሪዎችን ንድፍና ፎቶ በማካተት ከበቂ ዝርዝር መረጃ ጋር ማዘጋጀትም ያስፈልጋል። የአንድን ዕቃ ጠርዝ፣ እግር፣ እጅ ወይም የጌጣጌጥ ክፍሎችን የያዙ ሸክላ ስባሪዎች የምርምር አካል በመሆን የሸክላ እቃውን ዐይነት እና የጌጥጣጌጥ ንድፎችን ለመለየት ጠቃሚ ናቸው። የሸክላ እቃዎችን ዐይነትና አሰራር መለየት፣ ከመሰል ምርቶች ጋር ለማነፃፀርና ዐይነታዊ የዕድሜ ቅደም ተከተል ለመወሰን ይረዳል፤ ምክንያቱ ደግሞ የተወሰኑ ቅርጾች የተወሰነ ዘመን ልማድን ሊያመለክቱ የሚችሉበት አግባብ ስላለ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የባህል እና የኢኮኖሚ ልውውጦችን ጠቋሚ በመሆን መረጃ ይሰጣል፣ እንዲሁም ዕቃዎቹን በመጠቀም ሂደት ውስጥ በላያቸው ላይ የቀሩትን ንጥረ ነገሮች በመመርመር ስለ ተግባራቸው በትክክል መረዳት ይቻላል።■ [አ.ሊ.ጉ]

## የብረታ-ብረት ሥነ-ጥበብ

ብረት ማውጣት ወይም ማንጠር በሰው ልጅ ታሪክ ልዩ ቦታ ከሚይዙ የፈጠራ ውጤቶች ውስጥ ይመደባል፣ ምክንያቱ ደግሞ በተፈጥሮ ውስጥ የማይገኝ ባህሪያት ያላቸውን ምርት ስለሚፈጥር ነው። ብረቶች፣ የማይዝጉም (ወርቅ፣ ብር፣ መዳብ፣ ነሐስ) ሆነ የሚዝጉ (ብረት፣ ዐረብ ብረት (steel)፣ ጊዛ ብረት (cast iron)) በአብዛኃኛው ጠንካራ፣ ብርሐን የማያስተላልፉ፣ አንፀባራቂ ቀለም ያላቸውና ሙቀት ማስተላለፍ የሚችሉ ናቸው። ብረቶች እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም ዳግም ምርት ሊሰጡ የሚችሉ ማዕድን ናቸው። የብረት ምርት ረጅም የሆነ የሥራ ሂደት ይፈልጋል፣ በዚህ ውስጥም የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች የአካል እና የኬሚካል ውህድ በመፍጠር ወደተለየ ቁስና ይዘት የመለወጥ ሁኔታን ያሳልፋሉ። አንጥረኞች የብረት ቅንጣቶችን ከኦክሲጅን አተሞች እና ከብረት አለቶች ውስጥ ካሉ ሌሎች ንጥረ ነገሮች መለየት አለባቸው። ይህ ለውጥ በጣም ከፍተኛ ሙቀት ይፈልጋል (ለብር ከ950°ሴ በላይ፣ ለወርቅ እና ነሐስ በ1100°ሴ፣ ለብረት ከ1100-1500°ሴ)።

አንጥረኞች፣ የማቅለጫ ስፍራን ካዘጋጁ በኋላ የብረት ዐለት እና ከሰል ወደ ማቅለጫው በማስገባት ካቀጣጠሉ በኋላ አየር በማስገባት ሙቀቱ ከፍ እንዲልና ዐለቱ እንዲቀልጥ፤ ብረቱም ከተቀረው ዝቃጭ እንዲለይ ያደርጋሉ። ከዚህ በኋላ የተለያዩ መገልገያዎችን ያዘጋጃሉ፤ ከማይዝገው የብረት ዐይነት ቅርጽ ማውጫዎችን በመጠቀም መቆፈሪያ፣ ቀለበትና ሳንቲም የመሳሰሉ እንዲሁም ከሚዝገው የብረት ክፍል ዳግም ሙቀት በመስጠትና በመቀጥቀጥ ቢላዋ፣ ቀስትና ሌሎች ዕቃዎችን ያዘጋጃሉ። የተለያዩ ብረቶች ከባህሪያቸው አንጻር በእለት ከእለት ኑሮ ውስጥ ለሚያስፈልጉ ማናቸውም መገልገያዎች መስሪያነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ለምሳሌም ለእርሻ፣ ለአደ ጥበብ፣ ለጦር መሣሪያ፣ ለጌጣጌጥ እና ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ መገልገያዎች ይጠቀሳሉ። ከብረት ማዕድን ግኝት መባቻ ጀምሮ፣ አንጥረኞችና የዘርፉ ባለሞያዎች የተለያዩ የብረት ውህዶችን

በመፍጠር፣ የምርት ቴክኒኮቻቸውን በማሳደግ እና የየራሳቸውን የፈጠራ ውጤቶች በማምረት ለተገልጋዩ ማህበረሰብ ማቅረባቸውን ቀጥለዋል። የብረት ምርትና ዕደ-ጥበብ ምርምር በታሪክ እና በግዛቶች ውስጥ የብረት ማዕድን መገኛ ቦታዎችን፣ የዘርፉ ጥበብ ባለሞያዎችን ወይም አንጥረኞችን መሰረት በማድረግ የሚከናወን፣ በተጓዳኝም አዳዲስ ፈጠራዎችን፣ የምርትና ቴክኖሎጂ ለውጦችን፣ እና የምርት ሥርጭትን ለመገንዘብና ለመከታተል ይረዳል። በማህበረሰብ ደረጃም፣ የማምረት አቅም፣ ምርትን ጥቅም ላይ ማዋልና የጊዜ ቅደም ተከተል፣ የምርትና ቴክኖሎጂ ሽግግር የመሳሰሉ መረጃዎችን ለማጠናቀር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

በአፍሪካ አህጉር የብረታ-ብረት ልማትና አጠቃቀም በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ በተለያዩ መንገዶችና ጊዜያት የተከሰተ ነው። በአህጉሪቱ የብረታ-ብረት ታሪክ በዩሬሲያ ከታየው የዝግመተ ለውጥ ግንዛቤና (evolutionary perception) (ማህበረሰቡን በመዳብ፣ በነሐስ እና በብረት ዘመን ውስጥ መመደብ) ከቴክኖሎጂ ውሳኔ (technological determinism) ዕሳቤ የተለየ ነው። ይሁንና የተኩረት አቅጣጫ ከሆኑት የብረት ዐይነቶችና የቴክኖሎጂው ምደባ አንጻር አፍሪካ ወደ ሦስት የተለያዩ ታሪካዊ ክልሎች ሊከፈል ይችላል። ከነዚህም መካከል የመጀመሪያው ሰሜን አፍሪካ ነው፤ እሱም ከሜዲትራኒያን እስከ ቀይ ባህር ዳርቻ ያለውን አካባቢ የሚሸፍን፤ ከዕድሜ አንጻር ዘግይቶ የጀመረ ቢሆንም፣ ከአውሮፓ እና እስያ ሀገራት ጋር ተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት አምስተኛው ሺህ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ የብረት ማዕድናትን ጥቅም ላይ የማዋል እንቅስቃሴ ነበር፤ በመጀመሪያም ሀገር በቀል የሆኑ ብረቶችን (ወርቅ፣ ብር፣ ነሐስ፣ የሜትዮራይት ብረት፤ የሜትዮራይት ብረት በግብጽ ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል) በመጠቀም ጀምረዋል። ከዚያም መዳብ ያመርቱበት የነበረውን ማብላያ ወደ ብረት የማሳደግ እንቅስቃሴ አድርገዋል፤ ከዚህ በኋላ ከሦስተኛው ሺህ ዓመት ጀምሮ የመዳብ ቅይጦች የማዘጋጀቱ ተግባር ከፍተኛ ዕድገት ደረጃ ላይ ደርሷል። የንፁህ ብረት ምርት፣ ይህን ተከትሎ በአንደኛው ሺህ አጋማሽ የተከሰተ እንቅስቃሴ ነው።

ሁለተኛው ታሪካዊ ክልል፣ የሳሃሮ-ሳህሊያን አካባቢ (Saharo-Sahelian) ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት ባሉ የመጀመሪያው ሺህ ዓመታት በነሐስ እና ብረት ምርት የሚታወቅ፤ የተለያየ ባህል የተላበሱና በተመሳሳይ መልክዐ-ምድር ወይም ግዛት ውስጥ ይኖሩ በነበሩ ማህበረሰቦች ይገለፃል። የመጨረሻው፣ ከሳህሊያን በታች ያለው ክፍል (sub-Sahelian) ሲሆን የራሱ የሆነ የብረታ-ብረት ታሪክ ያለውና ከማይዝጉ ብረቶች ውጪ ባሉት ዐይነቶች ላይ ክህሎትን ያዳበረ ማህበረሰብ የተስተዋለበት አካባቢ ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ፣ የብረታ-ብረት ታሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት የመጀመሪያው ሺህ ዓመት ይጀምራል። ይህም የጌጣጌጥ ምርቶች ላይ የተወሰነና በሀገር ውስጥ የሚመረት ሳይሆን በዋነኝነት ከግብጽ፣ ኑቢያ እና አረቢያ ይገባ የነበረ ነው። ዕቃዎቹ በወቅቱ የነበረውን የሲራራ ንግድ እንቅስቃሴ እና ዓለም-ዓቀፍ ግንኙነቶች ያሳያሉ። ከክርስቶስ ልደት በኋላ የመጀመሪያው ሺህ ዓመት አጋማሽ ድረስ የአክሱማውያን ስልጣኔ የብረት ማምረት እንቅስቃሴ አልጀመረም። ከዛ በኋላ ግን የራሱን የብረት ምርት በመጀመር የተለያዩ ሳንቲሞች፣ ዕቃዎች እና መሳሪያዎችን ለመፍጠር ችሏል። ይሁንና ከላይ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ሂደቶች በአግባቡ ለመረዳት የሚያግዙ የቁሳቁስ ማስረጃዎች ግኝት በቂ አይደለም፤ ለምሳሌ የብረት ዝቃጮችና ማምረቻ ቦታዎችን መጥቀስ ይቻላል። ይህ ማለት ተጨማሪ ጥናቶችና አርኪኦሎጂካል ቁፋሮዎች ተጥናክረው ሊቀጥሉና በዘርፉ ያለውን የታሪክ ክፍተት ሊሸፍኑ እንደሚገባ ያመለክታል።

በመካከለኛ ዘመን፣ የጥንታዊ ብረታ-ብረት ጥናት (paleometallurgy) ትግበራ፣ ከሰሜን ኢትዮጵያ በዘለለ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች መስፋፋት ችሏል። በሁሉም ዐይነት ብረቶች መገልገያዎች ይመረቱ እና ጥቅም ላይ ይውሉ እንደነበር ሲታወቅ፤ ደቡባዊ ክልሎች ብር፣ ወርቅ እና ነሐስ ማዕድናት ስላልነበራቸው በብረት ላይ ጥገኛ ነበሩ። ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ፣ የብረት ዕደ-ጥበብና ምርት የተቀዛቀዘበት ወቅት ነው፤ ይህ ደግሞ ከምዕራባውያን የቅኝ ግዛት ኢኮኖሚና ፖለቲካ ፖሊሲ የመነጨ ተጽዕኖ እንደሆነ ተጠቁሟል። በተያያዘ ከውጭ ከሚገቡ ምርቶችና ጥሬ ዕቃዎች ጋር የነበረውን ውድድር መቋቋሙ አዳጋች ነበር፤ ቀስ በቀስም ክልከላዎችና ስም ማጥፋት ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ከዚህ የተነሳ ከማህበረሰቡ በተለየ አካባቢ የሚገኙና መገለል የሚደርስባቸውን አንጥረኞች መመልከቱ የተለመደ ነው። ■ [ካ. ሮ.ብ]

ማጠቃለያ

**ይህ ውብ መጽሐፍ** የኢትዮጵያን ረጅም ታሪክ ብቻ ሳይሆን፣ በኢትዮጵያውያን፣ ፈረንሳውያን እና ዓለም አቀፍ ምሁራንና ተመራማሪዎች መካከል የነበረውን ሳይንሳዊ ትብብር ብሎም የዕውቀት ልውውጥ ያሳያል። በዚህ ውስጥ የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የስኬቱ ዋና ተዋናይ ነው። በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጉዞ፣ ከቅርስ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ጎን፣ የፈረንሳይ ኤምባሲ የባህል ትብብር ፕሮግራም (service de Coopération et d'Action culturelle)፣ እና የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል ለአገሪቱ የታሪክ ግንዛቤ ዕድገትና የአርኪኦሎጂ ምርምር መዳበር ድጋፋቸው የጎላ ነው፤ ይህ በ1950ዎቹ የጀመረው የጋራ ትብብር፣ ዛሬም እንደቀጠለ ይህ ዓውደ-ርዕይ ምስክር ሆኗል።

ትዕግስት በተሞላበት ሁኔታ በአርኪኦሎጂ ተመራማሪዎች ቡድን፣ የተከናወኑ እልህ አስጨራሽ የመስክ ጥናቶች፣ በሺህዎች የሚቆጠሩ ታሪካዊ ቅርሶች እንዲሰበሰቡ፣ እንዲደራጁና እንዲጠኑ አስችለዋል። በዘርፉ ያለውንም ዕውቀትና ግንዛቤ በእጅጉ ያበለጸገ ሁኔታን ፈጥሯል። ይህም ጥረት በቅርስ ባለስልጣኑ ቤተ-መዘክር ለተቀመጡት ድንቅና ታሪካዊ ስብስቦች የጀርባ አጥንት ለመሆኑ ምስክር አያሻም። ጥቂት የተፈቀደላቸው ልሂቃንና ተመራማሪዎች ከቤተ-መዘክሩ ስብስቦች ጋር የመገናኘት ዕድሉ አላቸው። አሁን ብዙሃኑ ማህበረሰብና ዓላማ-መር ጎበኚዎች ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ፣ በተመረጡ ቅርሶች ተመርኩዘው ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ስልጣኔ አሻራ ግንዛቤ መጨበጥ የሚችሉበት፣ ቋሚ የሆነ የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ በብሔራዊ ሙዚየም ተከፍቶላቸዋል።

ዓውደ-ርዕዩ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት ክብርት ሳህለወርቅ ዘውዴና በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ክቡር ሬሚ ማርሾ መስከረም 19/2014 ዓ.ም ተመርቋል። የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን መስሪያ ቤትና የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል ባለሞያዎች ሙሉ የትግበራ እንቅስቃሴውን በጋራ መርተውታል፤ ልሂቃንን ከመጋበዝና ማሳተፍ እስከ አጠቃላይ ንድፍ በዚህ ቡድን ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሲሰሩ ቆይተዋል። የገንዘቡ ድጋፍ ከፈረንሳይ ኤምባሲ የተገኘና የሁለቱ ሀገራት የቅርስ ጥበቃና ጥናት የትብብር ማዕቀፍ አንድ አካል ነው።

ይህ በሳይንስና ባህል ዘርፍ ያለው ዲፕሎማሲያዊ ትብብር በኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ለተከፈተው ዓውደ-ርዕይ ገላጭ መጽሐፍ እንደሚያስፈልገው አመላክቷል። ስለሆነም ይህ መጽሐፍ በአውሮፓ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (Ministry of Europe and Foreign Affairs)፣ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኤምባሲ፣ የፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል፣ ሶሌብ አሳታሚ (éditions Soleb)፣ እና ነፃነት በጎ አድራጎት ተቋም ድጋፍ ለውጤት የበቃ ነው። ሥራውም የታሪካዊ አርኪኦሎጂ የደረሰባቸውን የዕውቀት ደረጃ የማካፈል፣ እና ተጨማሪ ማብራሪያና ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን አንዳንድ ቅርሶች የማሳየት ዓላማ ይዟል።

የኢትዮጵያ ጥንታዊነት በዓውደ-ርዕዩም ሆነ በዚህ መጽሐፍ ትኩረት ከተሰጣቸው ነጥቦች አንዱ ነው።ከዚህ አንጻር በዓውደ-ርዕዩ የተካተቱት ቅርሶች፣ የጽሑፍ ታሪክ መነሻን፣ ከደቡብ አረቢያ እና ሜዲትራኒያን አካባቢዎች ጋር የነበሩ ግንኙነቶችን፣ እንዲሁም

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ህዝቦችን የዕለት ተዕለት ሕይወት በሚያሳይ ተዕይንቶች የተደገፉ ናቸው። የአገሪቱ መካከለኛ ዘመን ባህልና ታሪክ በክፍለ-ዘመኑ ትኩረት ያገኘ፣ እናም በኢትዮጵያ ታሪካዊ ዘመን ከሚገኙ የተለያዩ የአርኪዮሎጂ ማስረጃዎች ጋር በተመጣጣኝ ሁኔታ የቀረበ ነው። በእርግጥ፣ የመካከለኛው ዘመን ማህበረሰቦች በተለምዶ በታሪካዊው ዘመን ውስጥ በተነሱ ሃይማኖቶች መሰረት እየተለዩ የሚቀርቡበት ሁኔታ ቢኖርም፣ የዓውደ-ርዕዩ አዘጋጆች በእነዚህ የዘመናት ምድብ ውስጥ የነበሩትን ማህበረሰቦች ግንኙነትና አስፈላጊነት በቁሳዊ ባህሎቻቸው ትስሥር ለማሳየት ሞክረዋል።  ይህም ወደ ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ በመመለስ ማንነቶች፣ ሃይማኖቶች፣ ባህል እና ድንበሮች ቋሚ ሳይሆኑ ተለዋዋጭና ተወራራሽ፣ ብሎም በብዙ ሁኔታዎች፣ በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ የተቀረጹ መሆናቸውን ያስታውሰናል።

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን፣ ከአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች የተሰበሰቡ ቅርሶችን በሳይንሳዊ አግባብ ጠብቆ ማቆየቱ፤ ባለፉት 70 ዓመታት ውስጥ የተመዘገቡትን የቁሳዊ ባህልና የታሪክ አሻራዎችን መርጦ ለማቅረብ ተችሏል። ከአንዳንድ ተቋማት፣ ተመራማሪዎች እና ዓለም ዓቀፍ ከሆኑ ቤተ መጻሕፍት ክምችቶች የተገኙ ምስሎችን ለማካተት ተሞክሯል። የቅርሶቹ ምርጫ በአዘጋጆች ብርቱ ጥረትና ሳይንሳዊ መንገድ የተከናወነ፤ በጥንቃቄ መለየት፣ ማፅዳት እና ማደራጀት የመሳሰሉ የአሥራር ሂደቶችን የተከተለ ነው። ከዚህ በዘለለ የቅርሶች ታሪካዊ አውድ ማብራሪያና ገለፃ በዋናነት የኢትዮጵያ እና የፈረንሳይ ባለሙያዎችን ያማከለ ቢሆንም የዓለም አቀፍ ሳይንሳዊ ኮሚቴ ድምር ውጤት እንደሆነ መናገር ይቻላል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር፣ የብሔራዊ ሙዚየም ዳይሬክተር፣ እንዲሁም አዘጋጆች፣ ከፕሮጀክቱ ጅማሮ እስከዚህ መግለጫ መጽሐፍ ህትመት ድረስ ላሳዩት ያልተቆጠበ ድጋፍና ቁርጠኝነት፣ በተጨማሪም የሳይንሳዊ አማካሪ ቦርድ አባላት፣ ሶሌብ አሳታሚ ድርጅት (éditions Soleb) እና የፈረንሳይ ኤምባሲ የባህል ትብብር ቡድን (service de Coopération et d’Action culturelle) ለሰጡት ሙሉ ድጋፍ ምስጋና አቀርባለሁ።

**ዦን-ኒኮላ  ባክ**

የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል

ዳይሬክተር  (እ.ኤ.አ ከ2022-2024 ዓ.ም)

# ማጣቀሻዎች

Francis **Anfray**
— "Une campagne de fouilles à Yĕḥā (février-mars 1960)", *Annales d'Éthiopie*, 5, 1963, pp. 171-232.
— "Matara : the Archaeological Investigation of a City of Ancient Eritrea", *P@lethnology*, 4, 2012.

E. **Bernan**, A. J. **Drewes** and R. **Schneider**, *Recueil des inscriptions de l'Éthiopie des périodes pré-axoumite et axoumite*, Paris, Académie des Inscriptions et Belles Lettres, De Boccard, 1991-2000.

Henri de **Contenson**
— "Les fouilles de Haoulti en 1959. Rapport préliminaire", *Annales d'Éthiopie*, 5, 1963, pp. 41-86.
— "Les fouilles à Axoum en 1957. Rapport préliminaire", *Annales d'Éthiopie,* 3 , 1959, pp. 25-42.
— "Trouvailles fortuites aux environs d'Axoum (1957-1959)", *Annales d'Éthiopie*, 4, 1961, pp. 15-38.

Carlo **Conti Rossini**, *Documenta ad illustrandam historiam. I, Liber Axumae*, vol. 54 and 58.2, Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium ; Scriptores Aethiopici, ser. 2, t. 24 and 27, Paris, 1909.

Catherine **D'Andrea** *et alii*, "The Pre-Aksumite Period : indigenous origins and development in the Horn of Africa", *Azania : Archaeological Research in Africa*, 58/3, 2023, pp. 329-392, on line: 10.1080/0067270X.2023.2236484.

Abraham-Johannes **Drewes**
— "Les inscriptions de Melazo", *Annales d'Éthiopie*, 3, 1959.
— *Recueil des Inscriptions de l'Éthiopie des Périodes Pré-Axoumite et Axoumite,* Tome III, *Traductions et Commentaires,* B, *Les Inscriptions Sémitiques*, Wiesbaden, Harrassowitz Verlag, 2019.

Nial **Finneran**, *The Archaeology of Ethiopia*, London, Routledge, 2007.

Iris **Gerlach**, "Cultural Contacts between South Arabia and Tigray (Ethiopia) during the Early 1st Millennium BC. Results of the Ethiopian-German Cooperation Project in Yeha*", *ZorA*, 6, 2013, pp. 264-277.

Jean **Leclant**, "Haoulti-Melazo (1955-1956)", *Annales d'Éthiopie*, 3, 1959, pp. 43-82.

Stuart C. **Munro-Hay**
— *Aksum: an African civilisation of late antiquity*, Edinburgh University Press, 1991.
— *Excavations at Aksum : an account of research at the ancient Ethiopian capital directed in 1972-74 by the late Dr Neville Chittick*, London, British Institute in East Africa, 1989.

David W. **Phillipson**
— (ed.), *The Monuments of Aksum: An Illustrated Account*, Addis Ababa University Press, London British Institute in Eastern Africa, 1997.
— *Foundations of an African civilisation: Aksum and the Northern Horn, 1000 BC-AD 1300*, Woodbridge, Currey, 2012.

Mike **Schnelle** et Daniela **Geyer**, "Grat Beʿal Gebri— a monumental half timber complex of the early 1st millennium B.C. in the Ethiopian Highlands", in Hubert Feiglsdorfer (ed.), *Earth Construction and Tradition*, vol. 2/4, Vienna, Institute for Comparative Research in Architecture, 2018.

Pawel **Wolf**, Ulrike **Nowotnick** and Saskia **Büchner**, *The Almaqah temple of Wukro in Tigrai / Ethiopia*, Berlin, Society for the Promotion of Museums in Ethiopia, 2017 ■

Francis **Anfray**, “Les stèles du sud Shoa et Sidamo”, *Annales d’Éthiopie*, 12, 1982.

R.P. François **Azaïs** and Roger **Chambard**, *Cinq années de recherches archéologiques en Éthiopie*, Librairie orientaliste Paul Geuthner, Paris, 1931.

Claire **Bosc-Tiessé** and Marie-Laure **Derat** (eds), *Lalibela. Site rupestre chrétien d’Éthiopie*, Toulouse, Presses universitaires du Midi, 2019.

Amélie **Chekroun**, “Ethiopian Medieval Islam. Towards a Documentary Revival”, *Revue des mondes musulmans et de la Méditerranée*, 153 | 2023, on line: http://journals.openedition.org/remmm/1926.

Marie-Laure **Derat** and Anne-Marie **Jouquand**, *Gabriel, une église médiévale d’Éthiopie. Interprétations historiques et archéologiques de sites chrétiens autour de Meshala Maryam (XV$^{e}$-XVII$^{e}$ siècle)*, Addis-Abeba, Centre français des études éthiopiennes-éditions De Boccard (*Annales d’Éhiopie*, hors-série), 2012.

François-Xavier **Fauvelle-Aymar** and Bertrand **Hirsch** (eds.), *Espaces musulmans de la Corne de l’Afrique au Moyen Âge*, Addis-Abeba, Centre français des études éthiopiennes-éditions De Boccard (*Annales d’Éhiopie*, hors-série), 2011, pp. 99-102. https://doi.org/10.4000/books.cfee.698.

François-Xavier **Fauvelle-Aymar** and Bertrand **Poissonnier** (eds), *La Culture Shay d’Éthiopie (X$^{e}$-XIV$^{e}$ siècle), Recherches archéologiques et historiques sur une élite païenne*, Addis-Abeba, Centre français des études éthiopiennes, éditions de Boccard (*Annales d’Éhiopie*, hors-série, 3), 2012.

François-Xavier **Fauvelle-Aymar** and Romain **Mensan** (dir), *Nora, ville islamique de l’Éthiopie médiévale (fin du XIII$^{e}$-début du XVI$^{e}$ siècle) : les fouilles de 2008*, Addis-Abeba, Centre français des études éthiopiennes, *Ad’É Books Archaeology & History*, 2024, pp. 177-178, https://doi.org/10.4000/12iz2.

Mohammed **Hassen**, *The Oromo and the Christian Kingdom of Ethiopia : 1300-1700*, Rochester, James Currey, (Eastern Africa Series), 2015.

Timothy **Insoll**, “Archaeological Perspectives on Contacts between Cairo and Eastern Ethiopia in the 12$^{th}$ to 15$^{th}$ Centuries”, *Journal of the Economic and Social History of the Orient*, 66, 2023, pp. 183-187. https://doi.org/10.1163/15685209-12341593.

Roger **Joussaume** and Jean-Paul **Cros**, *Mégalithes d’hier et d’aujourd’hui*, Errances-Hespérides, Arles, 2017.

Samantha **Kelly** (ed.), *A companion to medieval Ethiopia and Eritrea*, Leiden-Boston, Brill, 2020.

Julien **Loiseau**, Simon **Dorso**, Yves **Gleize**, David **Ollivier**, Deresse **Ayenachew**, Hiluf **Berhe**, Amélie **Chekroun** and Bertrand **Hirsch**, “Bilet and the wider world. New insights into the archaeology of Islam in Tigray”, *Antiquity*, 95 (April 2021), Issue 380, Cosmopolitanism in medieval Ethiopia (Timothy **Insoll** ed.), pp. 508-529.

Costantino **Pansera**, Quattro stele musulmane presso Ugogher Haribà nell’Enderta (fine sec. IV Egira), *Studi etiopici racolti da C. Conti Rossini*, vol. I, Roma, Istituto per l’Oriente, 1945, pp. 3-7.

Madeleine **Schneider**, “Stèles funéraires arabes de Quiha”, *Annales d’Éthiopie*, 7, 1967, pp. 107-122 ■

## መፍትሔ ቃላት

**ሐይማኖታዊ ደንብ** (processional)- ስርዓተ-ሃይማኖታዊ ተፈጥሮ ያለው፣ ክብር የተሞላበት እንቅስቃሴ፣ (መዝሙር፣ ጸሎት፣ ሰርግ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል)

**ሂጅራ**- የአረብኛ ቃል ሲሆን፣ ስደት ወይም ዘጸዓት የሚል ትርጉም አለው፤ ነብዩ ሙሀመድና ተከታዮቻቸው በ622 ዓመት ከመካ ወደ መዲና (ያትህሪብ) ካደረጉት ጉዞ ጋር ይገናኛል። ይህም ሁኔታ ለእስልምና ዘመን አቆጣጠር ቀመር መነሻ ሆነ፤ ይህ የዘመን አቆጣጠር ሂጅራ ይባላል።

**ሊተርጂካል** (liturgical)- በአምልኮ ወይም በመንፈሳዊ ሥርዓት ውስጥ ምስጋና እና ጸሎቶችን የሚያካትት ሊሆን ይችላል ግን የተለመደ ወይም የታወቀ ሥርዓት ነው።

**መሰዊያ**- በብሉይ ዘመን ለአማልክት ስጦታ የሚቀርብበት የተለየ ቦታ፣ ሳህን እና ጠረጴዛ ሊሆን ይችላል

**መስቀል ቅርጽ ንድፍ** (cruciform plan)- በመስቀል ቅርጽ የተገነባ

**መከላከያ መድሐኒት** (prophylactic)- ጤናን ከሚጎዱ ነገሮች ወይም በሽታን ለመከላከል የሚጠቅም መድሃኒት፣ ቅባት፣ ወይም ምግብ ሊሆን ይችላል።

**መካከለኛ ዘመን**- በጥንታዊ እና ዘመናዊ ዘመን መካከል ያለው ጊዜ

**መውቀር** (chiseling)- መሮ በመጠቀም ቅርጽ ወይም ጌጥ የማውጣት ሂደት (በመቦርቦር ወይም በመላጥ ሊሆን ይችላለ።

**ማለስለስ** (burnishing)- ጠንካራና ለስላሳ በሆነ መሳሪያ (ብዙ ግዜ የወንዝ ድንጋይ ወይም አለሎ) የሸክላ ዕቃን ውጫዊ አካል በመዳመጥ የማለስለስ፣ አንፀባራቂና ውሃ የማያሳልፍ የማድረግ ስራን ያመለክታል።

**ማቅረብ፣ መስጠት፤ ክልብ** (dedication)- አንድ ሥራ ወይም ስጦታ በአምላክ ወይም በአንድ ሰው ስም ማቅረብ። የተሰጠውን የሰራውን ሰው ለማስታወስ በሥራው ላይ ጽሑፍ ሊቀረጽ ይችላል።

**ምሰሶዎች፣ ቋሚዎች** (colonnade)- በህንፃ ወይም በመጠለያ ውስጥ ለጣራ ድጋፍ በተወሰነ እርቀት የሚቆም፤ ጣራ ተሸካሚ

**ሰሎሞናዊ ሥርዎ-መንግሥት**- ከ13ኛው እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያን ኢምፓየር ያስተዳደሩ ነገስታትን የሚወክል አስተዳደር፤ ከንጉሥ ሰሎሞን እና ንግሥተ-ሳባ የተገኘ መሆኑ የሚነገር የኢትዮጵያ ሥርዎ-መንግሥት

**ሰም የመሰለ ቅርጸ-አካል** (ሎስት-ዋክስ ካስቲንግ)- ከብረትና መስታወት ፈሳሽ ተፈላጊ ቅርጸ ቅርጾችን በትክክለኛ ቅጂ ለማምረት የሚጠቅም በፈለጉት አይነት ቅርጽ መቀያየር የሚችል

**ሰው-መሰል ቅርፅ የተላበሰ** (anthropomorphic)- በሰው አምሳል ወይም የሰው አካል ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ቅርፅ የተሰራ ነገር

**ሱልጣኔት**- በሙስሊም ሱልጣን የሚመራ የተለያየ መጠን የወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ ግዛት ወይም ሀገር

**ሳንቲም ማምረት** (minting)- ብረቶች ላይ ተፈላጊውን የሳንቲም ይዘትና ቅርጽ በማተም መቁረጥ ሂደት ነው

**ረጅም ጉዞ** (caravan)- ሸቀጥና መገልገያዎችን በተለያዩ የጋማ እንስሳት ላይ በመጫን በአስቸጋሪ መልክዓ-ምድርና በረሐዎች የሚደረግ ጉዞ ነው። ከነጋዴዎች (የሲራራ ንግድ)፣ አርብቶ አደሮችና ሐይማኖታዊ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያለው

**በጭስ ማከም** (smoking)- የሸክላ ዕቃዎች በእሳት ወይም በበቂ ሙቀት ከበሰሉ በኋላ፣ በሳር፣ በገለባ ወይም ሌሎች ቀላል ተቀጣጣይ ነገሮች ጭስ በማፈን የካርቦን ቅንጣቶች በላያቸው ላይ እንዲዋሃድና ጥቁር ወይም ግራጫ ቀለም እንዲኖራቸው የማድረግ ዘዴ ነው፣ ወዘማና ውሃ የማያሳልፉ እንዲሆኑም ይረዳል።

**ቡክራኒየም** (bucranium)- በቀንድ ከብት እናት አምሳል የተቀረጸና ዙሪያው በቅጠልና አበባ ጌጥ ንድፍ የተዋበ

**ባልጩት ድንጋይ** (obsidian)- ሲሊካ በሚባለው ማዕድን የበለጸገና ብርሃን የሚያንጸባርቅ የእሳተ ገሞራ ድንጋይ፤ የስምጥ ሸለቆ አካባቢ ይህ ድንጋይ በብዛት የሚገኝበት ስፍራ ነው።

**ባዝ-ሪሊፍ** (bas-relief)- ከዋናው አካል ትንሽ ወጣ ብሎ ተፈልፍሎ የተሰራ ቅርጽ ባዞላ ወይም ጥርብ ድንጋይ (አሽላር) - በመሮ ወይም መሰል መሳሪያዎች በአራት ማዕዘን ቅርጽ የሚዘጋጅ የወለል ወይም የግድግዳ ድንጋይ

**ተሰኪ፣ ተቆላላፊ ቅርጽ** (tenon)- ሁለት ነገሮችን እርስበርስ ለማያያዝ በሚሰሩ ተገጣጣሚ ቅርጾች ውስጥ፣ ተቀባዩ (mortise) ላይ ሊሰካ ወይም ሊገጥም የሚችለው ክፍል ነው። ብዙ ጊዜ በዕንጨት ስራ የሚስተዋል ዘዴ ነው።

**ተገጣጣሚ ግማሽ ክብ ቅስት** (arcature)- ተገጣጣሚና ጌጠኛ የበር፣ መስኮትና መሰል ክብ ቅስት ትክል ድንጋይ- ከአንድ ወጥ ድንጋይ በተለያየ ቅርጽና ንድፍ ወይም ተፈጥሯዊ ቅርጹን እንደያዘ መሬት ላይ ተተክሎ የሚገኝ ወይም የነበረ ነው

**ነሐስ** (bronze)- 75% የሆነ የመዳብ ቅይጥን የያዘ የብረት አይነት ነው ናብ አዳራሽ (nave)- ረጂምና ተያያዥ የሆነ አዳራሽ፣ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላኛው በቀላሉ መተላለፍ የሚያስችል ክፍተት ያለው ግንባታ ነው።

**አለት፣ የመሬት ጠንካራው ወለል፣** የመሬት መሰረት ድንጋይ (bedrock)- እንደ አፈር ካሉ የላይኛው መሬት አካል ስር የሚገኝ ጠንካራ ዓለት ወይም የድንጋይ ንብርብር

**አማልክት (ፓንቴዮን)** - ብዙ አማልክት ባሉት ሃይማኖት ውስጥ ያሉት የሁሉም አማልክቶች ድምር

**አርማ** (icon)- ቅዱስ ምስል፣ በአብዛኃኛው እንጨት ላይ የሚሳል፣ በኢትዮጵያና ምስራቅ አብያተ-ክርስቲያናት ክብር የሚሰጠው ነው

**አርብቶ-አደር**- በእርሻና ከብት እርባታ የሚተዳደር ማህበረሰብ

**አብርሀማዊ እምነት**- የአይሁድ፣ የክርስትናና፣ እስልምና እምነቶችን ያመለክታል

**አዳራሽ መሰል ንድፍ** (basilical plan)- ለሐይማኖት ወይም ለህዝብ መሰብሰቢያ አገልግሎት የሚታነጽ አዳራሽን ይገልጻል።

**ኢንትራዶስ** (intrados)- የግማሽ ክብ ቅስት ውስጠኛ ወይም ከስር ያለው ክፍል

**እንስሳት አምሳል**- በእንስሳት ቅርጽ ወይም መሰል ንድፎች የተሰራ ነገር

**እየሱሳዊ** (jesuit)- በሮማን ካቶሊክ ስር እ.ኤ.አ በ1540 ዓ.ም በኢግናስ ደ ሎዮላ በተቋቋመው እየሱሳውያን ማህበር አባል የሆነ ሰው እየሱሳዊ ይባላል።

**ዓመተ-ምህረት** (common era, CE)- ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለው ዘመን፤ እንዲሁም ዓመተ-ዓለም (before common era, BCE)- ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ዘመን ሲያመለክቱ ከክርስቲያኑ የዘመን አቆጣጠር የመነጩ መጠሪያ ናቸው

**ዓይናማ ንድፍ** (ኦፕንዎርክ) - የሥነ-ጥበብ አይነት ሲሆን፣ በብረት፣ እንጨት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ፣ ጨርቅ፣ቆዳ ወይም የዝሆን ጥርስ የመሰሉ ጠንካራ ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም የሚመረቱ ዕቃዎች ላይ ቀዳዳዎችን፣ ወይም ክፍተቶችን በመፍጠር የሚሰራ

**ዕጣን እና ከርቤ** (frankincence and myrrhe)- በምስራቅ አፍሪካ፣ አረቢያ እና እስያ ሀገሮች፣ ከሚገኙ ልዩ ዕፅዋት የሚሰበሰቡ መልካም መአዛ ያላቸው ለአምልኮ ስርዓትና ለመድሃኒትነት ተፈላጊ የሆኑ ሙጫዎች

**ከአንድ ወጥ ድንጋይ የተሰራ** (monolithic)- ከአንድ ድንጋይ የተቀረጸ ሐውልት፣ መታሰቢያ፣ ጌጥ፣ ወይም ህንጻ ሊሆን ይችላል።

**ኩፊክ** (kufic)- ስዕላዊ ውበት ያለው የአረቢኛ ፊደላት አጻጻፍ ዘዴ

**ካሚሊ ድርሃም** (kamili dirham)- በአዩቢድ ሥርዎ-መንግስት፣ በሱልጣን አል-ካሚል (1218-1238) ዘመን የተመረተ የብር ሳንቲም

**ካሜሊያን** (carnelian)- በከፊል የከበረ ድንጋይ፣ ማዕድን፤ ቡናማ ወይም ቀላ ያለ መልክ ያለው

**ካቦሾን** (cabochon)- በከፊል የከበረ ድንጋይ፤ ክብ ሁኖ የሚገኝ፣ የለሰለሰ ግን ያልተቀረጠ ድንጋይ ነው።

**ክምር ድንጋይ**- ብዙ ግዜ በመቃብርና የተለዩ መታሰቢያ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል በዛት ያላቸው ድንጋዮች ተሰብስበው የሚገኙበት

**ዝንጀሮ ራስ ንድፍ** (monkey heads)- በግንባታ ሂደት ከግድግዳ ወጣ ብለው እንዲታዩ የሚደረጉ ጫፎችን ያመለክታል፤ አብዝሃኛውን ጊዜ የጣራ ተሳላፊ ወይም የበርና መስኮት ጉበን ዕንጨቶች ላይ እንደጌጥ ይደረጋሉ።

**የመቃብር ላይ ጥቅስ** (ጽሑፍ) (epitaph)- ለሟች ማስታወሻ ወይም መታሰቢያ እንዲሁም የሟች መጨረሻ ቃል ኑዛዜ (እንዲህ ብላችሁ በቀብሬ ላይ ጻፉ የተባለ) ሊሆን ይችላል።

**የስእለት ስጦታ**- ስዕለቱ የደረሰለት አካል፣ ለገባው ቃል የሚሰጠው ስጦታ

**የሸክላ ቀለም** (glaze)- ቅባት-ነክ እና አንፀባራቂ ባህሪ ያለው፣ ፈሳሽ ነገር የማያሳልፍና ለማስጌጥ የሚጠቅም ልዩ የሸክላ ዕቃዎች ቀለም ነው።

**የቅሪተ-አካላት ቁፋሮ** (excavation)- የአፈርን ወይም ሌሎች ክምችቶችን በስልታዊ መንገድ በማንሳት የግኝቶችን አጠቃላይ አቀማመጥ እና መስተጋብርን መመልከትና መሰነድን ያካተተ ነው።

**የቅሪተ-አካል ቦታ**- በአርኪኦሎጂ ውስጥ፣ የቀድሞ እንቅስቃሴዎች (የቅድመ-ታሪክ፣ ታሪካዊ ወይም ዘመናዊ) ማስረጃ የሚገኝበት ቦታ፤ የተመረመረ ወይም ሊመረመር የሚችል እና የአርኪኦሎጂስቶች ትኩረት አካል የሆነ

**የቅርስ አቀማመጥና አቀራረብ** (museography)- በሙዚየም ስብስቦች እና ቅርሶች ላይ የሚደረግን ጥበቃ እና ለብዙሃን ዕይታ የማቅረብ ጥበብና ቴክኒክ ነው።

**የባህል መበረዝ** (acculturation)- ከአንድ የተለየ ማህበረሰብ ጋር በሚኖር የረጅም ጊዜ ግንኙነት የሚፈጠር የባህል ለውጥ

**የቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች** (secular clergy)- መነኮሳት ሳይሆኑ በቤተ-ክርስቲያናት ለምዕመናት አገልግሎት ለመስጠት የተሾሙ ዲያቆናትና ቀሳውስት

**የከተማ አምላክ** (tutelar god)- የአንድ ከተማ ጠባቂ አምላክ ወይም አማልክት

**የወገብ ጠርዝና ጌጥ ያለው** (carinated)- ከታችና ከላይ የኮን ቅርጽ ያለው፤ ሁለቱን ኮን ወይም ገበታ መሰል ቅርጾች ማጋጠሚያ ላይ በግልጽ የሚታይ አገናኝ የወገብ ቅርጽ ያለው የፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር መያዣ ዕቃ መለያ ቅጽል ስም ነው

**የድንጋይ ማኅተም** (intaglio)= ከለስላሳና ጠንካራ ድንጋይ ተቀርጾ የሚዘጋጅ ማኅተም

**የድንጋይ ዕቃ** (stoneware)- ለስላሳና አንፀባራቂ ባህሪን የተላበሰ ከድንጋይና ሸክላ አፈር ውህድ የሚሰራና በከፍተኛ ሙቀት የሚያልፍን ዕቃ ያመለክታል

**የግንባታ መሰረት** (ፖዲየም) - በሥነ ሕንጻ ውስጥ፣ ከመሬት ስር ተነስቶ ወደላይ የተሰራ የግንባታ መዋቅር ሲሆን አንድ ወይም ብዙ ተቀጣጣይ ንብብሮችን ለመደገፍ የሚያገለግል መሰረት ነው።

**የግድግዳ ጉጥ** (corbel)- የግንባታ አካል ሆኖ ከዋናው ግድግዳ ወጣ ያለ፣ ከድንጋይ፣ ዕንጨት፣ አርማታ፣ ወይም ብረት የሚሰራና ክብደት መሸከም የሚችል ቅጥያ ነው።

**የጸሎት፤ የቅዱሳን መታሰቢያ ስፍራ** (Shrine)- ለአያት፣ ጀግና፣ ሰማዕት፣ ቅዱስ፣ ለሆኑ አካላት አክብሮትና መታሰቢያነት የተዘጋጀ ወይም የተመረጠ ቅዱስ ቦታ፤ አምልኮና ጸሎት ይከናወንበታል

**ዲብ ወይም ጉብታ** (barrow)- በአንድ ወይም በርካታ መቃብር ስፍራ፥ በአፈር ወይም ድንጋይ ክምችት የተፈጠረ ደባል የመሬት አካል

**ዳሰሳ ጥናት**- የአርኪኦሎጂ ማስረጃ መኖሩን ለመለየት እና መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ የተለያዩ የምርምር ዘዴዎች

**ጃንደረባ** (eunuch)- በአንድ ማህበረሰብ ወይም የተለየ ተቋም ውስጥ ለተለየ አገልግሎት የተመረጠ ሰው፤ አገልጋይ፤ የዘር ፍሬው የተወገደ (ስልብ እንዲሉ)

**ጉበን** (architrave)- ከድንጋይ፣ ብረት ወይም ዕንጨት የተሰራ በሁለት ቋሚዎች ላይ የሚቀመጥ አግዳሚ ቅስት

**ግማሽ ክብ ቅስት ላይ የሚገኝ ጌጥ** (archivolt)- የበር፣ መስኮትና መሰል ክብ ቅስት ላይ ወጣ ብሎ ወይም በላዩ ላይ ተቀርጾ የሚገኝ ጌጥ

**ጠመዝማዛና ተሰካኪ ቅርጽ** (meandre)- ሥነ-ሕንጻ ወይም ጨርቃጨርቅ ስራ ውስጥ ዚግዛግ ወይም ተሽጋግረው የተሳሉ የሚመስሉ መስመሮችን ያካተተ ንድፍ

**ጥምር** (assemblage)- የተሳሰሩ-ቅሪተ አካላት (በኬሚካል ወይም በማዕድናት ምክንያት የሚፈጠር ቁርኝት)፤ አንድ ላይ ተቀብረው ወይም ተሰብስበው እንዲሁም ተያይዘው ሲገኙም በጥምረት የተገኙ ይባላል።

**ጥንታዊ** (antiquity) - ከፅሑፍ መጀመር ጋር ተያይዞ፣ ከቅድመ-ታሪክ ዘመን ቀጥሎ የመጣ፤ ከዚህ አንጻር በተለያየ ማህበረሰብ ውስጥ የተለያየ ጥንታዊ የዘመን ልኬት ሊኖር ይችላል።

**ጥንታዊ መጻህፍትና ጽሑፎች** (ማኑስክሪፕት) - በእጅ የተጻፈ ወይም የተገለበጠ ሥራ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ፣ ይህ ቃል በቤተ-ክርስቲያን ያሉ የብራና መጻሕፍትን ያመለክታል።

**ጥንታዊ የመቃብር ማዕከል** (necropolis)- የግልና የጋራ መቃብሮች በብዛት የሚገኙበትና ለዚሁ ተግባር የተወሰነ ስፍራ ሲሆን፣ ሐውልቶችንና መታሰቢያዎችን ሊይዝም ይችላል።

**ፖርሰሌን ሸክላ** (porcelain ware)- ስስ፣ ብርሃን ማሳለፍ የሚችል የሸክላ ዕቃ፣ በመጀመሪያ ቻይና ውስጥ የተሰራ፣ ከካኦሊን (ሲሊካ የያዘ ነጭ ማዕድን) የተሰራ እና ከ1,200 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ በሆነ ሙቅት እንዲበስል የሚደረግ ■





በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም፣ የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ፤ እ.ኤ.አ 2025 ዓ.ም

**ይህ መግለጫ መፅሐፍ፣** በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ውስጥ፣ ዕድሳት ተደርጎለት በ2014 ዓ.ም ዳግም ለህዝብ ለቀረበው፣ ቋሚ የታሪካዊ አርኪኦሎጂ ዓውደ-ርዕይ ማጠቃለያ ሥራ ነው። ይህም በተቋም ደረጃ ምስጋና በሚገባቸው፣ የፈረንሳይ ኤምባሲ፣ የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣንና የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል፣እንዲሁም በብሔራዊ ሙዚየም አማካኝነት እውን ሆኗል። ለዚህም ስኬት መሪ ለሆኑት፣ የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አበባው አያሌው፣ እንዲሁም የብሔራዊ ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈጻሚ አንዷለም ግርማዬ ያለንን አክብሮትና ምስጋና እናቀርባለን። በተያያዘ፣ ንጉሴ መኮንን እንዲሁም ሁሉም አስጎብኚዎችና የሙዚየሙ የሥራ ባልደረባዎች ምስጋና ይገባቸዋል።

ይህ መልካም ሥራና ውጤት የፈረንሳይ ኤምባሲ የባህልና ትብብር ማዕቀፍ ድጋፍና የቡድኑ አስተዋፅኦ ባይታከልበት ምናልባትም እውን መሆኑ ያጠራጥር ነበር፤ ስለሆነም ሶፊ ማካሜ፣ ሎራ ሴራኖ እና አሌክሲ ማክሌን እናመሰግናለን።

የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል የሥራ ባልደረቦች ሊያ ሮኤ እና ፍሎሪያ ዶላዲል ለእንግሊዝኛው ቅጂ ዳግም ንባብ፣ ትንሳኤ እስክንድርና አበባ አማረ ለዐማርኛው ቅጂ ጽሑፍ ትየባና እርማት፤ እንዲሁም ጋይታን ሪቻር የፈረንሳይኛውን ቅጂ በመገምና በማረም ላበረከተው አስተዋጾ፣ በጠቅላላው ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

የዓውደ-ርዕዩ እና የመግለጫ መፅሐፉ ይዘት የሳይንሳዊ ኮሚቴው ብርቱ ጥረት ውጤት ነው፤ ስለዚህ አበባው አያሌው፣ አህመድ ሀሰን፣ አንዷለም ግርማዬ፣ በረከት ዘውዱ፣ ብርሀነ አስፋው፣ ክሌር ቦስክ ቴሴ፣ ብሩክ ጂፋር፣ ደመረው ዳኜ፣ ማሪሎር ደራ፣ ደረሰ አየናቸው፣ ክሌሞ ሜናር፣ ታከለ መርዕድን ለምስጋና ስማችሁን አንስተናል።

አለምሰገድ ባልዳዶስ፣ በሀይሉ ሀብቴ፣ ኤፍሬም አማረ፣ ወርቁ ደራራ፣ ዮናስ በየነ፤ የመፅሐፉን ይዘት በማየትና በማረም ላበረከቱት አስተዋጾ፤ በተለይ አናይስ ቪዮ ጥንቃቄ ለተሞላው እይታና ማስተካከያ ምክረ-ሀሳቦቿ ከልብ እናመሰግናለን።

በሀይሉ ሀብቴ እና ኤፍሬም አማረ፤ መረጃዎቻችሁን ስለ ቅርስ ተቋሙ ታሪክ በማጣቀሻነት ተጠቅመናል፣ እናመሰግናለን። አናይስ ላሜሳ በካርታዎችና ሌሎች ንድፎች ዙሪያ ላደረገችው ድጋፍ እናመሰግናለን።

ዦን-ማርክ ቦቶኔ በፎቶ መረጃ ማደራጀት ወቅት ላደረገልን ከፍተኛ ድጋፍ ከልብ እናመሰግናለን። በዝርዝር ለመግለጽ ባይቻልም፣ ፎቶዎችንና ምስሎችን እንድንጠቀም ፈቃዳቸውን የቸሩን ተቋማትና ተመራማሪዎች በጥቅሉ ምስጋናችንን እነሆ ብለናል።

በመጨረሻም ያለ ጸሐፊዎች ድጋፍና ቸሮታ እዚህ አልተደረሰምና ልባዊ ምስጋናችን በያሉበት ዓለም እነሆ ብለናል። ■

**አለባቸው በላይ** አርኪኦሎጂስት
(ደብረ-ብርሐን ዩኒቨርሲቲ/
Cfee-አዲስ አበባ) 66, 70, 74

**አየለ ታረቀኝ** አርኪኦሎጂስት
(አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) 36

**ክሌር ቦስክ-ቴሴ** የስነ-ጥበብ ታሪክ ምሁር
(Cnrs፣ Ehess፣ የአፍሪካ ጥናት ተቋም-ፓሪስ/
Cfee-አዲስ አበባ) 49, 52

**አሜሊ ሼክሩን እና** የታሪክ ምሁር
(Cnrs፣ Iremam፣ አያክስ-ማርሴይ ዩኒቨርሲቲ /
Cfee-አዲስ አበባ) 43, 56, 62

**ሉሲል ደኒዞ** አርኪኦሎጂስት
(Cfee-አዲስ አበባ፣
ቧሮ ሙዚየም ዳይሬክተር) 7, 15, 18, 22, 24,
26, 32, 38, 40

**ማሪ-ሎር ዴራ** የታሪክ ምሁር
(Cnrs፣ Orient & Méditerranée፣
ፓሪስ/ Cfee-አዲስ አበባ) 43, 45, 54

**ደረሰ አየናቸው** የታሪክ ምሁር
(HornEast project Erc /
Cfee-አዲስ አበባ) 45

**ሲሞ ዶርሶ** አርኪኦሎጂስት
(Orient & Méditerranée፣ ፓሪስ I ፓንቴኦ
ሶርቦ ዩኒቨርሲቲ) 60, 62

**አንቱአን ጋሪክ** የድንጋይ ግንባታ ባለሞያ
(Cnrs, Cfee, Addis Ababa) 79

**አን-ሊዝ ጉዦ** አርኪኦሎጂስት
(Cfee-አዲስ አበባ/ Temps፣ Paris) 7, 54,
66, 70, 72, 80

**ሕሉፍ በርሔ** አርኪኦሎጂስት
(መቀሌ ዩኒቨርሲቲ/
Cfee-አዲስ አበባ) 30, 38

**ቲሞቲ ኢንሶል** አርኪኦሎጂስት
(የአረብና እስላማዊ ጥናቶች ተቋም፣
ኤክስተር ዩኒቨርሲቲ) 56

**ዡሊያ ሎአዞ** የታሪክ ምሁር
(ኢያክስ-ማርሴይ ዩኒቨርሲቲ፣
Iremam-አያክስ-ማርሴይ) 58

**ክሌሞ ሜናር** አርኪኦሎጂስት
(Cfee-አዲስ አበባ/ የቱታቨል ቅድመ-ታሪክ ጥናት
ማዕከል በአውሮፓ- ዳይሬክተር) 7

**ሮማ መንሷ** አርኪኦሎጂስት
(የፈረንሳይ ኮሌጅ- ፓሪስ/
Traces-ቱሉዝ/ Cfee-አዲስ አበባ) 62

**ሃና ፓርሰን-ሞርጋን** አርኪኦሎጂስት
(የአረብና እስላማዊ ጥናቶች ተቋም፣
ኤክስተር ዩኒቨርሲቲ) 64

**በርትራን ፖአሶኔ** አርኪኦሎጂስት
(Inrap/ Traces-ቱሉዝ) 72

**ካሮሊን ሮቢዮ-ብሩነር** አርኪኦሎጂስት
(Cnrs፣ Traces-ቱሉዝ/
Cfee-አዲስ አበባ) 81

**ተክሌ ሐጎስ** አርኪኦሎጂስት
(አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) 26

**ዮሐንስ ገ/ሥላሴ** የታሪክ ምሁር
(መቀሌ ዩኒቨርሲቲ/
ኤርፈርት ዩኒቨርሲቲ) 24

ጥቁርና ነጭ ቀለም ፎቶዎች
ከአርኪኦሎጂ ኢኒስቲቲዩት ምስል
ክምችት የተወሰዱ፣ በአብዝሃኛው
የከበደ ቦጋለና ፍራንሲስ አንፍሬይ
ስራ ውጤት ናቸው።

የመካነ-ቅርስ ቦታ ፎቶዎች
በተመራማሪዎች መልካም ፈቃድ
የተካተቱ ሲሆኑ ሌሎች ፎቶዎች
በጠቅላላ በዚሁ ፕሮግራም
በጥንቃቄ የተነሱ ናቸው።

የዓውደ-ርዕዩን አሁናዊ ገፅታ
የሚያሳዩ ሁለት ፎቶዎች-
በአን-ሊዝ ጉዞ

የሳይንሳዊ ኮሚቴ አባላት
አበባው አያሌው፣ አህመድ ሀሰን፣
አለምሰገድ በልዳዶስ፣
አንዷለም ግርማዬ፣
በሀይሉ ሀብቴ፣ በረከት ዘውዱ፣
ብርሀኔ አስፋው፣ ክሌር ቦስክ ቴሴ፣
ብሩክ ጂፋር፣ ደመረው ዳኜ፣
ማሪሎር ደራ፣ ደረሰ አየናቸው፣
ኤፍሬም አማረ፣ ክሌሞ ሜናር፣
ታከለ መርዕድ፣
አናይስ ዊዮ፣ ወርቁ ደራራ፣
እና ዮናስ በየነ

የዓውደ-ርዕይ ፅንሰ-ሃሳብ አዘጋጆች
አበባው አያሌው፣
ደመረው ዳኜ፣ ሉሲል ደኒዞ፣
አን-ሊዝ ጉዞ፣ ክሌሞ ሜናር

የህትመት ባለመብቶች
የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን/
የኢትዮጵያ አርኪኦሎጂ
ኢኒስቲቲዩት፤ ገጽ 11፣ 12፣ 14፣
17፣ 19፣ 20፣ 21፣ 33፣ 35፣ 42፣
48፣ 50፣ 68 እና 76
የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ጥናት
ማዕከል/ የኢትዮጵያ አርኪኦሎጂ
ኢኒስቲቲዩት፤ ገጽ 50
ማሪ-ሎር ደራ፤ ገጽ 47
ሮማ መንሳ፤ ገጽ 57 እና 78
ሮዤ ጁሶም፤ ገጽ 67

ሕትመት ዲዛይን
አን-ሊዝ ጉዞ፣
ሉሲል ደኒዞ
እና ለ-ጉዊ
የመጽሐፉ ሳይንሳዊ አደረጃጀት
አን-ሊዝ ጉዞ
እና ሉሲል ደኒዞ
የሕትመት አስተባባሪዎች
ዣ-ኒኮላ ባክ፣
ኮንስታንስ ፐሪን-ዡሊ
እና ኦሊቪዬ ካቦን
የመጽሐፉ ዲዛይንና ገጽ ቅንብር
ኦሊቪዬ ካቦን
የዐማርኛ ትርጉም
ስንታየሁ ኀበዜ
ፎቶና ሚዲያ
ለ-ጉዊ
እና ሁኅ ዱሳ
ፎቶ ቅንብር
ኦሊቪዬ ካቦን
እና ሁኅ ዱሳ

**English version**
print
ISBN 978-2-918157-65-6
free digital
ISBN 978-2-918157-66-3

**French version**
free digital
ISBN 978-2-918157-69-4

**Amharic version**
print
ISBN 978-2-918157-67-0
free digital
ISBN 978-2-918157-68-7

**éditions Soleb 2025**



AMBASSADE DE FRANCE EN ÉTHIOPIE ET AUPRÈS DE L'UNION AFRICAINE
Liberté Égalité Fraternité

cfee Centre français des études éthiopiennes

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ethiopian heritage authority

UMIFRE Unités mixtes des instituts français de recherche à l'étranger

NetSnet



N
0 500 1 000 km
Massawa
Asmära
Adulis
Mäṭära
Yəḥa
Aksum
Kʷiha / Bilet
Maqala
Gondär
Lalibäla
Səmära
Djibouti
Baḥər Dar
Zayla'
Däse
Qeṭetiya
Tätär Gur
Asosa
Nora
Däbrä Bərhan
Derre Dawa
Harla
Ǝnsälale
Jigjiga
Harär
Sure Qäbänawa
Naqamtee
Addis Abäba
Tiya
Gambella
Asälla
Jimma
Hawasa
Dila
Chelba-Tutitti
Tuto Fela
Arba Mənç
Site
City
River
Lake
Jinka
0 100 200 km

# የኢትዮጵያ የታሪክ ዘመን የጊዜ ሰሌዳ


የተለያየ ቀለም ቅብ ያላቸው ንድፎች ታዋቂ የባህላዊ አካባቢዎችን እና ሐይማኖት ተከታይ ለሆኑ ማህበረሰቦች አመላካች ናቸው። የመልካዓ-ምድራቸው ወሰንና ቀጣይነት ተመሳሳይ ቀለም ተጋርቷል። ይህ ገለፃ ከንድፍ በዘለለ ውስብስብ፣ መድብለ ባህልና መድብለ ሃይማኖት የሆነውን ማህበረሰብ ፍፁም ውክልናን አይወስድም


■ **ሐምራዊ-** ከአብርሃማዊ እምነት ውጪ ያሉና ከግዙፍ ድንጋይ ጋር የተገናኘ ባህል ያላቸው

■ **ብርቱካናማ-** ጥንታዊ


■ **ሰማያዊ-** ክርስቲያን


■ **አረንጓዴ-** ሙስሊም






2ኛው ሺህ ዓመት ቅ.ል.ክ.
2nd millennium BCE







500
600
700
800
900
1000
1100
1200
1300
1400
1500
1600
1700
2ኛው ሺህ ዓመት ዓ.ክ.
2nd millennium CE



**ይህ መግለጫ መፅሐፍ፤** የአርኪኦሎጂስቶች፣ የታሪክ ምሁራን፣ የሥነ-ጥበብ ታሪክ አዋቂዎች፣ የጥንታዊ ፅሑፎች ጥናት ባለሞያ (epigraphist)፣ እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድ የጥንታዊና መካከለኛው ዘመን ታሪክ ተመራማሪዎች ድምር ውጤት ነው። የማህበረሰብ ዓርማ ከሆኑ ቅርጻ-ቅርጾች እስከ ዕለት ተዕለት መጠቀሚያ ቁሶችን ያማከሉ 17 የቅርሶች ስብስብ በዚህ መፅሐፍ ተካተዋል። እነዚህም በዕድሜ ቅደም ተከተል፣ ታሪካዊ ዕሴቶቻቸው እና በኢትዮጵያ የታሪክ ሂደት ውስጥ ጥልቅ ምልከታ እንዲኖር በማስቻል አቅማቸው የተመረጡ፤ ከዋና ዋና መካነ-ቅርስ ቦታዎች የተገኙ ናቸው። የቁሳዊ ቅርሶቹ ብዝኃነት፣ በክህሎት የዳበረ ዕደ-ጥበብ ሞያን፤ የቅርሶቹ በተለያየ መልክዓ-ምድርና ዘመናት መገኘት ድግሞ ያልተገደበ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ፣ መድብለ-ባህል፣ ተያያዥነትና የእርስ በእርስ ግንኙንት ነፀብራቅ ናቸው።

free digital version
Isbn 978-2-918157-68-7
printed version
Isbn 978-2-918157-67-0

ISBN-13: 978-2-918157-67-0
9 782918 157670

s o l e b
5 rue Guy-de-la-Brosse
75005 Paris